## ክፍል ሰባት

### የአስፍሐ ወልደሚካኤል መንግሥት

### (ነሐሴ 1955 - ኅዳር 1962)

ገጽ

1. አስፍሐ ማን ነው? ........ 461
2. ዳግማይ መራህ መንግሥቲ ........ 466
3. የመጀመሪያው ዓመት ........ 469
4. ሁለተኛው የአስፍሐ ዘመን ........ 484
5. ባንዲራው የኢትዮጵያ ሆነ ........ 486
6. በኢትዮጵያ ሁለት መንግሥት የለም ........ 488
7. ሶስተኛው ዘመነ አስፍሐ ........ 490
8. የፌዴሬሽኑ መፍረስ አስፈላጊ ነበር ........ 492
9. ባይ ባይ ፌዴሬሽን ........ 502

# አስፍሐ ማን ነው?

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር መጋቢት 13 ቀን 1914 ዓ.ም በአካለ ጉዛይ አውራጃ በሰገነይቲ ከተማ የተወለዱት አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ በከረን ከተማ ዘርዓ ክህነት ከተባለው የጣልያን ትምህርት ቤት የተመረቁ ናቸው።

ከልጅነታቸው ጀምሮ የኢትዮጵያዊነት ያገር ፍቅር ስሜት ያደረባቸው መሆኑን አጋጣሚ ዕድል ባገኙ ቁጥር ለማሳየት ይሞክሩ ነበር። በ1930 ዓ.ም የጣልያን አልጋ ወራሽ ልዑል ዑምቤርቶና የዱካ ዳኦስታ እናት ከረንን ለመጎብኘት ሲመጡ፣ ከዘርዓ ክህነት ተማሪዎች መካከል፣ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ መርጠ ው እንዲያነቡ አስፍሐ ተመደቡ። ወጣቱ ተማሪ በታዘዙት መሠረት፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ « ዮሴፍን ወንድሞቹ ለአሳፊ ነጋዴዎች እንደሸጡት » የሚገልጸውን ጥቅስ መርጠው በጋለ መንፈስ አነበቡት። እንግዶቹም በተማሪው ንቃትና በቋንቋ አቀራረቡ መደሰታቸውን ገለጡ። ጉብኝቱ ከተፈጸመ በኋላ፣ የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር አስፍሐን ለብቻ ጠርቶ ይህን ጥቅስ ለምን መረጥክ ? ብሎ ጠየቃቸው። « ...... <u>እኛ ኤርትራውያኖች ንጉሥ ምኒልክ ለጣልያን ሸጠውን ነው እንጂ፣ ኢትዮጵያውያን ነን</u> ...... » ብለው መለሱለት። መንፈሳዊው መምህር በወጣቱ አስፍሐ አስተሳሰብ ከመደነቅ በስተቀር ለምን ፖለቲካ ውስጥ ገባህ? ብሎ እርምጃ አልወሰደባቸውም። የኤርትራ ሕዝብ የጣልያን ኮሎኒ ሆኖ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ፣ አፄ ምኒልክ ሸጡን ለወጡን በሚል ፕሮፓጋንዳ የተመረዘ በመሆኑ፣ እንኳንስ በዚያን ጊዜ፣ ዛሬም ቢሆን ይኸው አስተሳሰብ አልተለወጠም።

አስፍሐ ወልደሚካኤል በካቶሊክ ሀይማኖት የተጠመቁና በሚሲዮን ያደጉ በመሆናቸው፣ ጣልያንኛቸው በጣም ጥሩ ነው ተብሎ ይደነቅላቸዋል። ከዚህ የቋንቋ ችሎታቸው የተነሳ፣ ከአሥራ ስምንት ዓመት ዕድሜያቸው ጀምሮ፣ ለአሥር ዓመታት የሥራ ኤክስፔሪያንሳቸው የዳበረው በአስተርጓሚነት ሥራ ላይ ነው። በ1936 ዓ.ም ጣልያን መላ አገራችንን ከያዘ በኋላ፣ በሙሶሊኒ ለተሾሙት የኢትዮጵያ ገዥዎች፣ ለዱካ ዳኦስታና (DUCA DAOSTA) በተለይም ለጄኔራል ናዚ በቅርብ ለማገልገል የበቁት በዚሁ በአስተርጓሚነት ሞያቸው ነበር። በነዚሁ የፋሽስት ባለሥልጣኖች ድጋፍ ወደ ሮማ ተልከው፣ በቅኝ ግዛት ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ፣ ለጥቂት ጊዜ የአድሚኒስትራሲዮን የሥራ ልምድ ካደረጉ በኋላ፣ ለማዞትና ለእሥር ወደ ጣልያን አገር ተይዘው ለተላኩት፣ የኢትዮጵያ መኳንንቶችና ከፍተኛ ባለሥልጣኖች፣ ጉዳይ ፈጻሚና አነጋጋሪ ሆነው ሠርተዋል። በዚሁ ጊዜ እሥረኞቹ በዕለት ሕይወታቸውና በመኖሪያቸው መንገላታት እንዳይደርስባቸው፣ አስፍሐ ለቅኝ ግዛት ጉዳይ ሚኒስትሩ በጥሩ ሁኔታ በማስረዳት፣ ከፍ ያለ እርዳታ ማበርከታቸውን ብዙዎቹ ኢትዮጵያውያኖች ያስታውሱላቸዋል።

በ1937 ዓ.ም የታወቀው የፋሽስት መምህር ኤንሪኮ ቸሩሊ (ENRICO CHERULLI) የኢትዮጵያ ገዥ የዱካ ዳኦስታ ምክትል ሆኖ ሲሾም፣ አስፍሐን የካቢኔው አባልና አማካሪ አድርጉ መደባቸው። በዚያን ጊዜ የአስፍሐ ፍላጎት ሮማ ቆይቶ ከፍተኛ ትምህርት ለመቀጠል ነበር። ቸሩሊ ግን ለኢትዮጵያ አድሚኒስትራሲዮን ችሎታህ በቂ ነው ብሎ አገዳቸው። ወደ አዲስ አበባ ከመመለሳቸው በፊት፣ በቸሩሊ አማካይነት በቬኔሲያ ቤተመንግሥት (PALAZZO

VENEZIA) ሙሶሊኒ ዘንድ ቀርበው በጥቂት ዓመታት ውስጥ ለፈጸሙት መልካም አገልግሎት፣ « ካቫሊየሬ » የተባለውን የፈረሰኛ ደረጃ ኒሻን ተሸለሙ:: ኒሻኑን ደረታቸው ላይ ያንዠረገገላቸው እራሱ ሙሶሊኒ መሆኑንና እጃቸውንም ጨብጦ ምስጋና እንዳጉረፈላቸው፣ አስፍሐ በሰፊው አስረድተውናል:: በግራሲያኒ (GRAZIANI) ቦታ የተተካው ዱካ ዳኦስታም፣ አስፍሐ ከሮም ሲመለሱ የፊታውራሪነት ማዕረግ ሰጥቷቸዋል::

አስፍሐ ወልደሚካኤል በወጣትነታቸው ዘመን፣ በብልህነታቸውና በትጋታቸው በፋሽስት መሪዎች ዘንድ ከፍተኛ ግምት የተሰጣቸው መሆኑንና፣ ከዚህም በላይ ሹመትና ሽልማት ማግኘታቸውን አንድም ቀን ምስጢር አድርገውት አያውቁም:: በዚህ ዓለም በኖሩበት በሰማኒያው ዓመታት ውስጥ፣ በዚያ በጨካኙ የፋሽስት ዘመን የወገናቸውን የብዙውን ኢትዮጵያዊ ሕይወት ለማትረፍ በፈጸሙት በጎ ሥራ፣ የሚደሰቱና የሚኩሩ ነበሩ:: « ...... ኢትዮጵያን የያዝነው ሕዝቡን ለማሠልጠንና ከጨለማ ወደ ብርሃን ለማሻገር ነው ብላችሁ፣ ለዓለም የተናገራችሁት ቃል ዛሬ የት ደረሰ ...... በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚፈጸመው ሁሉ፣ አለፍርድ መግደል፣ ከሰብዓዊ መንፈስ ውጭ ማሰቃየት ከሆነ፡ ማን ይቀበላችኋል ? ...... አገሩንስ አለ ሕዝቡ መሬቱን ብቻ መግዛት ትችላላችሁ ወይ ? ...... » በማለት፡ አስፍሐ ለጄኔራል ናዚ እና ለዱካ ዳኦስታ የሚያቀርቡት ሀሳብ ቀስ በቀስ ተደማጭነትን እያገኘ፣ ብዙ ኢትዮጵያውያኖች ከሞትና ከሥቃይ፣ ከእሥራትና ከመጉላላት መዳናቸው በሰፊው ተመስክሯል:: በእሳቸው እርዳታ ከሞት የተረፉት አንዳንዶቹ ኢትዮጵያውያኖችም፣ አስፍሐ ወልደሚካኤል በዚያ በክፉ ዘመን ለወገናቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳዩት ተቆርቋሪነትና የፈጸሙት ሰብዓዊ ሥራ « የውስጥ አርበኝነት ማዕረግ » ሊያሰጣቸው ይገባል የሚል ሀሳብ ያቀረቡ ነበሩ:: ሌሎች ደግሞ ይህን ሀሳብ በመቃወም ሲተቹ፡ « ...... ፋሽስቶች በሕዝቡ ላይ የሚፈጽሙት ግፍ አሳዝኗቸው፣ ብዙዎቹን ወገኖቻቸውን ከሞትና ከስቃይ ለማዳን አስፍሐ ወልደሚካኤል ያደረጉት ጥረት ትልቅ ሰብዓዊ ሥራ ሆኖ መቆጠሩ የተገባ ነው:: ይሁን እንጂ የፋሽስት ገዥዎች የአስፍሐን ምክር አዳምጠው፣ የግፍ አገዛዛቸውን በመለወጥ፣ ሠላማዊ የሆነ አስተዳደር ሲመሠርቱ፣ ይህ ፖሊሲያቸው የኢትዮጵያን የነፃነት ንቅናቄ ለማዳከምና፣ እያታለለ የታጋዩን ሕዝብ ቁጥር ለመቀነስ አልረዳም ወይ ? ...... ለምሣሌ ብዙ ሕዝብ ወደ ጫካ ገብቶ መራራውን የአርበኝነት ሕይወት መቀበል የጀመረው፡ ጨካኙ ግራሲያኒ በየካቲት 1937 ዓ.ም ከፈጸመው አሰቃቂ ዕልቂት በኋላ አይደለም ወይ ? ...... ስለዚህ፡ እኒ አስፍሐ የፈጸሚቸውን አንዳንድ በጎ ሥራዎች ለይቶ የሚገባውን መልካም አስተያየት ከማድረግ በስተቀር፣ የውስጥ አርበኝነት ደረጃ መስጠት ተገቢ አይደለም ...... » የሚል አስተያየት ሰጥተዋል:: ጥቂቶች ደግሞ የአስፍሐን የፋሽስት ዘመን ታሪክ የሚያሳፍር አድርጉ ለማሳየት፣

የናዚ አስተርጓሚ፡ የሙሶሊኒ ተሸላሚ
የዱካ ዳኦስታ ፊታውራሪ፡ የቸሩሊ ዋና አማካሪ

እያሉ፣ በግጥም መልክ በመጻፍ የበተኑ ነበሩ:: አስፍሐ ግን በዚህ ምንም አልተነኩም:: ይልቁንም የተጻፈው ስህተት የማይገኝበት ትክክል ነው በማለት ሊያሳፍሯቸው የደከሙትን ጠላቶቻቸውን አሳፍረው መልሰዋቸዋል:: ይህን በመሰለ ሁኔታ እኔ ራሴ ምስክር ሆኜ ያየሁት፣ አንድ የደረሰ ነገር ትዝ ይለኛል:: ጊዜው ግንቦት 1966 ዓ.ም ነው:: ቢትወደድ አስፍሐ፣ በአዲሱ የጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ካቢኔ የፍርድ ሚኒስትርነታቸውን ለአቶ ማሞ ታደሰ አስረክበው፣ አቶ አበበ ረታን



ፊታውራሪ አስፍሐ ወልደሚካኤል
(ኋላ ደጃዝማች፣ ቢትወደድ)

በኤርትራ የንጉሠ ነገሥቱ ም/እንደራሴ 1952 - 1962

የኤርትራ ጠቅላይ አስተዳዳሪ (ቺፍ ኤግዚኩቲፍ) 1955 - 1962

በመተካት ጤና ጥበቃ የተዛወሩበት ሰሞን ነው:: ቢትወደድ አስፍሐ በተገኙበት በአንድ ወዳጅ ቤት የራት ግብዣ ላይ፣ ኢትዮጵያውያን ሐኪሞች በቀድሞው የጤና ጥበቃ ሚኒስትር አሠራር አልተደሰቱም የሚል ስሬ ክርክር ተይዞ ነበር:: ቢትወደድ የሚደረገው ውይይት አልጣማቸውም:: ሆኖም « ..... እኔ እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያውያን ሐኪሞች የተበሳጩበት ጉዳይ መኖሩን የሚያመለክት መረጃ አልደረሰኝም:: ..... » አሉ::ወዲያው በአርበኝነታቸው በጣም የሚኩሩ አንድ ደጃዝማች፣ ድንገት ብልጭ ብሎባቸው ጨዋ ባልሆነ መንገድ፣ « .... እናንተ፣ ባንዶች ሆናችሁ ለጣልያን ስታገለግሉ፣ የኢትዮጵያ አርበኞች በያለበት የሚያዘጋጁትን የጦር ኘላን በመረጃ የምትሰበስቡበት ዘዴ እንዴት ነበር ? .... » ብለው ጠየቋቸው:: በድንገት ያ የሞቀ ጨዋታ ቀዝቅዞ ለጥቂት ደቂቃ በሁሉም ዘንድ ድንጋጤ ታየ:: ቢትወደድም የረጋ መንፈሳቸውን ሳያደፈርሱ በረቀቀና ጨዋ በሆነ አነጋገር መልሱን በፍጥነት ሰጡ:: « ...... ማንም ሰው እንደሚያውቀው እኔ ለፋሽስት መንግሥት ደንበኛ አስተርጓሚው ሆኜ ሠራሁ እንጂ፣ ፊርማቶሪው አልነበርኩም:: ...... ሆኖም አንዳንድ አርበኞች ነን ባዮች፣ ገንዘብ ከተሰጠን ለጣልያን ገብተን እናገለግላለን እያሉ የሚጽፏቸውን ደብዳቤዎች፣ ከአማርኛ ወደ ጣልያንኛ በመተርጐም አንዳንድ ምሥጢር የማውቅ መሆኔን አልክድም ..... » አሏቸው:: ይህንን ውርጅብኝ የተከናነቡት ደጃዝማች ምንም ሳይናገሩ ብድግ ብለው ከግብዣው ቤት ወጡ::

አስፍሐ ወልደሚካኤል ለፋሽስት መንግሥት የሰጡትን አገልግሎት ምን ጊዜም ለመደበቅ የሞከሩበት ጊዜ አልነበረም:: « .... ባንዳ በተባለው ስሜ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼን በመርዳት ብዙ ሰብዓዊ ተግባር የፈጸምኩበት በመሆኔ፣ ሕሊናዬ ንፁሕ ነው ...... » እያሉ፣ እስከ ሕይወት መጨረሻቸው ድረስ ይናገሩ ነበር:: እኔም ከብዙ ዘመን ጀምሮ ስለሚያውቁኝ ወዳጅነቴን በመተማመን አንድ ቀን ደፍሬ « ... በፋሽስት ዘመን ብዙዎቹን ወገኖችዎን ለማዳን የቻሉት፣ ለጠላቶችዎ ጥሩ አገልግሎት በመስጠት እምነት ስለተጣለብዎ መሆኑ ግልጽ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ብቻዎን ከሕሊናዎ ጋር ሲሟገቱ፣ በሰጡት አገልግሎት ውስጥ አንዳንድ የሚቆጭዎ ነገር ያጋጥምዎታል ወይ ? ....» ብዬ ጠይቄያቸው ነበር:: ባጭሩ በሰጡኝ መልስ፣ «... መቸም እንዳልከው ከበላይ አለቃ ከጠላትም ሆነ ከወዳጅ፣ ጠቃሚ ነገር ለማግኘት፣ ጠቃሚ የሆነ አገልግሎት መስጠት አስፈላጊነቱ አይካድም:: ትልቁ ቁም ነገር አንተ ያገኘኸው ከሰጠኸው የበለጠ ከሆነልህ፣ የበለጠ ትደሰታለህ እንጂ የሚቆጭህ ነገር አይኖርም ..... » አሉኝ::

ፋሽስት ከኢትዮጵያ ተባርሮ ነፃነት ሲመለስ፣ አስፍሐ ወልደሚካኤል ወደ ትውልድ አገራቸው ወደ ኤርትራ አልተመለሱም:: ከልዑል አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋወሰን ጋር ተዋውቀው፣ በመጀመሪያ በጐንደር፣ ቀጥሎ በወሎ፣ ለአራት ዓመታት በጸሐፊነት ተመድበው ሠርተዋል:: ከነፃነት መመለስ በኋላ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ስለ አስፍሐ ችሎታና መልካም ሥራ ብዙ ስምተው ስለነበረ፣ ጥቅምት 9 ቀን 1945 ዓ.ም የትግሬ ዋና ጸሐፊ አድርገው ሾሟቸው:: በዚያን ጊዜ ጠቅላይ ግዛቱን በተጠባባቂነት ለሚያስተዳድሩት ለራስ አበበ አረጋይ ጃንሆይ በላኩት ደብዳቤ፣ «.....አስፍሐ ወልደሚካኤል በተመልካችነቱና በአርጋታው፣ ከዚህ ቀደም በጠላትም ዘመን በሥራው መልካም ሥራ ያስመሰከረ ነው ..... » ብለዋል:: የትግሬ ጠቅላይ ግዛት ዋና ጸሐፊ ሆነው ለሶስት ዓመታት በሠሩበት ጊዜ፣ ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ተዛውረው፣ ለአንድ ዓመት የመንግሥት ንብረት ዋና ዲሬክተር ሲሆኑ፣ ቀጥሎም ለአራት ዓመታት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የክፍል ዋና ዲሬክተር ተብለው ሲመደቡ፣ ትልቁ ሥራቸው፣ የኤርትራና

የኢትዮጵያ አንድነት እንቅስቃሴ ዋና አማካሪና የሥራ አስተባባሪ በመሆን ነበር:: ብዙ ጊዜ ወደ ኤርትራ እየተጓዙ ከማህበረ ፍቅረ ሀገር የአንድነት ድርጅት መሪዎች ጋር በስፋው በመወያየት፣ ለንጉሠ ነገሥቱ እና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ የሚያቀርቧቸው ሀሳቦች በቂም ነገር የተደመጡና የተሠሩባቸው ናቸው::

ታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት፣ ኤርትራ በፌዴሬሲዮን ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል በወሰነ ጊዜ፣ አስፍሐ ወልደሚካኤል ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከአሥመራ በጻፉት ደብዳቤ፣ « ..... የኤርትራ ሕዝብም የን ሁሉ ተጋድሎ ያደረገው ለፍጹም አንድነት እንጂ ለፌዴሬሲዮን አስተዳደር አልነበረም:: ..... ነገር ግን በወገንና በአድልዎ መንፈስ ከሚመራው የዓለም ሸንጎ፣ ከዚህ የተሻለ ፍርድ ማግኘት ካልተቻለ፣ አንድ ቀን ምናልባትም በቅርብ ቀን፣ እዋናው ግባችን እንደምንደርስ ካለን ጽኑ ተስፋ ጋር፣ በክርስቲያናዊ ትዕግሥት ተቀብለነዋል ...... » የሚል አስተያየት ገልጸው ነበር::

በ 1952 ዓ.ም የኤርትራ ፌዴሬሽን አስተዳደር ሲጀመር፣ አስፍሐ ወልደሚካኤል የግርማዊነታቸው ምክትል እንደራሴ ሆነው እንዲሾሙ ያቀረቡ፣ ወይም ሊሆኑ ይገባል ብሎ ያሰበ አንድም ባለሥልጣን አልነበረም:: ለዚህ ደረጃ ከፊታውራሪነት ማዕረግ ጋር የመረጧቸውና የሾሟቸው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ናቸው:: ለኤርትራ ምክትል እንደራሴነት፣ ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ የመረጡት፣ የራስ ኃይሉ ተሰፋማርያምን ልጅ ፊታውራሪ ኪዳነማርያም ኃይሉን ነበር::

ፊታውራሪ አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ ከትውልድ አገራቸው ከኤርትራ ሌላ፣ በጎንደር በሸዋ፣ በወሎ በትግሬ፣ እየተዘዋወሩ የኢትዮጵያን መሠረተ ታሪክ፣ ባሕሉንና ሥርዓቱን ደህና አድርገው ያጠኑ ናቸው:: እንደበታቸው የተፍታታ፣ ብዕራቸው የተስተካከለ ከመሆኑም በላይ፣ ለአርጋታና ለአስተዋይነት በተመቸው መልክም ጠባያቸው፣ ንጉሠ ነገሥቱ ይወዷቸው ነበር:: ለምክትል እንደራሴነት ጃንሆይ ብቻቸውን መርጠው ሲሾሟቸው፣ ያለ ጥርጥር አንድ ቀን፣ የተድላ ባይሩ ወራሽ ሊሆን ይችላል ብለው ሳያስቡ አልቀሩም:: ለሶስት ዓመታት ያህል በቆየው በተድላ ባይሩ የአስተዳደር ዘመን፣ ንጉሠ ነገሥቱ የውስጡን ጉዳይ የተከታተሉትና የሚመስላቸውንም እርምጃ የወሰዱት፣ አብዛኛውን ጊዜ ከታማኛቸው ከአስፍሐ ወልደሚካኤል በሚቀርብላቸው ራፖር መሆኑን የሚያረጋግጡ ብዙ ማስረጃዎች አሉ:: ከተድላ ባይሩ መሰናበት በኋላ፣ የምርጫው ውድድር በሚካሄድበት ጊዜ፣ « ..... በእኛ በኩል አስፍሐ እንዲመረጥ መልካም ፈቃዳችን ብቻ ሳይሆን፣ አጥብቀን የምንፈልገው ነው ..... » ብለው፣ ንጉሠ ነገሥቱ ለእንደራሴያቸው ለቢትወደድ አንዳርጋቸው መሣይ የሰጡት ትእዛዝ፣ በአስፍሐ ላይ ያላቸውን ሙሉ እምነት የሚያረጋግጥ ነው:: አስፍሐም ለስባት ዓመታት፣ የኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ሆነው አስተዳደሩን በመምራት በቆዩበት ዘመን፣ ንጉሠ ነገሥቱ የጣሉባቸውን ዕምነት በትክክል የፈጸሙና ያስደሰቱ ናቸው:: ለብዙ ጊዜ የታገሉበት የኤርትራ ፌዴሬሽን ፈርሶ፣ የፍጹም አንድነቱ ውህደት ከተከናወነ በኋላ፣ ወደ አዲስ አበባ ተዛውረው፣ በመጀመሪያ የፍርድ ሚኒስትር፣ ቀጥሎም የጤና ጥበቃ ሚኒስትር፣ በመጨረሻም የዘውድ ምክር ቤት አባል ሆነው ሠርተዋል::

በደርግ ዘመን፣ አንዳንድ የቀድሞ ባለሥልጣኖች፣ ደርግ ራሱ እስኪታዘባቸው ድረስ ሲቀላምዱና ሲቀልሉ፣ አስፍሐ ወልደሚካኤል ለንጉሠ ነገሥቱ ያላቸውን ታማኝነት አልለወጡም:: በብዕራቸው ለጃንሆይ በሚጽፏቸው

ደብዳቤዎች፣ « ..... የግርማዊነትዎን ውለታ መመለስ የምንችለው፤ እስከለተ ሞታችን ድረስ ታማኝዎችዎ ሆነን ስንገኝ ብቻ ነው ....... » ይሉ ነበር:: በእኔ ዕዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ምርምር፣ ቢትወደድ፣ እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ፣ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ታማኝነታቸውን፤ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ አንድነት የጠነከረ ዕምነታቸውን የጠበቁ፤ ታላቅ ሰው ናቸው::

# ዳግማይ መራሕ መንግሥቲ

የፍልሰታ ጾም በተጀመረ ማግሥት ነሐሴ (August) 8 ቀን 1955 ዓ.ም፣ አስፍሐ ወልደሚካኤል የኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ሆነው መመረጣቸው በድሬደዋ የሠላም አዳራሽ ቤተመንግሥት በተሰማ ጊዜ፣ ንጉሠ ነገሥቱ በጣም ደስ አላቸው:: አጠገባቸው የነበሩት የሐረር ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ኮሎኔል ክፍሌ እርገቱ (ኋላ ደጃዝማች) ሲናገሩ፣ በዚያን ቀን በጃንሆይ ላይ የታየው የደስታ ስሜት የመረብን ወሰን ካቋረጡበት ዕለት የበለጠ ነበር ብለዋል::

የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሣይ የላኩት ቴሌግራም፤ « ..... የግርማዊነትዎ መልካም ፈቃድ የሆነበት የፊታውራሪ አስፍሐ ምርጫ በአርባ ስምንት ድምፅ ድጋፍ መከናወኑን በታላቅ ትህትና እገልጻለሁ ...... » በሚል ቃል ብቻ ሲወሰን፣ ተመራጩ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ያስተላለፉት መልዕክት የጃንሆይን ስሜት እጅግ የሚነካ ሆነ:: « ...... ለዚህ ከፍተኛ ኃላፊነት ያስመረጠኝ ምን ይሆን ? ቢባል፤ የግርማዊነትዎ ታማኝ አገልጋይ ከመሆኔና ከፍጹም ኢትዮጵያዊነቴ በስተቀር፣ ሌላ ሞያ እንደሌለኝ የታወቀ ነው ...... » ሲሉ ፊታውራሪ አስፍሐ የጋለ ደስታቸውን ከልብ ለሚወዷቸው ንጉሠ ነገሥት ገለጡ::

የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል እንደሚባለው፤ የአስፍሐ የስሜት አገላለጽና አቀራረብ፣ ጃንሆይ የሚጥሉባቸውን ዕምነት የበለጠ የሚያጠነክረው ሆነ:: ፊታውራሪ፣ የኤርትራን መንግሥት መሪነት ሲረከቡ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ምክትል እንደራሴነታቸውን ይዘው እንዲቀጥሉ የጃንሆይ መልካም ፈቃድ ስለሆነ፣ ሥልጣናቸው ከተድላ ባይሩ የተሻለና የተመቻቸ ሆነላቸው:: « ዳግማይ መራህ መንግሥቲ » (ዳግማዊ የመንግሥት መሪ) ተብለው በሕገ መንግሥቱ መሠረት ሥርዓተ መሐላቸውን ሲፈጽሙ፣ ለኤርትራ ከአስፍሐ በኋላ ሌላ፤ « ሳልሳይ መራህ መንግሥቲ » (ሳልሳዊ የመንግሥት መሪ) እንደማይኖር እርግጠኛ ነበሩ:: ሹመታቸው በተመረቀበት ዕለት ለፓርላማው ያደረጉት ንግግር፣ የአዲሱ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ዓላማና ግብ ምን መሆኑን በግልጽ የሚያበስር እንደነበረ ይታያል::

« ...... ኤርትራ ከሌሎቹ የኢትዮጵያ አውራጃዎች የተለየ አስተዳደር ኣላት ቢባልም፣ ከኢትዮጵያ ቤተሰብነት የተለየች አለመሆንዋን መዘንጋት የለብንም:: ...... እኛ ኤርትራውያን በንጉሠ ነገሥታችን በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ልብ ውስጥ፣ የተሰጠንን የመወደድ ደረጃ አጥብቀን መያዝ አለብን:: ...... ለኤርትራና ለኤርትራውያን የሚጠቅመውን ሁሉ፣ በእኝህ በተቀደሱ አባት ንጉሠ ነገሥታችን እጅ ብናስቀምጠው እንጂ፣ እያንዳንዳችን ተነስተን ይህን እንሠራለን፣ ይህን እናደርጋለን ብንል ጥቅማችንን አለማወቅ ይሆንብናል ...... »

ከዚህ በላይ የተመለከተው የአዲሱ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ አስተያየት፣ ኤርትራ በምንም ረገድ ከኢትዮጵያ ቤተሰብነት የማትለይ መሆንዋንና የአገሪቱም ቀወደፊት ዕድል በንጉሡ ነገሥቱ ብቻ እንዲወሰን አጥብቆ የሚያሳስብ ነው:: ከዚህም አልፎ የአስፍሐ መንግሥት የመነሻ ዓላማውና የመጨረሻ ግቡ፣ የኤርትራን ፌዴሬሽን ስርዞ አስተዳደሩን ከኢትዮጵያ ጋር ለማዋሀድ መሆኑን በግልጽ ያመለክታል:: ይህ ካቢኔ፣ በምን አኳኋን ከአሰበው ግብ ለመድረስ እንደጣረ፣ በጉዞው ላይ ያጋጠመውን ልዩ ልዩ ፕሮብሌም እንዴት አድርጐ ለመፍታት እንደሞከረና፣ ምንስ ያህል ጊዜ እንደፈጀ ወደፊት እናያለን::

ሌላው በአስፍሐ የሥልጣን ምረቃ ዲስኩር ውስጥ እጅግ አስደናቂና የማይጠበቅ ሆኖ የተገኘው፣ ስለቀድሞው የኤርትራ መሪ ስለ ደጃዝማች ተድላ ባይሩ፣ ከአዲሱ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ በረዥሙ የተገለጸው አስተያየት ነው:: የተድላ ባይሩ ባለጋራ እንዳልነበሩና ዛሬም እንዳልሆኑ፣ በሕዝቡ ዘንድ እንዲታወቅላቸው፣ ስለ ቀድሞው ቺፍ ኤግዜኩቲፍ አስፍሐ ያደረጉት ዲስኩር፣ እጅግ ከፍ ያለውን አክብሮታቸውንና ፍቅራቸውን እንዲገልጽላቸው ሞክረዋል::

ተድላ ወንድሜ ! ..... የአምላክ ፈቃዱ ሆኖ ወንድም በወንድሙ መተካት ስለአስፈለገ፣ በኤርትራ ሕዝብ መልዕክተኞች ተመርጬ፣ የተከበሩትንና እጅግ የማፈቅራቸውን ወንድሜን ደጃዝማች ተድላ ባይሩን ለመተካት እዚህ እገኛለሁ:: ...... ደጃዝማች ተድላ የማፈቅራቸው ወንድሜ ናቸው ብዬ ስናገር፣ በዚች ሰዓት ላይ የሚነፍሰውን ወሬ በማሰብ ከእናንተ ማህል የሚገረም መኖሩ የታወቀ ነው:: ነገር ግን የማፈቅራቸው ወንድሜ ናቸው ስል፣ በእውነት ወንድሜ መሆናቸውን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ:: ......

...... በዚያ ጨለማ በሆነው በትግሉ ዘመን፣ እንደ አንድ እናት ልጆች ፍጹም በሆነ ወንድማማችነት፤ በሁለት አካል ውስጥ አንድ ትንፋሽ የነበረን ነን:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የነበረኝን ባልንጀራነትና ዕምነት፣ ምንጊዜም ሳጐድለው አልፈልግም:: ...... ወንድሜ ደጃዝማች ተድላ በእውነትና ከልብ በመነጨ አስተሳሰብ፣ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ አንድነት የተሰጡ፣ በሚያስደንቅና በሚያኮራ መልክ እስከ መጨረሻው የታገሉ ናቸው:: ደጃዝማች ተድላ የአንድነት ማህበራችን መሪ ሆነው በሚጥሩበት ዘመን፣ ንፁህ ሀሳባቸውንና የቆሙበትን ዓላማ ለማወናበድ፣ ከግራም ከቀኝም የሚሞክራቸው አልጠፉም ነበር:: ...... ደጃዝማች ተድላ ግን ምንም ሳይዛነፉ፣ ከጠዋቱ ላመኑበት ለኢትዮጵያና ለኤርትራ አንድነት፣ ከአገር ፍቅር ማህበር የተጣለባቸውን አደራ በትክክል መፈጸማቸውን በአድናቆት የሚመሰክርላቸው እንጂ፣ የሚክዳቸው ከቶ አለ እልልም:: ...... ወንድሜ ደጃዝማች ከዚያ ከታላቁ ትግል በኋላ፣ ኤርትራን ባስተዳደሩበት ዘመን፣ በተለይ ስለ አንድ ትልቅ ጉዳይ የፈጸሙትን ሳልጠቅስ ማለፍ አልፈልግም:: ደጃዝማች ተድላ፣ በኤርትራ አውራጃዎች መካከል ምንም ዓይነት የአስተዳደር ልዩነት እንዳይኖር፣ ያሳዩትን እቋም ከልቤ አደንቃለሁ:: ...... መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እኔ ኦሪትንና ነቢያትን ፍጹም ለማድረግ እንጂ ልሽራቸው አልመጣሁም እንዳለው ሁሉ፣ በዚህ ረገድ እኔም የወንድሜን የደጃዝማች ተድላን እምነት የምከተል መሆኔን ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ ....... » ብለው ንግግራቸውን ፈጸሙ::

የዚህ ዓለም የፖለቲካ ሕይወት ከመንፈሳዊና ከሰብዓዊ ተግባር ምን ያህል የተለየ መሆኑን መረዳት የሚቻለው ይህን በመሳሰለው ታሪክ ነው:: አስፍሐ

ወልደሚካኤል በወጣትነታቸው ዘመን በቃፊሙት ኤክስፔሪያንስ ብቻ ሳይሆን፣ በተፈጥሮአቸውም ብልህ የሆኑ የፖለቲካ ሰው ናቸው:: ተድላ ባይሩን « የማፈቅራቸው ወንድሜ አካሌ » እያሉ በማቃበጥ ካደረጉት የፖለቲካ ዲስኩር ውጪ፣ የቀድሞው ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ አንድነት ስለአደረጉት ተጋድሎ የተናገሩት፤ ትክክል መሆኑ አይካድም:: ሆኖም አስፍሐ እንዳሉት፣ ወንድም በወንድሙ የተተካው፣ በተዓምርና በመለኮት ፈቃድ ሳይሆን፣ ወንድም በወንድሙ ተፈንቅሎ መሆኑ ሳይገለጽ ተደብቆ መኖር አይችልም:: ደጃዝማች ተድላ፤ የፌዴሬሽኑን ማፍረስ ጉዳይ ችላ እያሉ፣ አቶኖሚውን ለማጠንከር ስለፈለጉ፣ ከሥልጣናቸው ሰቅሰቀው ካብረሯቸው ወገኖች፣ ዋናው መሪ አስፍሐ ወልደሚካኤል መሆናቸውን ራሳቸው አስፍሐም አልካዱም::

በግንቦት 1987 ዓ.ም ቢትወደድ አስፍሐ ሮም መጥተው እኔ ዘንድ በሰነበቱበት ጊዜ፣ ከደጃዝማች ተድላ ባይሩ ጋር ስለነበራቸው አለመግባባት የነገሩኝን አስታውሳለሁ:: « ..... ስለ አገር ጉዳይ የሀሳብ መለያየት ሲፈጠር፣ እንኳንስ ወዳጅ ወንድም ከሚባል ሰው ይቅርና፣ ከወለዱትም ልጅ ጋር የፖለቲካ ባለጋራነትን መፍጠሩ የማይቀር ነው:: እኔ የወዳጄ ወንድሜ ተድላን ፌዴራሊስትነት መቃወሜንና፤ በዚህም ምክንያት ከሥልጣን እንዲወርዱ የበኩሌን እርዳታ ማበርከቴን አልክድም:: በሠራሁትም አልፀፀትም:: ወንድሜ ተድላ በተንኮለኞች ምክር ተመርዘው፣ ኤርትራን ከኢትዮጵያ አስተዳደር የተለየች ለማድረግ በተነሱ ጊዜ፣ « ..... እባክዎ ? ያ ሁሉ የሚያምረው ታሪክዎ ከኢትዮጵያዊት ኤርትራ ጋር ተዋቅሮ ለዘለዓለሙ እንዲኖር አድርጉ ..... » ብዬ ለምኛቸው ነበር:: ምን ይሆናል ? አልሰሙኝም:: ...... እኔ ለአገር ጉዳይ ብዬ የሠራሁትንና እሳቸውንም የተቃወምኩበትን አልደብቅም:: እሳቸው ግን እኔን ከምክትል እንደራሴነት እንድሻር፣ በወዳጃቸው በጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ በኩል ያደረጉትን ሙከራ እና፣ ለጃንሆይም ማመልከታቸውን ይክዱ ነበር ...... » ብለዋል::

የፖለቲካ ሰው የሆኑት አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ በሥልጣን ምረቃ ዲስኩራቸው ላይ ባለጋራቸውን ደጃዝማች ተድላን ብቻ ሳይሆን፣ እንዳይመረጡ ተቃውመዋቸው የነበሩትን ቢትወደድ አንዳርጋቸውንም አሞግሰዋል:: «..... የታላቁ መሪያችን የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሀሳብ ገላጭ ሆነው፣ ወገንና ሀይማኖት ሳንለይ፣ በኢትዮጵያዊ መንፈስ እንድንጣመር ሌት ተቀን ለሚደክሙት ለክቡር ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሣይ የጠለቀ ምሥጋናችንን ምክር ቤቱ እንዲገልጽልን እጠይቃለሁ:: ...... » ብለው ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ያቀረቡትን ሀሳብ ፓርላማው ድጋፉን በጭብጨባ አሰማላቸው:: ይህ አነጋገር የአስፍሐ ልባዊ አስተሳሰብ ሳይሆን ፖለቲካዊ አቀራረብ መሆኑን ያልተረዳ የለም::

## የመጀመሪያው ዓመት

1955 - 1956

ፊታውራሪ አስፍሐ የኤርትራን መንግሥት ሥልጣን እንደተረከቡ፣ የካቢኔ አባሎቻቸውን ቁጥር፣ በተድላ ጊዜ ከነበረው ከአምስት ወደ ስድስት ከፍ አድርገው፤ የሥራውን መደብ ለሶስት ክርስቲያኖችና ለሶስት እስላሞች እኩል

**በማከፋፈላቸው፣** በፓርላማውና በየአውራጃው ያሉትን የፖለቲካ ታዛቢዎች **አስደስተዋል።** በተጨማሪም የቺፍ ኤግዜኩቲፉ ሥልጣን፣ በሕዝብ ፊት የጉላ **መስሉ** እንዳይታይ፣ በሚዘዋወሩባቸው ቦታዎች ሁሉ የፕሮቶኮል ግርግር እንዳይበዛ፣ በአውቶሞቢላቸው ላይ ስንደቅ ዓላማ እንዳይውለበለብ፣ ቢሮአቸውም ለባለ ጉዳይ ዝግ እንዳይሆን በማድረጋቸው፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ አድናቆትንና ተወዳጅነትን አስገኝቶላቸዋል።

አዲስ አበባ ለሥራ ጉዳይ ሲሄዱ፣ ለደጃዝማች ተድላ ይደረግ እንደነበረው በአውሮፕላን ጣቢያ የፕሮቶኮል አቀባበል እንዲደረግላቸው፣ ከቤተመንግሥቱ ካዲላክ እንዲላክላቸው፣ ሳሎን ያለው የማረፊያ ሆቴል እንዲዘጋጅላቸው፣ የፀጥታ መኰንን ኮርጆአቸውን እየያዘ እንዲጠብቃቸው አልፈልግም አሉ። የቤተመንግሥቱ ባለሟል፣ የሚኒስትሮቹ ወዳጅ፣ የአዲስ አበባ ቤተኛ በመሆናቸው፣ የእንግድነት መልክ አይታይባቸውም ነበር። በደጃዝማች ተድላ ባይሩ ዘመን፣ በፖለቲካም ሆነ በአስተዳደር ረገድ ቅሬታ የፈጠሩትን ጉዳዮችና፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉንም ከሥልጣን እስከ ማስለቀቅ ያደረሱትን ምክንያቶች፣ አስፍሐ ደህና አድርገው ስለሚያውቁ፣ በአዲሱ አመራር ብዙ ነገሮችን ለማሻሻልና የተለየ መልክ ለመስጠት አልተቸገሩም።

ንጉሠ ነገሥቱ ከተድላ ባይሩ ጠብቀው ያጡትን እንዲያገኙ፣ ፓርላማው በተድላ አመራር የጐደለበት እንዲሟላለት፣ የተቃዋሚው ወገን ሕገ መንግሥቱ የሚሰጠው መብት እንዲከበርለት፣ አስፍሐ ወልደሚካኤል የሚወስዷቸው እርምጃዎች ሁሉ፣ በሁሉም ዘንድ ሙሉ ተስፋ የሚያሳድሩ ሆኑ። በፓርላማውና በኤግዜኩቲፉ ሥልጣን መካከል መቀራረብንና መተማመንን በጥቂት ቀናት ውስጥ ከመሠረቱ በኋላ፣ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ በአስቸኳይ የሚያስፈልጓቸውን ሁሉ ማግኘት ጀመሩ።

መስከረም 24 ቀን 1955 ዓ.ም ሥልጣን በተረከቡ በአንድ ወር ተኩል ጊዜ ውስጥ፣ የተድላ ባይሩ የቅርብ ወዳጅና ዋና ደጋፊ ሆነው የኖሩት፣ የፓርላማው ምክትል ፕሬዚዳንት ብላታ ደምሣስ ወልደሚካኤል ተሽረው፣ <u>መላከ ሠላም ዲሚጥሮስ ገ/ማርያም</u> እንዲሾሙ አስደረጉ። ብላታ ደምሣስ ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው እንዲለቁ የቀረበላቸውን ሀሳብ አለቀበልም በማለታቸው፣ ፓርላማው በድምፅ ብልጫ እንዲወስን ሲጠየቅ፣ ከተቃዋሚ በስተቀር አንድም ደጋፊ ሳያገኙ ቀሩ። በምትካቸው የ<u>ታወቁት መላከ ሠላም ዲሚጥሮስ ግን፣ አንድም ተቃዋሚ ሳይቀርባቸው</u> በሙሉ የድጋፍ ድምፅ የፓርላማው ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ተመረጡ።

መላከ ሠላም ዲሚጥሮስ ገብረማርያም፣ ዕድሜያቸውን ሙሉ ለኢትዮጵያዊት ኤርትራ ያደረጉት ተጋድሎ ወሰን የሌለው ነው። <u>ዲሚጥሮስ ዘንድ፣ « ኢትዮጵያ ወይ ሞት » የተባለው የአንድነቶች መመሪያ ዓላማ፣ ቃሉ በግልጽ ከሚያስረዳው ውጭ የተለየ ትርጉም አልነበረውም።</u> በዚያ በትግሉ ዘመን፣ « ..... ኤርትራ ያለ እናቷ ያለ ኢትዮጵያ ሕይወት አይኖራትም። ከእናት አገር ተለይተን የኖርን እና በባዕድ አገዛዝ ሥቃይ የተቀበልን ሁሉ፣ ለኢትዮጵያዊት ኤርትራ ብንሞት፣ ሞታችን ጽድቅ እንጂ ኩነኔ የለውም ...... » እያሉ ወገኖቻቸውን ለማንቃትና ለማዘጋጀት የፈጸሙት ድካም ባጭሩ ተወስቶ የሚያልቅ አይደለም። የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን በ1950 ዓ.ም ኤርትራ መጥቶ በከረመበት ጊዜ፣ « ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀላቀል የማይቻል ከሆነ፣ ሌላው

ምርጫችሁ ምንድን ነው ? ...... » የሚል ጥያቄ ከፓኪስታኑ ወኪል ሲቀርብላቸው፣ መላከ ሠላም ዲሚጥሮስ የሰጡት መልስ ጠያቂውን አስደንግጦት ነበር:: « በእኛ በኩል ኢትዮጵያ ወይ ሞት ብለናችኋል:: በሥልጣናችሁ ኢትዮጵያዊ መሆንን ትከለክሉን ይሆናል:: ሞትን ግን ልትከለክሉን አትችሉም:: ስለዚህ፣ ሁለተኛው ምርጫችንን ለእኛ ተዉልን:: እናንተን አይመለከትም » ብለው፤ በቆረጠ መንፈስ በመናገራቸው፣ የኢትዮጵያ ጠላት የሆነው የፓኪስታኑ ወኪል ተጨማሪ ጥያቄ ለማቅረብ አልሞከረም:: እኝህ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ለአንድነት ያደረጉት ትግል ራሱን የቻለ መጽሐፍ የሚያስፈልገው ስለሆነ፣ በየአጋጣሚው አንዳንዱን ሁኔታ ለመጥቀስ ካልሆነ በስተቀር፣ ታሪኩን በሙሉ ለመዘርዘር አይቻልም:: ወደ መነሻ ጉዳዩ እንመለስና፣ የመላከሠላም ዲሚጥሮስ የፓርላማው ምክትል ፕሬዚዳንት ሆኖ መመረጥ፣ ለአንድነቶች ብቻ ሳይሆን፤ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ለመንግሥታቸውም ከፍ ያለ ደስታ ሰጥቶ ነበር:: አንግዲህ አስፍሐ ብቻውን አይደለም:: በኢትዮጵያና በኤርትራ ሕዝቦች መካከል አንድነት በይበልጥ እንዳይተሳሰር፤ እስካሁን ደንቃራ ሆኖ ያስቸገረውን የፌዴሬሽን ሕገ መንግሥት በቶሎ ለማጥፋት፤ በፓርላማው ለመላከሠላም የተሰጠው ሥልጣን ወሳኝ ነው ተብሎ ከፍ ያለ ዕምነት ተደረገ::

የአስፍሐ ካቢኔ ሥራውን ከጀመረ ከሁለት ወር በኋላ፣ ለጥቅምት ጊዮርጊስ (2/11/55) ለሚከበረው የንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የብር ኢዮቤልዩ የዘውድ በዓል፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ የአስተዳደር ውህደት ሊፈጸም ይችላል ብለው በጣም የተጣደፉ፤ ጥቂቶች የአንድነት ወገኖች ተንቀሳቅሰው ነበር:: ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም በዚህ በኢዮቤልዩ የዘውድ በዓላቸው አዲስ ሕገ መንግሥት የሚያውጁበት ጊዜ ስለሆነ፤ ኢትዮጵያዊት ኤርትራም የፌዴሬሽን ልብሷን ጥላ፣ የታላቋ ኢትዮጵያ ዕድል ተካፋይ ብትሆንላቸው፣ መልካም ፈቃዳቸው ብቻ ሳይሆን፣ ታላቅ ደስታም እንደሚሰጣቸው ጥርጥር አልነበረውም:: ነገር ግን በሩቅ በቀላል የገመቱት፣ ሲቀርቡት ይከብዳል እንደሚባለው ሁሉ፣ « መንግሥቲ አስፍሐ » በሩቅ የገመተውን በቅርብ ሲመዝነው፣ የኤርትራን ፌዴሬሽን ለማፍረስ ከፍ ያለ ዝግጅትና ረዥም ጊዜ እንደሚጠይቀው ተገነዘበ:: ጉዳዩ በጥልቅ ሲመረመር፤ እንኳንስ ከሁለት ወር በኋላ ለሚከበረው የዘውድ ኢዮቤልዩ ቀርቶ፤ ከሁለት ዓመት በኋላም ለሚደረገው በዓል ለማድረስ እርግጠኛ መሆን እንደማይቻል ተገመተ:: ስለዚህ፣ የአስፍሐ መንግሥት ከጠዋቱ አስቦት የነበረውን ትልቅ ጉዳይ በቶሎ ለመፈጸም የማይችልበትን ምክንያት፣ ለአንድነት ወገኖቹ ከፍ ባለ ምሥጢር አብራርቶ ማስረዳት አስፈለገው::

1.- « ...... ነሐሴ 8 ቀን 1955 ዓ.ም ፊታውራሪ አስፍሐ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ሆነው የተመረጡትን፤ የተድላ ባይሩን የአንድ ዓመት የሥልጣን ዘመን ለመፈጸም ነው::

2.- ይህ አንድ ዓመት ከማለቁ በፊት፣ የፓርላማው የሁለተኛው ተርም ጠቅላላ ምርጫ መዘጋጀትና መከናወን አለበት::

3.- ይህ በጊዜያዊነት ለአንድ ዓመት ተመርጦ የተቋቋመው መንግሥት፣ የኤርትራን አስተዳደር ከኢትዮጵያ ጋር ለማዋሀድ፣ ከጊዜው ማጠር የተነሣ የማይቻለው ሆኗል:: ይህን የታሰበውን መሠረታዊ ዓላማ ያለ ችግር ከግቡ ለማድረስ እንዲቻል፣ ለሁለተኛው ጠቅላላ የፓርላማ ምርጫ

ተመጓጓሪዎች የሚሆኑት የአንድነት ወገኖች፣ በብዛት ወንበር እንዲያገኙ ከአሁኑ በብርቱ መዘጋጀትና መደራጀት ያስፈልጋል::

4.- ይህ እስከሚፈጸምበት ጊዜ ድረስ፣ የአስፍሐ መንግሥት ፌዴሬሽኑን በአሠራር ዘዴ አያዳከመ፣ ከኢትዮጵያ ጋር ለሚደረገው የአስተዳደር ውህደት፣ ግንባር ቀደም በሆኑት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ፣ በየመልካቸው አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ወስኗል:: .... »

እንግዲህ ይህ በምሥጢር የተሰራጨው ማብራሪያ እንደሚያስረዳው፣ በ1953 ዓ.ም ደጃዝማች ተድላ ባይሩ « ...... ኢትዮጵያዊነቴን በይፋ እያረጋገጥኩ፣ የኤርትራን ሕገ መንግሥት በተግባር አጠናክረዋለሁ ..... » ብለው እንደፎከሩት ሁሉ፣ በ1955 ዓ.ም ደግሞ፣ ፊታውራሪ አስፍሐም ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ ምቹ ጊዜ እስካገኝ፣ ሕጉን በአሠራር እያዳከምኩ አንድነቱን በተግባር አራምዳለሁ የሚል አቋም፤ ለወገኖቻቸው ማሳየት ግዴታ ሆኖባቸዋል ማለት ነው::

አስፍሐ ወልደሚካኤል ሀሳባቸውን አፍታተው እና አጣፍጠው ለማስረዳት፤ የተለየ ስጦታ ስላላቸው፣ በአሁኑ ሰዓት ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ፓርላማውን መጠ የቅ፣ ለሞት የሚያጣጥረውን ጠላት፣ ነፍስ እንዲዘራ መቀስቀስ ይሆንብናል ብለው፣ ያቀረቡትን ምክንያት፣ የአንድነት ወገኖች በጥሩ መንፈስ ተቀበሉላቸው:: ንጉሠ ነገሥቱም አይዞህ በርታ ከማለት በስተቀር፤ በዝርዝር ፕላናቸው ውስጥ ገብተው ጥያቄ አላከታተሉባቸውም:: ሆኖም ትልቁን ጉዳይ ለጊዜው በቀጥታ አለመንካት ይሻላል ቢባልም፣ ፊታውራሪ እንዳቀረቡት ሀሳብ፣ ከኢትዮጵያ ጋር አስተዳደሩን ለማዋሀድ የሚያስችሉትን ግንባር ቀደም ጉዳዮች ለማከናወን፣ ጊዜ መፍጀት አያስፈልግም ሲሉ አንድነቶች አስጠንቅቀዋል::

በአንድነት አጥባቂነታቸው እጅግ በታወቁት በደጃዝማች ገብረዮሐንስ ተስፋማርያም የአስፍሐ ካቢኔ የኢኮኖሚ ሴክሬተሪ መሪነት፣ አሥር የምክር ቤቱ የአንድነት ወገኖች ተሰብስበው ለአስተዳደሩ ፍጹም ውህደት ዋና ዋና ተቀዳሚ ቁም ነገሮች ናቸው የሚሏቸውን አራት ጉዳዮች አጥንተው አቀረቡ::

1. አማርኛ ከትግርኛ ቀጥሎ የኦፊሴል ቋንቋ እንዲሆን፣

2. የኤርትራ ባንዲራ ተሰርዞ፤ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ብቻ እንዲሆን፣

3. ለኤርትራ የተለየ ማህተም ቀርቶ ታላቁ የኢትዮጵያ ማህተም ብቻ እንዲሠራበት፣

4. የኤርትራን ቺፍ ኤግዜኩቲፍ፣ በየተራ አንድ ጊዜ ከክርስቲያኖች ማህል፤ በሚቀጥለው ጊዜ ከእስላሞች ወገን፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እየመረጡ እንዲሾሙ፤

የሚል ሀሳብ ነበር::

እነዚህን አራት ዋና ዋና ጉዳዮች ፓርላማው በፍጥነት ካጸደቃቸው በኋላ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ሀያ አምስተኛ የዘውድ ኢዮቤልዩ በዓል ቀርበው፣ ኢትዮጵያዊት

ስለሆነና፣ አሁንም በዚሁ ለመቀጠል መፈለጉን ስለአስመሰከረ፣ ፊታውራሪ አስፍሐ መጀመሪያ እንዳስመረጡት ሁሉ፣ ዛሬም መልሰው ከሥልጣን ለማውረድ ልዩ ጥረት ማድረግ አስፈላጊያቸው ሆነ። ኢድሪስን ከሥልጣን ለማውረድ የሚችለው ፓርላማው ስለሆነ፣ የመማክርቶቹን ድጋፍ ለማግኘት የአስፍሐ ሀሣብ የሚከተለው ነበር።

« ...... ከሰኔ እስከ ሐምሌ 1955 ዓ.ም ድረስ ደጃዝማች ተድላ ፓርላማውን አከታትለው ለአርባ ቀናት በዘጉበት ጊዜ፣ በምክር ቤቱ ገበታ ላይ የተከመሩት ሥራዎች ምን ያህል አሳሳቢ እንደነበሩ ሁላችንም እናስታውሳለን። በዚያን ጊዜ ከሥልጣን በተነሱት በዓሊ ራዳይ ቦታ በጨዋነቱና በችሎታው የታወቀ ሰው፣ በእርጋታ ተፈልጐ እስኪመረጥ ድረስ፣ ኢድሪስ መሐመድ አዱም ለጊዜው ፕሬዚዳንት ሆኖ እንዲመደብ መደረጉን ሁላችንም እናስታውሳለን። አሁን ፈጣሪ ይመሥገን ፓርላማችን ያንን ሁሉ ችግር አሳልፎ ኃላፊነቱንና ተግባሩን ለመፈጸም ሙሉ ሁላም አግኝቷል። ስለዚህ፣ ለፓርላማችን በጠባዩና በምግባሩ፣ በችሎታውና በአቋሙ፣ የተከበረ ፕሬዚዳንት መርጦ መሾም የሚያስፈልግበት ጊዜ ነው። በበኩሌ፣ በቆላው ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ግምት የተሰጣቸውን፣ እኛም በጨዋነታቸውና በአዋቂነታቸው የምናከብራቸውን፣ ሼህ ሐሚድ ፈረጅ ሐሚድን ፓርላማችን በሙሉ ድምፅ እንዲመርጣቸው እጠይቃለሁ ...... » ብለው፣ ፊታውራሪ አስፍሐ ያቀረቡት ሀሳብ ብዙዎቹን የፓርላማ አባሎች የሚማርክ ሆነ። ሼህ ኢድሪስ ደግሞ በበኩሉ ፊታውራሪ የሚጠነስሱለትን ሳይሰማ፣ በፕሬዚዳንትነት ለመቆየት ይረዳኛል በማለት፣ ከራቢጣዎች ጋር ውስጥ ውስጡን ሲወሳልት ሰነበተ። በሰኔ 1956 ዓ.ም በሀርጊጐ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ትምህርት ቤት ሲመረቅ፣ እንደራሴውና ቺፍ ኤግዜኩቲፉ፣ የፓርላማው አባሎችና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች በተካፈሉበት በዓል ላይ፣ ጥቂቶች የራቢጣዎች ወገኖች ነን የሚሉ፣ « ኢድሪስን እንደግፋለን » የሚል ሠሌዳ ለጥፈው ሲዘዋወሩ ታዩ። ይህንን በሥፍራው ተገኝተው የተመለከቱት የፓርላማ አባሎች በጣም ተናደው ስለነበረ፣ አሥመራ እንደተመለሱ ኢድሪስን ሽረው፣ አስፍሐ እንደጠቆሙት ከዓሊ ራዳይ ወገኖች አንዱ የሆኑትን፣ ሼህ ሐሚድ ፈረጅ ሐሚድን ለፕሬዚዳንትነት መረጡ።

ደጃዝማች ተድላ በሥልጣን በነበሩበት ዘመን በፓርላማው ውስጥ የተመኩባቸውና ያመኗቸው፣ ፕሬዚዳንቱን ዓሊ ራዳይን እና ምክትል ፕሬዚዳንቱን ብላታ ደምሳስ ወልደሚካኤልን እንደነበረ ይታወሳል። እንደዚሁም፣ ፊታውራሪ አስፍሐ በብላታ ደምሳስ ቦታ ከተመረጡት፣ ከመላከሠላም ዲሚጥሮስ ጋር እንደ ወንድማማች የሚፈቃቀሩ ሲሆን፤ በራቢጣው ኢድሪስ ቦታ የተተኩት ሼህ ሐሚድም የቅርብ ወዳጃቸው ስለሆኑ፣ የሚተማመኑባቸው ደጋፊዎች አግኝተዋል።

የተድላ ባይሩን የአንድ ዓመት የሥልጣን ዘመን ለመፈጸም የተመረጡት ፊታውራሪ አስፍሐ፣ እንደተመኙትና ብዙም ሰዎች እንደጠበቁት፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ፌዴሬሽኑን አፍርሰው ኤርትራን በጃንሆይ አስተዳደር ለማዋሀድ የሚቻል ባለመሆኑ ቅር ብሏቸዋል። ቀጥሎም ምንም እንኳን የታሰበውን ሙሉ በሙሉ ለመፈጸም ባይቻል፣ በዓረብኛ ቦታ አማርኛን አፊሴል ቋንቋ ለማድረግ፣ የኤርትራን ባንዲራ በኢትዮጵያ ለመለወጥና ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ጃንሆይ እንዲሾሙ፣ በነ ደጃች ገብረዮሐንስ ተቻኩሎ የቀረበው ሀሳብ እክል ስለገጠመው፣ ፊታውራሪ አልተደሰቱም። ሆኖም ይህ የአንድ ዓመት ሥልጣን ቁም ነገር ያለው ታሪክ ሳይፈጸምበት ሊያልፍ አይገባም በማለት፣ የቀረው ቢቀር የኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ በፓርላማ በመመረጥ ፋንታ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እንዲሾም፣

የተባለውን ሀሳብ እንደገና አድሶ ለማስፈጸም፣ በሚያዝያ 1956 ዓ.ም አስፍሐ ወልደሚካኤል ቆርጠው ተነሱ:: ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የኤርትራን ቺፍ ኤግዜኩቲፍ እየመረጡ እንዲሾሙ የምክር ቤቱን አባሎች ለማስማማት ከፊታውራሪ የቀረበው ሀሳብ በሚከተለው መልክ ነበር::

1- ንጉሠ ነገሥቱ የኤርትራን ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ከፓርላማው አባሎች መካከል ለአንድ ተርም ክርስቲያን፣ ለሚቀጥለው ተርም እስላም እየመረጡ ይሾማሉ::

2- ንጉሠ ነገሥቱ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ አድርገው የሚሾሙት፣ ተራው የክርስቲያን በሚሆንበት ጊዜ፣በመማክርቶቹ የሚመረጠው የፓርላማው ፕሬዚዳንት እስላም ይሆናል:: እንደዚሁም የሚሾመው ቺፍ ኤግዜኩቲፍ እስላም ሲሆን፣ የፓርላማው ፕሬዚዳንት ከክርስቲያን ወገን ይመረጣል::

3- ለቺፍ ኤግዜኩቲፉ ምክትል እንዲሆን የሚመደበውና፣ ለፓርላማው ምክትል ፕሬዚዳንትነት የሚመረጠው፣ ለዋናዎቹ ቦታዎች በሚደረገው አኳኋን ይከናወናል:: ይህም ማለት በሌላ አነጋገር፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ እስላም ሲሆን፣ ምክትሉ ክርስቲያን፣ የፓርላማው ፕሬዚዳንት ክርስቲያን ከሆነ፣ ምክትሉ እስላም፣ ይሆናል ማለት ነው::

4- በንጉሠ ነገሥቱ የሚሾመው ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ቀጥታ ኃላፊነቱ፣ ለፓርላማውና ለንጉሠ ነገሥቱ ስለሆነ፣ <u>በኤርትራ የዘውድ እንደራሴ እየተባለ የሚሾመው ይሰረዛል::</u>

5- ይህ ዓይነቱ አሠራር በተግባር ላይ ከዋለ፣ ለመላው የኤርትራ ሕዝብ እንድነትንና ፍቅርን፣ በሀይማኖት መከባበርንና መተማመንን የሚፈጥር ይሆናል:: እስከ ዛሬ ድረስ በቀጠለው አሠራር፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ክርስቲያን፣የፓርላማው ፕሬዚዳንት እስላም እንዲሆን ተከፍሎ መመደቡ፣ የዴሞክራሲ ሥርዓትን አያሟላም ....... ::

ይህ ከዚህ በላይ የተተነተነው የፊታውራሪ አስፍሐ ሀሳብ፣ በምክር ቤቱ ውስጥ ሁለት ሶስተኛውን የድጋፍ ድምፅ እንደሚያገኝ ከተረጋገጠ በኋላ፣ ፓርላማው ውሳኔውን ከማጽደቁ በፊት፣ አንድ የመልዕክተኞች ቡድን (ከክርስቲያኖችና ከእስላሞች የተውጣጣ) ወደ አዲስ አበባ ተልኮ የጃንሆይን መልካም ፈቃድ እንዲጠይቅ ስምምነት ተደረገ:: በዚህ ጊዜ፣ የግርማዊነታቸው እንደራሴ ቢትወደድ አንዳርጌ፤ ጉዳዩ በጣም ከፍተኛ ስለሆነ፣ መልዕክተኞች ከመላክ እኔው ራሴ ለጃንሆይ አቅርቤ ባስፈቅድ ይሻላል ብለው፣ በአስቸኳይ ወደ አዲስ አበባ ሄዱ:: ንጉሠ ነገሥቱም እንደራሴያቸው ይዘው የመጡትን ጉዳይ አይተው ከተደሰቱ በኋላ፤ ራስ አበበ አረጋይ የመከላከያ ሚኒስትር፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ጸሐፊ ትእዛዝ ተፈራወርቅ የጽሕፈት ሚኒስትር፣ አቶ ገብረወልድ እንግዳወርቅ ም/ጸሐፊ ትእዛዝ ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሣይ በአስረጅነት በሚገኙበት ተሰብስበው፣ ጃንሆይ ለጉዳዩ አፈጻጸም የሚሰጡትን ውሳኔ በአስቸኳይ አጥንተው እንዲያቀርቡ አዘዙ::

የመከላከያ ሚኒስትሩ ስብሰባውን ሲከፍቱ፣ « ..... የኤርትራን ጉዳይ ከሁላችን የበለጠ የሚያውቀውና ብዙ የደከመበት አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ በጃንሆይ ሊታዘዝበው ጉዳይ ሀሳብ እንዲሰጠን እጠይቃለሁ ...... » አሉ:: የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩም፣ በአራት ነጥቦች የተከፈሉ አስተያየቶች አቀረቡ::

1. የኤርትራ ፌዴራሲዮን አስተዳደር፣ አሁን ባለው ሕገ መንግሥት እስከቀጠለ ድረስ፣ በምንም ምክንያት ጃንሆይ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ለመሾም አይችሉም::

2. የኤርትራ መንግሥት መሪ የግዴታ በጃንሆይ መሾም አለበት ከተባለ፣ ሕገ መንግሥቱ መሻሻል አለበት::

3. ሕገ መንግሥቱን ለማሻሻል የሚቻለው፣ በመጀመሪያ መሻሻል የሚያስፈልገው ጉዳይ፣ ከፌዴራሉ አክት ጋር የማይጋጭ መሆኑ በሕግ አዋቂዎች ተጠንቶ እንዲረጋገጥ ያስፈልጋል::

4. የሚሾመው ቺፍ ኤግዜኩቲፍ፣ እንደተባለው ክርስቲያንም ሆነ እስላም፣ በፓርላማ ከተመረጠ በኋላ ከሆነ፤ ጃንሆይ ሿሚ መሆናቸው ለወጉ ካልሆነ በስተቀር፤ የተለየ ሥልጣን እንደማይጨምርላቸው መታወቅ አለበት:: ከዚህም በቀር የኤርትራ ፓርላማ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን እየመረጠ ሲያቀርብ ጃንሆይ ሿሚ ከሆኑ፣ በኢትዮጵያም ጠቅላይ ሚኒስትር የሚሆነውን ፓርላማው እየመረጠ ጃንሆይ ሹመቱን ሰጭ እንዲሆኑ ለምን አይደረግም? የሚል ጥያቄ መቅረቡ ስለማይቀር፣ ለመልሱ መዘጋጀት ያስፈልጋል::

5. ፊታውራሪ አስፍሐ ከዚህ ቀደም እንደነገሩኝ፣ የሚሾመው ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ኃላፊነቱ በቀጥታ ለፓርለማውና ለጃንሆይ ስለሚሆን፣ <u>በኤርትራ የንጉሠ ነገሥቱን እንደራሴ መሾም አያስፈልግም:: በዚህ በኩል ብዙ ወጪ ይቀንሳል:: ለሥራውም ቅልጥፍና ይሰጣል::</u> የሚል ሀሳብ ነው:: ይሁን እንጂ አሁን ባለው ሁኔታ ይህን ሀሳብ በሥራ ላይ ለማዋል የኤርትራን ሕገ መንግሥት የሚያናጋና ለጃንሆይም አመራር ምቹ አለመሆኑን ዘርዝሬ ለፊታውራሪ አስፍሐ ነግሬያቸው ነበር:: አሁን እንደገና ይኸው ሀሳብ ከቀረበ በፊተኛው ጊዜ የሰጠሁት አስተያየት አልተደመጠም ማለት ነው:: ...... በእኔ በኩል ክቡር ራስ የጠየቁኝን ለማጠቃለል፤

1ኛ/ የቀረበው ሀሳብ በሥራ ላይ ለማዋል ብዙ የሕግ ችግር ስለአለበት፣

2ኛ/ ይህ ዓይነቱ መሻሻል ለጃንሆይ አመራር ምቹም፣ ጠቃሚም ስለማይሆን፣



" ....... OH ! MON DIEU PROTEGE - MOI DE MES AMIS ....... "

« ...... እባክህ አምላኬ ከወዳጆቼ ሰውረኝ ....... »

አንዳርጋቸው መሣይ
ሚያዝያ 1956 ዓ.ም

3ኛ/ [redacted] ሕገ መንግሥት ሳይነካ መቆየቱ፣ ከአራት ዓመት በኋላ ከጣልያን የሞግዚት አስተዳደር የሚላቀቁትን ሱማሌዎች ከኢትዮጵያ ጋር እንዲሆኑ ይስባቸዋል ብለን ስለምናስብ፣

4ኛ/ በተጨማሪም የኤርትራ ሕገ መንግሥት ተከብሮ እንደሚቆይ፣ ጃንሆይ ለተባበሩት መንግሥታት የሰጡትን ቃል መጠበቅ ግዴታ ስለሚሆን፣

ይህን የቺፍ ኤግዜኩቲፍ አሿሿም ጉዳይ መቀበል አያስፈልግም እላለሁ:: ...... »

ጃንሆይ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን የሚሾሙ ከሆነ፣ <u>በኤርትራ ያለው የግርማዊነታቸው እንደራሴ ቢሮ እንደሚዘጋ፤ ከፌታውራሪ አስፍሐ ሀሳብ መቅረቡን ቢትወደድ እንደርጌ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚሰሙት፣ ከዚህ ካቶ አክሊሉ ንግግር ስለሆነ፣ ከፍ ያለ ድንጋጤና መገረም ደረሰባቸው::</u> በፈረንሣይ የተማሩ በመሆናቸው ወደ አቶ አክሊሉ መለስ ብለው፣ " - OH MON DIEU PROTEGE-MOI DE MES AMIS " <u>« እባክህ አምላኬ ከወዳጆቼ ሰውረኝ »</u> የሚለውን የጥንታዊውን የጀርመን ንጉሥ የዳግማዊ ፍሬዴሪክን ድርሰት ጠቀሱላቸው:: በዚያን ሰዓት ቢትወደድ የተሰማቸው፣ አስፍሐ ምክትሌ ብቻ ሳይሆን ወዳጄም ስለሆነ፣ ሳይነግረኝ በጀርባዬ ይህን ተንኮል ይሠራብኛል ብዬ አልጠበቅኩም የሚል ነው::

ይህ ሀሳብ አሥመራ በተጠናበት ጊዜ እንደራሴው በምን ምክንያት ሳይሰሙት እንደቀሩ ቢትወደድ አስፍሐን ጠይቂያቸው ነበር:: ቢትወደድ በሰጡኝ መልስ፣ « .... <u>ችግሩ የተፈጠረው በመስማትና ባለመስማት ሳይሆን፣ ነገርን በጥልቅ በመረዳትና ባለመረዳት</u> መካከል ይመስለኛል:: እኛ እየተሰበሰብን በኮሚቴ ስናጠና፣ እንደራሴው የፕሬስ ሹማቸውን ወክለው በእሱ በኩል በየቀኑ ሪፖርት ይቀርብላቸው እንደነበረ አስታውሳለሁ:: እንግዲህ ቢትወደድ አንዳርጌ ያተኮሩት በዋናው መሠረታዊ ጉዳይ ላይ ብቻ ሆኖ፣ ዝርዝሩን አልተከተሉት ይሆናል እንጂ፣ በእኛ በኩል ምሥጢር አድርገን የያዝነው ነገር አልነበረም ...... » ብለዋል:: በዚያን ዘመን የቢትወደድ አንዳርጋቸው የፕሬስ ሹም የነበረውን አቶ ዮሐንስ ተስፋእግዚእን ጠይቄው፤ እሱ የሚያስታውሰው የሚከተለውን ነው:: «....... ጃንሆይ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን በቀጥታ በሚሾሙ ጊዜ፣ ለኤርትራ እንደራሴ አያስፈልግም የሚለው የነ አስፍሐ ፕላን በምሥጢር የተያዘ አልነበረም:: ቢትወደድ አንዳርጌ ይህንን እንዴት ሳይሰሙት እንደቀሩ በሕይወቴ ሲገርመኝ ይኖራል:: ሀሳቡ በሚጠናበት ጊዜ፣ የፖለቲካውን ሁኔታ እየተከታተልኩ ለእንደራሴው ሪፖርት የማቀርብ እኔ ነበርኩ:: እርግጥ <u>ባቀረብኳቸው ማስታወሻዎች ሁሉ፣ የነ አስፍሐ ፕላን የእንደራሴውን ቢሮ እንደሚያዘጋ፣ ሪፖርት ማድረጌ ትዝ አይለኝም::</u> ቢትወደድ አንዳርጌ አለመስማታቸውን የተረዳሁት፣ ከአዲስ አበባ ሲመለሱ በጣም ተናደው በተለይ በእኔ ላይ ከፍ ያለ ወቀሳ በማውረዳቸው ነው:: ...... »

እንግዲህ ከቢትወደድ አስፍሐ መግለጫ ሆነ፣ ከዮሐንስ ተስፋእግዚእ ማስታወሻ እንደምንረዳው፣ በኤርትራ የግርማዊነታቸው እንደራሴ መሠረታዊ የሆነውን ጉዳይ እንጂ ዝርዝሩን እንዲያውቁት አለመደረጉ ግልጽ ነው:: የፌታውራሪ አስፍሐ ፕላን መዘዙ የእንደራሴውንም ሥራ የሚሰርዝ መሆኑ ባልተጠበቀ መንገድ የተገለጠው፣ በራስ አበበ አረጋይ ስብሰባ ላይ ስለሆነ፣ ቢትወደድ አንዳርጌ በጣም ተናደው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ

ለጉባኤው ያቀረቡትን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ እደግፋለሁ አሉ:: እንደሚታወሰው ቢትወደድ አንዳርጌ ወደ አዲስ አበባ በፍጥነት የመጡት፣ ጉዳዩን በቀጥታ ለጃንሆይ አቅርበው ካስፈቀዱ በኋላ፣ ከፍ ባለ የደመቀ አጀብ አሥመራ ለመመለስ ነበር እንጂ፣ የነ አስፍሐ ፕላን እንዳይፈጸም ዋና ተቃዋሚ ለመሆን አልነበረም። የቢትወደድ ጉዳዩን የደገፉት፣ ከአሥመራ ወደ አዲስ አበባ ከመነሳታቸው በፊት፣ ቢትወደድ ጉዳዩን የደገፉት፣ የኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ በጃንሆይ ከተሾመ በኋላ፣ ኃላፊነቱ በቀጥታ ለንጉሠ ነገሥቱና ለፓርላማው ይሆናል ሲባል፣ በሥራ አፈጻጸም ረገድ፣ የጃንሆይ እንደራሴ በጃንሆይ ስም ሆነው፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ለመቆጣጠርና መምሪያ ለመስጠት ሥልጣን የሚያገኙ ስለመሰላቸው ነው:: ነገር ግን በተንከለኞቹ ጥበብ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ጃንሆይ ከሾሙ በኋላ፣ የክቡር እንደራሴው ቦታ እንዲዘጋ መታሰቡን አንዳርጋቸው መሣይ ገና ከመነሻው አውቀውት ቢሆን ኖሮ፣ አዲስ አበባ ድረስ አይጓዙም ነበር::

በመከላከያ ሚኒስትሩ ሊቀመንበርነት በተካሄደው ስብሰባ ላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ያቀረቡትን ሀሳብ በኤርትራ ቢትወደድ አንዳርጌ ድጋፋቸውን ሲሰጡ የተናገሩት ቃል፣ የራስ አበበ ኮሚቴ ጉዳዩን ባጭሩ ለመወሰን የሚያመቸው ሆነ:: « ...... ክቡር አቶ አክሊሉ በሰፊው የተናገረውን አድምጬ በጣም ደስ ብሎኛል:: እነ ፊታውራሪ አስፍሐ ይህን ሀሳብ ከየፓርለማ አባሎች ጋር አጥንተው ሲያቀርቡ፣ በኤርትራ ሕገ መንግሥት ላይ ምን ችግር እንደሚፈጥርና፣ በኢንተርናሲዮናል የፖለቲካ ጉዳይም፣ የጃንሆይን መልካም ስም የሚያስነካ መሆኑን አልተረዱትም:: ከዚህም በላይ ጃንሆይ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ይሾማሉ ቢባልም፣ መጀመሪያ ፓርላማው ከመረጠው በኋላ ስለሆነ፣ ጠቃሚነት የለውም:: ይህ ዓይነቱ አሠራር እንግሊዝ አገር ለንግሥት ኤልሳቤጥ የተሰጠውን ሥልጣን የሚመስል ነው:: ...... አቶ አክሊሉ በተናገረው ላይ እኔ የምጨምረው ቢኖር፣ አሁን የሚሠራበት የኤርትራ ሕገ መንግሥት ለጃንሆይ የፈጠረው አንዳችም ችግር አለመኖሩን ነው:: ስለዚህ ፌዴራሲዮኑ ሳይነካ እንዳለ በሠላም እንዲቀጥል ማድረጉ ለብዙ ነገር በጣም ጠቃሚ መሆኑን አቶ አክሊሉ ካቀረበው ሀሳብ ጋር በሙሉ እተባበራለሁ:: ...... » ይህ ከቢትወደድ አንዳርጋቸው መሣይ የተሰጠው መግለጫ፣ ሳይጠበቅ በድንገት እንደፈነዳ ቦንብ የሚቆጠር ሆነ። ይህን ሁሉ ካዳመጡ በኋላ፣ ሳይጠበቅ በድንገት እንደፈነዳ ቦንብ የሚቆጠር ሆነ። ይህን ሁሉ ካዳመጡ በኋላ፣ <u>እጅግ የብዙ ሰዎችን ሀሳብ በማስተባበርና ፍሬ ነገሩን ጨምቆ በማቅረብ፣ እጅግ የታወቁትና የተከበሩት ራስ አበበ አረጋይ፣</u> ለጉዳዩ ማስሪያ የተናገሩት ቃል የሚከተለው ነበር::

« ..... ኤርትራን የሚያስተዳድረው ዋናው ኃላፊ፣ በፊት እንደሚደረገው በዚያው በእነሱ ፓርላማ መመረጡ ቀርቶ፣ ጃንሆይ ቢሾሙት ይሻላል የተባለው ሀሳብ እዳር እንዲደርስ፣ ቢትወደድ የደከምክበት ዋና ነገር ነው ብለን ነበር:: ጃንሆይም ዛሬ እዚህ የተሰበሰብነውን ያዘዙን፣ ለጉዳዩ አፈጻጸም የሚበጀውን አሟልተን እንድናቀርብ ነው እንጂ፣ ሀሳቡ ውድቅ እንዲሆን፣ ቢትወደድም ትስማማበታለህ ብለን አልነበረም:: መቸም ሁላችንም በልማድ እንደምናውቀው፣ ከመነጋገርና ሀሳብ ከመለዋወጥ የተነሣ፣ አንዳንድ በመጀመሪያ ያልታየ ተደብቆ የቆየ ፍሬ ነገር ብቅ ስለሚል፣ አቶ አክሊሉ በሰፊው የነገረን፣ ሁላችንንም ከመነሻችን ወደ ተለየ ሀሣብ ላይ እንድናመራ ያደረገን ይመስለኛል:: ...... ይኸ የኤርትራ መተዳደሪያ ሕግ እንደዚሁ እስካሁን ባለበት አኳኋን ቢቆይ፣ በዓለም ማህበርና በታላላቆቹ መንግሥታቶች ዘንድ፣ የጃንሆይ የተከበረ ስም እንደሚጠበቅ፣ ከዚህም በቀር የወደፊቱ ነገራቸው ያልተለየላቸው ሱማሌዎች፣ ከጣልያን ሲወጡ

ወደ እኛ እንዲመጡ ይረዳል እያለ፤ አቶ አክሊሉ በየጊዜው ማስረዳቱን አላቆመም:: ለዚህ ሁላችንም ምስክሮች ነን:: ዛሬም ነገሩን ደህና አድርገን እንድናብላላው፣ በስፊው አስታውሰናል:: ..... አቶ አክሊሉ ባቀረባቸው ሀሳቦች ውስጥ (አራት ይመስሉኛል) በእኔ በኩል በጣም አዲስ ሆነው የታዩኝ ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ተይዘዋል::

....... የመጀመሪያው፣ አሁን የሚሠራበት ሕግ ካልተለወጠ፣ ጃንሆይ ሆማሲኑን የኤርትራውን እለቃ ለመሾም የማይችሉ መሆናቸውን ነው:: ሁለተኛው ሕጉ ቢለወጥም ተሿሚውን ከመካከላቸው የሚመርጡት ፓርላማዎቹ ስለሆኑ፣ ለወግ ካልሆነ በስተቀር፣ ለጃንሆይ ሥልጣን ጠቃሚ አይደለም የተባለው ነው:: በዚህ ነገር ላይ ቢትወደድም ስታስረዳ ከእንግሊዝ አገር በማመሳሰል የጠቀስከው ይኸንን በማሰብ ሳይሆን አይቀርም:: እነዚህ ሁለቱ ጉዳዮች በጣም የሚታሰቡ ናቸው:: ነገሩ ሁሉ በዚህ በተባለው አኳኋን ላይ የሚገኝ መሆኑን ስንመለከት፣ እስከ ዛሬ የሚሠራበትን የኤርትራን ሕግ ማስለወጡ ለምንም እንደማይጠቅም ለሁላችንም በግልጥ የታየ መስሎኛል:: አሁን ዋናው ቁም ነገር፣ ጃንሆይ ከሀማሴኖቹ ለቀረበላቸው ማመልከቻ፣ ጉዳዩ አለመፈቀዱን ገልጠው መልስ ሲሰጡ፣ የትኛውን ምክንያት በማስቀደም፣ የትኛውን በማስከተል እንደሚሻል፣ አቶ አክሊሉ ሀሳብ ሰጥተን ስብሰባውን ብናቆም ይሻላል::

<u>አቶ አክሊሉ፣</u>

ከሁሉ አስቀድሜ ክቡር ራስ፣ስብሰባችንን ሲከፍቱ ለተናገሩትና አሁንም ለስብሰባችን መዝጊያ ለገለጹት ጥልቅ አስተያየት ከፍ ያለ ምሥጋናዬን እንዲቀበሉኝ እለምናለሁ:: ዕድል አጋጥሞኝ እርስዎ በሚመሩት ሰብሰባ በተገኘሁ ቁጥር፣ ብዙ ትምህርት እማራለሁ:: እንደዚሁም ባልጠበቅኩትና ባላሰብኩት መንገድ፣ ስለ ኤርትራ ጉዳይ ያቀረብኩት ሀሳብ በክቡር ቢትወደድ አንዳርጋቸው ስለተደገፈልኝ ትልቅ ደስታ ተሰምቶኛል:: አሁን ክቡር ራስ ወደ ጠየቁኝ ልመለስና፣ ለኤርትራ ፓርላማ አባሎች ከጃንሆይ የሚሰጠው መልስ በጣም ማጠር አለበት የሚል አስተያየት አለኝ::
«.....በኢትዮጵያዊነት ተጨንቃችሁ፣ለአስተዳደሩ መሻሻል ያቀረባችሁልን ሀሳብ በጣም የሚያስደስት ነው:: ጉዳዩን ካጠናነው በኋላ፣ በዛሬው ሰዓት ይህን ሀሳብ በሥራ ላይ እንዲውል የፈቀድን ጊዜ፣ ጠላቶቻችን የፖለቲካ መዛሪያ አድርገው በዓለም ማህበር በኩል ሊያጠቁን ይችላሉ:: ከዚህም በቀር በሱማሌ በኩል ያለውን ዓላማችንንስ ለሚያበላሽብን፣ ይኸ ያቀረባችሁልን ሀሳብ ለጊዜው እንዲቆይ ይሁን ..... » ተብሎ ቢጻፍላቸው ይሻላል::

<u>ቢትወደድ አንዳርጋቸው፤</u>

አቶ አክሊሉ የሰጠው ሀሳብ በቂ ነው:: ሌላ መጨመር አያስፈልግም:: ሆኖም የጃንሆይ መልስ በጽሑፍ ከሚሰጥ፣ ቃሉ ይኸው የተባለው ሆኖ፣ እኔ መማክርቶቹን ቤተመንግሥት ጠርቼ ብነግራቸው ይሻላል::

<u>ራስ አበበ አረጋይ፤</u>

« ...... ማለፊያ ሀሳብ ነው:: ቢትወደድ አንተም እዚህ ድረስ መጥተህ ብዙ ከደከምክ በኋላ ጉዳዩ ያልተፈቀደበትን ምክንያት በቤተመንግሥቱ ሰብስበህ ብታስረዳቸው ይሻላል:: ...... አሁን ሁላችንም በዚሁ ስለተስማማን፤ አቶ ገብረወልድ በአንተ በኩል የሚጨመር ሀሳብ ከሌለ፤

ጉዳዩ በቶሎ ለጀንሆይ ቀርቦ እንዲወሰን እንተው እንደሚሆን እንደሚሆን አድርገው:: ...... »

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ በምክትል ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረወልድ እንግዳወርቅ፥ ተዘጋጅቶ የቀረበላቸውን ቃለ ጉባኤ ከተመለከቱ በኋላ፣ የተጠናውን ሀሳብ ሲያጸድቁ፥ የሰጡት መሪ ቃል የሚከተለው ነበር::

« ...... አክሊሉ ለሱማሌም ሆነ ለሌላ ጉዳይ ምክንያት እየደረደረ፣ የዚህ የኤርትራ ፌዴራሲዮን ነገር እንዳይነካ መወትወቱ፣ መቼም የማይቀር ነገር ሆኗል:: ...... እኛ የምንሾመው የኤርትራ አስተዳዳሪ፣ አለማህ አጠፋህ ብለን የምንጠይቀው እኛ ብቻ ነን እንጂ፣ ፓርላማውም ከእኛ ጋር ጠያቂ እንዲሆን እንፈቅድም:: በዚህ በኩል አክሊሉ የተናገረው የተገባ ነው:: እንዳርጋቸውም ፓርላማዎቹ ይኸን ነገር ሲያቀርቡለት፣ ጠቃሚነቱንና ጉጂነቱን በመገምገሪያ እዚያው ማጣራት ነበረበት:: እዚህም ለማስፈቀድ ከመጣ በኋላ፣ የአክሊሉን ሀሳብ ሲያሞቅ መታየቱ የተገባ አደለም:: ....... እዚህ ላይ አስፍሐ የሚጨነቀውና በየቀኑ የሚደክመው፣ ከቅንነት ጋር ከልቡ መሆኑ መታወቅ አለበት:: ...... አሁን በአበበ አረጋይ ተጠንቶ የቀረበልን ሀሳብ እንዲፈጸም ይሁን ..... »

የግርማዊነታቸው እንደራሴ አሥመራ ከተመለሱ በኋላ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉንና የሀሳቡ ደራሲዎች የሆኑትን ዋና ዋናዎቹን የፓርላማ መማክርቶች በቤተመንግሥቱ ሰብስበው፥ ጉዳዩ ያልተፈቀደበትን ምክንያት ሲያስረዱ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አክሊሉ በዓለም ማህበር በኩል እና በተለይም በሱማሌ ጉዳይ ችግር ይፈጥራል ብለው በመቃወማቸው ነው አሉ:: ቢትወደድ እንደዚህ የተናገሩት፣ የመማክርቶቹ ሀሳብ በጀንሆይ በኩል ዋጋ የተሰጠው መሆኑንና ሳይፈቀድ የቀረበት ምክንያት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ስለተቃወሙ ነው ብሎ ለማሳመን ነበር:: በዚህ ጊዜ እርስዎስ ክቡር እንደራሴ፣ እስከ ምን ድረስ ተሚገቱልን ? ብሎ ደፍሮ የሚጠይቃቸው ቢኖር፣ የሚሰጡትን መልስ በአድናቆት ለመስማት የማይጓጓ አልነበረም:: መላከ ሠላም ዲሚጥሮስ ገብረማርያምና ደጃዝማች ገብረዮሐንስ ተስፋ ማርያም፥ « ...... <u>እኛ ለፍተን የምናግለውን ምድጃ አቶ አክሊሉ በየጊዜው በረዶ የሚለቁበት በምን ምክንያት ነው</u> ? ....... » ብለው ቱግ አሉ:: የተሰበሰቡት መማክርቶቹም ብስጭታቸው እየጋለ ሲመጣ፣ ዘዴኛው አስፍሐ ቶሎ ብድግ ብለው የተፋፋመውን እሳት አበረዱት::

« ...... የኤርትራ ሕገ መንግሥት ጉዳይ የተባበሩት መንግሥታትና የኃያላን አገሮች እጅ ያለበት መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን:: ፌዴራሲዮኑን የሚነካ አንድ እርምጃ በወሰድን ቁጥር፣ ብዙ ጥያቄዎች ይቀርባሉ:: ለዚህ መልሱን የሚሰጡትና የሚሟገቱት፥ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ናቸው:: ግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችንም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸውን ጠይቀው፣ በቀረበላቸው አስተያየት መሠረት ለጊዜው እንዲቆይ ያዘዙት፣ በእውነት ችግር የሚፈጥር መሆኑን ቢያምኑበት ነው እንጂ፣ እኛን ቅር አሰኝተው የአቶ አክሊሉን ሀሳብ ለመቀበል ብለው አይደለም:: አቶ አክሊሉ ደግሞ የአንድነታችን ተዋጊ ሆነው የፈጸሙትን ሁሉ እኛም መርሳት የለብንም:: ዛሬ ለኤርትራ ጉዳይ ኃላፊዎቹ እኛ ነን፥ ጉዳዩን የምናውቀው እኛ ነን፥ እያሉ የሚመጻደቁት ሁሉ፣ በዚያ በትግሉ ዘመን ሌላ ቦታ የነበሩ እንዳች አስተዋፅኦ ያላደረጉ፣ የሙግቱን ታሪክ እንኳን በሚገባ ያልተከተሉ ናቸው:: አቶ አክሊሉ ግን የንጉሠ ነገሥታቸውን አደራ ይዘው የኤርትራን ጉዳይ

የጀመሩትና ያስፈጸሙት እሳቸው በመሆናቸው ችግሩን ከማንም የበለጠ ያውቁታል:: ...... ግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችን በክቡር እንደራሴያቸው አንደበት የላኩልን ንጉሣዊ መልዕክት፣ ስፖለቲካው ጉዳይ ሲባል፤ ህዝባችን ለጊዜው ይቆይ አሉ እንጂ፤ ይውደቅ አላሉም:: ይህንን መሪ ቃል እንደተለመደው በደስታ አክብረን እንቀበላለን:: አሁን እፊታችን የተደቀነ አንድ ትልቅ ሥራ አለ:: ይኸውም ከሶስት ወር በኋላ የሚደረገው የፓርላማችን የሁለተኛው ተርም ምርጫ ነው:: ባለን አቅም ሁሉ በርትተን፣ የአንድነት ወገኖቻችን በያለበት ድጋፍ አግኝተው እንዲመረጡልን ማድረግ አለብን:: ለዚህ ግባችን፤ የተወደዱት ንጉሠ ነገሥታችንና የክቡር እንደራሴያቸው እርዳታ እንደማይለየን የታወቀ ነው:: ኢትዮጵያዊት ኤርትራ ኢትዮጵያዊነቷን የሚነካባት የለም:: አንድ ቀን ምናልባትም በቅርብ ጊዜ ከግባችን እንደርሳለን ...... » ብለው፤ ፊታውራሪ አስፍሐ የሰጡት ማብራሪያ መማክርቶቹን ስለአረካቸው፣ ምንም ዓይነት ጥያቄ ሳያቀርቡ እንደራሴውን ተሰናብተው ከቤተ መንግሥቱ ወጡ::

ቢትወደድና ፊታውራሪ ልብ ለልብ ተዋውቀዋል:: በአስፍሐ መሪነት በኤርትራ ፓርላማ ውስጥ የተፀነሰውን ፕላን ጃንሆይ ፈቅደው ቢሆን ኖሮ፣ ቢትወደድ ሥራ ፈት እንደሚሆኑ የተረዱት፣ አዲስ አበባ በራስ አበበ ስብሰባ ላይ መሆኑ ይታወሳል:: ወዲያውም፤ ከጃንሆይ ለማስፈቀድ በሞቀ መንፈስ ይዘውት የሄዱትን ዶሴ፣ እንዳይጸድቅ ዋና ተቃዋሚ ሆነው ያደረጉትን ንግግር፡ ፊታውራሪ ሰምተዋል:: ከዚህም በላይ በዚያ በትግሉ ዘመን ምንም ዓይነት አስተዋፅኦ ያላደረጉ፤ አሁን የኤርትራ ጉዳይ ይመለከተናል ባዮች የሆኑት፣ ሌላ ቦታ የነበሩ ናቸው በማለት ፊታውራሪ አስፍሐ በአግቦ የተናገሩት፣ የቀድሞውን የበጌምድርና የስሜን ጠቅላይ ገዥ፣ የዛሬውን በኤርትራ የጃንሆይ እንደራሴ ለመንካት ሳይሆን አልቀረም::

ከእንግዲህ ወዲህ ከዚህ ከግንቦት እስከ መስከረም 1956 ዓ.ም ድረስ ባሉት ወራቶች፣ ፊታውራሪ አስፍሐ የተጠመዱበት ትልቁ ሥራ፣ የሁለተኛውን ተርም ጠቅላላ የፓርላማ ምርጫ ማዘጋጀት ስለሆነ፣ ለአስተዳደሩ መዋሀድ የታሰቡትን ጉዳዮች ሁሉ ለመፈጸም፣ ለመጭው የሥልጣን ዘመን እንዲተላለፉ ማድረግ ግዴታ ሆኖባቸዋል:: በ1952 ዓ.ም እንግሊዞች ባዘጋጁት የመጀመሪያው ፓርላማ ምርጫ፣ ከመላው ኤርትራ ግዛት ሠላሣ አራት (34) ክርስቲያኖችና ሠላሣ አራት እስላሞች (34) እንዲመረጡ ስለተደረገ፣ አሁንም ለሁለተኛው ጊዜ ይኸው ድልድል እንዲከበር የፊታውራሪ ዋና ጥረት ነበር:: በፓርላማው ውስጥ ለተዘጋጁት ስልሣ ስምንት (68) ወንበሮች የእስላሞቹ ወኪሎች ከክርስቲያኑ እንደራሴዎች ቁጥር ያነሱ ሆነው ከተገኙ፤ የሀይማኖት ልዩነት ተደረገ የሚል የጠላት ፕሮፓጋንዳ እንዳይነሳ በብርቱ ታስቦበታል:: እንዲሁም ፌዴሬሽኑ ተሰርዞ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ለማዋሀድ እንዲቻል፣ ለምርጫው ከሚወዳደሩት ከክርስቲያኖቹም ሆነ ከእስላሞቹ ውስጥ፣ የአንድነት ደጋፊዎች የሆኑት በብዛት እንዲመረጡ፣ ብዙ ጥረት ተደርጉበታል:: የእስላም ሊግ ወገኖችም እነ ኢብራሂም ሡልጣንና እነ ዑመር ቃዲ፣ ለመጀመሪያው ፓርላማ የተመረጡት በእንግሊዞች እርዳታና በጣልያኖች ገንዘብ እንደነበረ ይታወሳል:: አሁን በዚህ በሁለተኛው የምርጫ ዘመን እንግሊዞች ስለሌሉ፣ ጣልያኖችም ስለተዳከሙ፣ አንዳንድ ኢትዮጵያን ከሚጠሉ የዓረብና የእስላም አገሮች እርዳታ በመፈለግ፣ ወገኖቻቸውን በብዛት ለማስመረጥ በብርቱ ደክመው ነበር::

በዚህ አኳኋን በአንድነት ደጋፊዎችና በተቃዋሚዎቹ መካከል ውድድሩ ለአንድ ወር ያህል ሲጦፍ ከከረመ በኋላ፣ የምርጫው ውጤት ሲታይ፣ ቺፍ ኢግዜኩቲቭ በወጡትና በተመኙት መልክ ሆኖ ተፈጸመላቸው።

1. እንደታሰበው ከመላው ኤርትራ ግዛት ሠላሣ አራት (34) ክርስቲያኖችና ሠላሣ አራት (34) እስላሞች ተመረጡ።

2. የራቢጣዎቹ መሪዎችና ቀንደኞች የነበሩት እነ ኢብራሂም ሡልጣን፣ ዑመር ቃዲ፣ ኢድሪስ መሐመድ አዱም፣ የከረኑ ቃዲ ሙሣ፣ የዓድቀይሁ ቃዲ ዓሊ ...... ወዘተ ..... ሳይመረጡ ቀሩ።

3. የፌታውራሪ አስፍሐ ወዳጅ፣ የቀድሞው የፓርላማ ፕሬዚዳንት ዓሊ ራዳይና ወገኖቻቸው በሙሉ ተመርጠው የቀድሞ ቦታቸውን ያዙ።

4. በምርጫው ውጤት ማግሥት፣ ፓርላማው ጠቅላላ ስብሰባ አድርጐ፣ ፊታውራሪ አስፍሐ ወልደሚካኤልን ያለአንዳች ተቃዋሚ በሙሉ ድምፅ ለአራት ዓመታት የኤርትራ ቺፍ ኢግዜኩቲቭ አድርጐ መረጣቸው።

አስፍሐ ወልደሚካኤል የዚህን የሁለተኛውን የፓርላማ ምርጫ ውጤት ትልቅ ድል አድርገው ስለቆጠሩት፣ ለንጉሠ ነገሥቱ በላኩት ደብዳቤ ስሜታቸውን የገለጹት እጅግ በሞቀ የደስታ መንፈስ ነበር። « ...... የግርማዊነትዎ ፍቅር ያደረበት የኤርትራ ታማኝ ሕዝብዎ፣ በጃንሆይ ለጋስነት በተሰጠው ሕገ መንግሥት መሠረት፣ የሁለተኛውን ዘመን የፓርላማ ምርጫ በሥርዓት አከናውኗል። ...... የአስተዳደሩንም መሪነት እንደገና አደራውን በእኔ አገልጋይዎ ላይ ጥሎታል። ..... አዲሱ የኤርትራ ምክር ቤት በኤርትራ ሕዝብ ስም ሆኖ፣ እኔን አገልጋይዎን ያለ አንዳች ተቃዋሚ በሙሉ ድምፅ የመረጠው፣ የግርማዊነትዎን መልካም ፈቃድ ለመፈጸም ስለሆነ፣ በጃንሆይ ዘንድ ሞገስ ያስገኝል ብዬ አምናለሁ። ....... ለአንድነታችን ተሡሳኪች የነበሩትም እነ ኢብራሂም ሡልጣንና ኢድሪስ አዱም ከነመሰሎቻቸው፣ ሕዝቡ ስላልመረጣቸው እንደወጡ ቀርተዋል .... »

ለሁለተኛ ጊዜ የተመረጡት ቺፍ ኢግዜኩቲፍ፣ ባለፈው ውድድር ላይ አርባ ስምንት የድጋፍ ድምፅ ሲያገኙ፣ ሀያ የሚሆኑ መማክርቶች ተቃዋሚዎች ነበሩ። ዘንድሮ ግን ከስልሣ ስምንቱ አባሎች ውስጥ፣ አንድም ተቃዋሚ ሳይኖር መመረጣቸው እጅግ አስደስቷቸዋል። ከዚህ በላይ ደግሞ ውስጥ ውስጡን ባደረጉት ብርቱ ጥረት፣ ዋና ዋና ጠላቶች የነበሩት እነ ኢብራሂም ሡልጣን እንደወጡ እንዲቀሩ አስደርገዋል። የአርባ ሁለቱ ዓመት ጐልማሳው አስፍሐ፣ ይህን ሁሉ ድል ሲያገኙ፣ በጣም ከሚወዷቸው ንጉሠ ነገሥት የተለየ አባታዊ ምረቃ ይደርሰኛል ብለው ሳይጠብቁ አልቀሩም። መቼም፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘንድ፣ በጣም ያስደስታቸዋል የተባለው ነገር፣ አንዳንድ ጊዜ እንደታሰበው ስለማይሆን፣ የጃንሆይ ቴሌግራም ሳይውል ሳያድር በፍጥነት ቢደርስም፣ ይህን ያህል የተጋነነውን ደስታ የሚያሣል አልነበረም። « ..... የአስተዳደሩን ኃላፊነት እንድትቀጥል በእኛም በኩል የተፈቀደ ስለሆነ፣ ፓርላማዎቹ የፈጸሙት የተገባ ነው። አንተም ብዙ ሥራዎች ስላሉብህ ባለፈው ጊዜ ያሳየኸውን ደስ የሚያሰኝ ትጋት እንድትቀጥል እግዚአብሔር ይርዳህ ...... » በሚል ቃል የተወሰነ ነበር።

ከዚህ በላይ እንደሚታየው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቴሌግራም፣ እንኳን ተመረጥክ ..... እንኳን ደስ አለህ ..... አላለም:: የጃንሆይን መልካም ፈቃድ ፓርላማው መፈጸሙ የተገባ መሆኑን የሚገልጥና፡ እንዳለፈው ጊዜ የአስፍሐ ትጋት እንዲቀጥል የሚያሳስብ ነው:: የንጉሠ ነገሥቱ መልዕክት ከልማዱ ቀዝቀዝ ያለ ሆኖ በመገኘቱ፡ አስፍሐ ሥጋት አላደረባቸውም:: « ...... የጌታዬን ጠባይ ደህና አድርጌ አውቃለሁ:: ቴሌግራሙን ለሚያዘጋጀው ሰው መምሪያ በሚሰጡበት ጊዜ፣ ያለጥርጥር አንድ የሚያናድድ ሌላ ነገር በድንገት ደርሶ መንፈሳቸውን አስቸግሮት ይሆናል እንጂ፣ ለታማኛቸው ለአስፍሐ በዚች ቃል ብቻ አይወስኑም ነበር ...... » ብለው ተርጉመውታል::

እንግዲህ፣ የአስፍሐ ወልደሚካኤል የአንድ ዓመት የሥልጣን ዘመን በሥን አኳኋን እንደተፈጸመ ሲታይ፣ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ የነበረው ምኞት ሁሉ አልተሳካም ቢባልም፡ በአብዛኞዎቹ የአንድነት ወገኖች ዘንድ፣ ከተድላ ባይሩ ዘመን የተሻለ መግባባትና ሠላም የሰፈነበት ዓመት ነው ተብሎ ተገምቷል::

# ሁለተኛው የአስፍሐ ዘመን

1956 - 1960

ደጃዝማች ተድላ ባይሩ፣ የኤርትራ መሪነቱን በተቀበሉ በመጀመሪያው ዓመት፣ ፌዴሬሽን ለማፍረስ የሚጠበቀውን እርምጃ አልወሰዱም በማለት፣ እንድነቶች በሚያወርዱባቸው ወቀሳ ተወጥረው እንደነበረ ይታወሳል:: እርግጥ ነው ተድላ የኤርትራ «ቀዳማይ መራሂ መንግሥቲ» በመባል፣ ሥልጣኑ ከዕለት ወደ ዕለት እየጣማቸው ስለሄደ፣ ፌዴሬሽኑን ማፍረስ አልፈለጉም:: ይሁን እንጂ ደጃች ተድላ ቢፈልጉም ኖሮ፣ ማፍረሱ ቀላል እንዳልነበረ፣ አስፍሐና ጓደኞቻቸው የተረዱት በእሳቸው ቦታ ከተተኩ በኋላ ነው:: በቴዎሪ መገንባት እንጂ ማፍረስ ይከብዳል ስለማይባል፣ በዚያን ጊዜ ተድላ ባይሩ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ ምን ያህል ችግር እንደነበረባቸው፣ በዝርዝር ለማስረዳት ፈቃደኛ ቢሆኑም እንኳን፣ ተቀባይ እንደማይኖራቸው የታወቀ ነበር::

ከተድላ በኋላ በ1956 ዓ.ም የሁለተኛው የፓርላማ ጠቅላላ ምርጫ በተደረገ ጊዜ፣ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች እነ ኢብራሂም ሡልጣን ሳይመረጡ በመቅረታቸው፣ አንድነቶች ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ ሜዳው ተመቻቸው ተብሎ ሙሉ ተስፋ ተደረገ:: ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ከፊታውራሪነት ወደ ደጃዝማችነት ደረጃ ያሳደጓቸው አስፍሐ ወልደሚካኤል ግን፣ በመጀመሪያው ዓመት ባገኙት ኤክስፔሪያንስ፣ በቴዎሪና በፕራቲክ መካከል ያለውን ልዩነት በይበልጥ ስለተረዱ፣ በሁለተኛውም የሥልጣን ዘመን በሩጫ የሚፈጸም ነገር አለመኖሩ ግልጽ ሆኖ ታያቸው:: « ከእንግዲህ ወዲህ ከልባችን የምንፈልገውን ትልቁን ጉዳይ (የፌዴሬሽኑን ማፍረስ) ከግቡ ለማድረስ የምንችለው ደረጃ በደረጃ እየተራመድን ነው » የሚል አቋም ያዙ:: ደግነቱ እነዚህ ደረጃ በደረጃ የሚከናወኑት ጉዳዮች ምንና ምን መሆናቸውንና፣ እያንዳንዳቸውንም ለመፈጸም ምን ያህል ጊዜ እንደሚጠይቅ፣ደጃዝማች አስፍሐ አስቀድመው ባለመግለጻቸው፣ለተቆጣጣሪዎቻቸው ምቹ አልሆኑም:: የንጉሠ ነገሥቱ ባለሟል በመሆናቸውና፣ ከወገኖቻቸው

ከአንድነቶችም ጋር ያላቸው መግባባት የጠነከረ ስለሆነ፣ ይኸ ቀረ ይኸ ጐደለ የሚል ወሬና ሁሜታ አላስጋቸውም።

አስፍሐ ወልደሚካኤል ከቺፍ ኤግዜኩቲፍነት ሥልጣናቸው ጋር በኤርትራ የግርማዊነታቸው ምክትል እንደራሴነቱን ደርበው መያዛቸው፣ ለውጪ ታዛቢዎች ሆነ ለተግባሩ አፈጻጸም ተገቢ አለመሆኑን ቢትወደድ አንዳርጌ ደጋግመው ያቀረቡትን ሀሳብ ንጉሠ ነገሥቱ አልተቀበሉትም። እንዲያውም በታህሣሥ 1958 ዓ.ም አንዳርጋቸው መሣይ ራስ ተብለው የአገር ግዛት ሚኒስትርነትን ሲሾሙ፣ ደጃዝማች አስፍሐ ተጠባባቂ እንደራሴ ሆነው ሥራውን እንዲመሩ የጃንሆይ መልካም ፈቃድና ትዕዛዝ ተሰጠ። በዚህ መሠረት ከታህሣሥ 1958 ዓ.ም እስከ ታህሣሥ 1959 ዓ.ም ድረስ ለአንድ ዓመት የዘውድ እንደራሴነቱንና የመንግሥቱን መሪነት ሥልጣን በማጣመር፣ ደጃዝማች አስፍሐ የተመቸ መልካም የሥራ ዘመን አሳልፈዋል።

በሕገ መንግሥት አንቀጽ 56 እንደተደነገገው፣ ለኤርትራ የውስጥ አስተዳደር የሚያስፈልገውን የሕግ ረቂቅ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ አዘጋጅቶ ለፓርላማው ሲያቀርብ፣ ምክር ቤቱ ተነጋግሮበት በድምፅ ብልጫ ይወስናል። ከዚህ በኋላ በአንቀጽ 15 መሠረት በፓርላማው የጸደቀው ሕግ አዋጅ ሆኖ እንዲወጣ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ አቅርቦ የሚያስፈቅደው ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ነው። ከ1952 ዓ.ም ጀምሮ በየጊዜው ፓርላማው የሚያሳልፈው የሕግ ረቂቅ ከፌዴራሉ መንግሥት ሥልጣን ጋር የማይጋጭ መሆኑን አጣርቶ እንዲታወጅ ለመፍቀድ፣ ቢትወደድ አንዳርጋቸው ጊዜ ይፈጁሉ የሚል ሁሜት ነበር። ከታህሣሥ 1958 እስከ ታህሣሥ 1959 ዓ.ም ድረስ በነበረው የአስፍሐ ተጠባባቂነት ዘመን፣ ይኸ ችግር ሳይታይ ቀረ። አሠራሩም በሚከተለው አኳኋን ይከናወን ነበር።

1. ፓርላማው የወሰነው የሕግ ረቂቅ በአዋጅ እንዲወጣ፣ አስፍሐ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ፣ ለአስፍሐ ተጠባባቂ እንደራሴ ያቀርባል።

2. ተጠባባቂ እንደራሴ አስፍሐ፣ ፓርላማው ያሳለፈው ሕግ ከፌዴራሉ ከኢትዮጵያ መንግሥት ሥልጣን ጋር የማይጋጭ መሆኑን በደቂቃ ውስጥ መርምሮ ያረጋግጥና፣ ሕጉ አዋጅ ሆኖ እንዲታተም ለቺፍ ኤግዜኩቲፍ አስፍሐ ያስተላልፋል።

3. ቺፍ ኤግዜኩቲፍ አስፍሐም፣ ከተጠባባቂ እንደራሴ አስፍሐ በደረሰው ፈቃድ መሠረት፣ ሕጉን አዋጅ አርጐ ያወጣዋል።

በዚህ አኳኋን በአስፍሐ ተጠባባቂ እንደራሴና በአስፍሐ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ መካከል፣ ፍጹም የሆነ መግባባትና መተማመን ስለተፈጠረ፣ በአንድ ዓመት ውስጥ የተከናወነው የሥራ ቅልጥፍና፣ የፌዴሬሽኑን መፍረስ ጉዳይ ጨርሶ አስረስቶት ከረመ።

በታህሣሥ 1959 ዓ.ም የቀድሞው የንጉሠ ነገሥቱ አማች፣ ጄኔራል ዐቢይ አበበ የፍርድ ሚኒስትርነቱን ለቅቀው፣ በኤርትራ የግርማዊነታቸው እንደራሴ ሆነው ሲሾሙ፣ ደጃዝማች አስፍሐም በዚህ ታላቅ ሹመት ሥነ ሥርዓት ላይ

እንዲገኙ ተደርጐ፣ የእሳቸውም የምክትል እንደራሴነት ሥልጣን የሚቀጥልላቸው መሆኑ ተነገራቸው:: በዚህ ዕለት ከነበሩት ተሿሚዎች መካከል፣ ከስዊድን የባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትርነት ሥራቸውን ጨርሰው የተመለሱት ደጃዝማች ተድላ ባይሩ፣ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል እንዲሆኑ ሲነገራቸው፣ ደጃች አስፍሐ ከሊጋባው አጠገብ ቆመው ተሞልካች ሆነው ነበር::

አዲሱ የጃንሆይ እንደራሴ ዐቢይ አበበና፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ አስፍሐ ቀደም ያለ ትውውቅ ባይኖራቸውም፣ እየተከባበሩ ለመግባባትና ለመቀራረብ ጊዜ አልወሰዱም:: አስፍሐ የተድላን ሥልጣን ሲረከቡ፣ የፕሮቶኮሉን ግርግር በማሻሻላቸው ከፍ ያለ አድናቆት አንዳገኙት ሁሉ፣ ጄኔራል ዐቢይ ደግሞ የቤተመንግሥቱ ሥርዓት እንዲቀለጥፍና፣ ለባለ ጉዳዮች በሩ ዝግ እንዳይሆን በማድረጋቸው፣ እጅግ የተወደዱ ሆኑ:: ዐቢይ አበበ በተፈጥሮአቸው ጨዋነትና እርጋታ፣ ደግነትና ትህትና ያላቸው ሰው በመሆናቸው፣ በኤርትራ ሕዝብ ዘንድ የተሰጣቸው ከፍተኛ ግምትና አክብሮት የተለየ መልክ ነበረው:: በጥር ወር 1960 ዓ.ም የግርማዊነታቸው እንደራሴ አሥመራ ደርሰው አዲሱ ሥራቸውን ሲጀምሩ፣ በመጭው ነሐሴ ወር ለሰስተኛው ተርም ለሚደረገው የፓርላማ ምርጫ፣ ቺፍ ኤግዜኩትፉ ከፍ ያለ ዝግጅት ላይ ነበሩ:: እንደዚሁም ለሁለተኛ ጊዜ የተመረጠ ብትን የአራት ዓመት የሥልጣን ዘመን ለመፈጸም ስምንት ወር ብቻ ስለሚቀራቸው፣ በዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ እንደማይችሉ የታወቀ ነበር:: ሆኖም በእነዚህ ስምንት ወራቶች ውስጥ አንዳንድ ታሪክ ነክ የሆኑ ጉዳዮች ሳይፈጸሙባቸው እንዳይቀሩ፣ ለኤርትራ ፌዴሬሽን ምልክት የሆነውን <u>ባንዲራ ለመሰረዝና፣ የአስተዳደሩንም መጠሪያ ስም ለማሻሻል፣</u> አስፍሐ ወልደሚካኤል አርምጃ ወሰዱ::

## ባንዲራው የኢትዮጵያ ሆነ::

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በተለይ የአስፍሐ መንግሥት እንደተጀመረ፣ ይህን በተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር ሀሳብ የተዘጋጀ ሰማያዊ ቀለም ባንዲራ ለማጥፋት፣ አንድነቶች ብዙ ሙከራዎች አድርገው እንደነበረ ይታወሳል:: ነገር ግን የእስላም ሊግ አባሎች ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እያከታተሉ የሚያቀርቧቸው አቤቱታዎች ስለበረከቱ፣ አንድነቶች የቀመኙትን በቶሎ ለመፈጸም አላመቻቸውም:: በሁለተኛው የፓርላማ ምርጫ፣ ምንም እንኳን ከእስላም ሊግ ወገኖች፣ ብዙዎቹ የአንድነት ተቃዋሚዎች ባይመረጡም፣ ባንዲራውን ለመሰረዝ፣ የመማከርቶቹን ሁለት ሶስተኛ የድጋፍ ድምፅ ለመሰብሰብ አልተቻለም:: በመጨረሻው ቺፍ ኤግዜኩቲፉ መማክርቶቹን ለማግባባት የተጠቀሙበት መግለጫ የሚከተለው ነበር::

« ..... የኤርትራ ሕዝብ በኮሎኒያሊስት ጣልያን ዘመን ሆነ በእንግሊዞች ጊዜ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ የሆነውን <u>የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ለሠርግም ሆነ ለቀብር ሥርዓት ሲጠቀምበት እንደቆየ የሚዘነጋ የለም::</u> ...... ኤርትራ ወደ እናት አገሯ ወደ ኢትዮጵያ ስትመለስ፣ ለውስጥ አስተዳደሯ የተሰጣት የአቶኖሚ መብት በቂ ሆኖ ሳለ፣ በተጨማሪ የባንዲራ መለዮ የተደረገባት በውጭ ጠላቶች በተዘጋጀ ተንኮል መሆኑን የሚስተው የለም:: ...... የኤርትራ ሕዝብ ክርስቲያኑም ሆነ እስላሙ፣ ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የተለየ ባንዲራ ይቁምልን ብሎ አለመጠ የቁንም የሚክድ የለም:: ...... እንግዲህ በታሪካችን ያልነበረ፣ ከኤርትራ ሕዝብ



ሌፍትናንት ጄኔራል ዐቢይ አበበ፡

በኤርትራ የግርማዊነታቸው እንደራሴ፡ (በፌዴሬሽኑ ዘመን፡ 1960 - 1962)
የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ፡ (ከፌዴሬሽኑ በኋላ፡ 1963 - 1964)

ያልተጠየቀ፣ በጠላቶቻችን ሀሳቡ ተጠንስሶ፡ በጠላቶቻችን ወዳጆች ቀለማቱ ተመርጦ፡ የተሰቀለብንን ባንዲራ በምን ምክንያት ? ለምንስ ጥቅም ? ተሸክመን እንኖራለን ? ..... ይህን ሁሉ በማየት፣ ጥንታዊ ታሪካችንን አድሰን በፍቅርና በሕብረት ተሳስረን ለመኖር እንድንችል፣ የኛ የኤርትራውያኖች ባንዲራ የእናታችን ሰሰቱ ሕብረ ቀለማት፣ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ብቻ እንዲሆን ውሳኔያችሁን እለምናለሁ:: ...... ይህንን ሀሳብ ምክር ቤቱ የማይቀበለው ከሆነ፣ የታሪክ ኃላፊነት ስለአለብኝ የኤርትራ ሕዝብ ራሱ እንዲወስን ሬፈራንደም አዘጋጅቼ እጠይቃለሁ ...... » ብለው ቺፍ ኤግዜኩቲፉ አቋማቸውን ገለጡ:: በፓርላማው መሆኑ ቀርቶ ሕዝቡ እንዲወሰን ቢጠየቅ፣ ደጃች አስፍሐ ጥርጥር የሌለው ድል እንደሚያገኙ ስለታወቀ፣ የእስላም ሊግ ወገኖችም ከመቃወም መደገፉ ይሻላል አሉ::

የአስፍሐ መንግሥት ለሁለተኛ ጊዜ ከተመረጠ፣ ከሶስት ዓመት ከአራት ወር ተኩል በኋላ፣ ታህሣሥ 24 ቀን 1959 ዓ.ም በአውሮፓውያኖች የልደት በዓል ዋዜማ የኤርትራ ፌዴሬሽን ምልክት የሆነው ባለ ሰማያዊ ቀለም ባንዲራ ተሠርዞ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ የሆነው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ብቻ እንዲሆን፣ ፓርላማው ያለ አንዳች ተቃዋሚ በሙሉ ድምፅ ውሳኔውን ሰጠ::

በአገር ፍቅር እሳት እየነደዱ፣ ለፍጹም አንድነት የተሰዉትና ብዙ ፈተናዎችን የተቀበሉት መላከሠላም ዲሚጥሮስ ገብረማርያምና ጓደኞቻቸው፣ በሶስቱ ሕብረቀለማት ያሸበረቀው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ብቻውን በኤርትራ ሕንፃዎች ላይ ሲውለበለብ ሲያዩት፣ ኢትዮጵያዊት ኤርትራ እውነተኛ ልብሷን ያጠለቀችው ዛሬ ነው አሉ:: « .... የታገልነውም የሞትነውም፣ ለእናታችን ለኢትዮጵያ ባንዲራ ነው እንጂ ከውጭ የመጣ ልዩ ምልክት እንዲሰጠፋብን አይደለም ...... » ብለው መላከሠላም ዲሚጥሮስ በ1952 ዓ.ም ሕገ መንግሥቱ በሚዘጋጅበት ጊዜ ያሰሙትን ተቃውሞና ያሳዩትን ቆራጥነት፣ እውነተኛው ታሪክ ምንጊዜም የተከበረ ቦታውን አይነፍገውም::

አስፍሐ ወልደሚካኤልም፣ ይች ለኤርትራ መለዮ እንድትሆን በጠላቶቻችን ተገፍቶ፣ የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር አንሴ ማቴንሶ የፈጠራት ባንዲራ በመሰረዟ፣ ለፍጹም አንድነት ጉዞ የመጀመሪያው ተቀዳሚ እርምጃ አድርገው ቆጥረውታል::

# በኢትዮጵያ ሁለት መንግሥት የለም::

በፌዴራሉ አክት ነጥብ 2 እና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 4 በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተገለጸው " GOVERNMENT OF ERITREA " (የኤርትራ መንግሥት) ሲሆን፣ መሪው ደግሞ በእንግሊዘኛ " CHIEF EXECUTIF " ተብሏል:: የኦፊሴል ቋንቋ በሆነው በትግርኛ፣ የአገሩ መጠሪያ « ናይ መንግሥቲ ኤርትራ » ሲሆን አስተዳዳሪው ደግሞ « ናይ ኤርትራ መራሀ መንግሥቲ » (የኤርትራ መንግሥት መሪ) እየተባለ ሲጠራ ቆይቷል::

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ይህንን የኤርትራ መንግሥትና፣ የኤርትራ መንግሥት መሪ የሚባለውን የመጠሪያ ስም ጨርሶ እንዳልተቀበሉት በሁሉም

ዘንድ የታወቀ ነበር:: እንኳንስ በጽሑፍ በቃል እንኳን ንግግር ሲያደርጉ፣ በተድላም ጊዜ ሆነ አሁን በአስፍሐ፣ « የኤርትራ መንግሥት መሪ » ወይም « ቺፍ ኢግዜኩቲፍ » በሚል አጠራር ተጠቅመው አያውቁም:: ገና ከመጀመሪያው፣ መስከረም ፲፫ ቀን 1952 ዓ.ም የፌዴራሉን አከት ሲያጸድቁ በተደረገው ትልቅ በዓል ላይ፣ አቶ ተድላ ባይሩን በዲስኩራቸው ውስጥ እየደጋገሙ የጠቀሱት «የኤርትራ አስተዳዳሪ» እያሉ ነው::

ንጉሠ ነገሥት ኃይለሥላሴ፣ ተድላ ባይሩን በሚያንከባክቡበት ዘመን፣ ለዚህ የኤርትራ መንግሥት መሪ፣ ለሚባለው መጠሪያ « አስተዳዳሪ » በሚል ቃል ይለውጠዋል ብለው ተስፋ አድርገው ነበር:: ተድላ ግን በታሪካቸው ተዘርዝሮ እንደተገለጸው፣ ይህች « ናይ ኤርትራ መራሒ መንግሥቲ » (የኤርትራ መንግሥት መሪ) የተባለችውን ስም ከዕለት ወደ ዕለት እየወደዷት ስለመጧት፣ የጃንሆይን ፍላጐት ችላ ብለው ከረሙ:: የጃንሆይ ምርት የሆኑት አስፍሐ ግን፣ የጌታቸውን ፍላጐት ደህና አድርገው ስለሚያውቁ፣ ምቹውን ጊዜ ሲያጠኑ ከኖሩ በኋላ፣ ቺፍ ኢግዜኩቲፍ በሆኑ በአምስተኛው ዓመት ያስቡት ተፈጸመላቸው::

« መንግሥቲ ኤርትራ » የተሰኘው የኤርትራ አስተዳደር እንዲባል፣ « ናይ ኤርትራ መራሒ መንግሥቲ » የሚለው የኤርትራ አስተዳዳሪ ተብሎ እንዲሰየም፣ በግንቦት 1960 ዓ.ም ለፓርላማው የቀረበው ረቂቅ ውሳኔ በመሚክርቶቹ ሙሉ ድጋፍ ጸደቀ:: የኤርትራን ባንዲራ እንዲሰረዝ ባስደረጉ በአምስተኛው ወር፣ እነዚህን የስም ለውጦች ሲያስወስኑ፣ አስፍሐ ፕላናቸውን ቀደም አድርገው ለንጉሠ ነገሥቱ አልገለጹም:: ጃንሆይ እንዲያውቁት የተደረገው፣ ጉዳዩ በፓርላማው ጸድቆ ለሕዝብ መገለጫ ከመውጣቱ ከጥቂት ሰዓቶች በፊት ነበር:: ንጉሡ ነገሥቱ ዜናውን እንደሰሙ ወዲያውኑ አስፍሐን በስልክ አስጠርተው፣ « ..... ለመሆኑ ለምን ጉዳይ ይጠቅማል ብለህ ነው ይህንን ያስወሰንከው ? ..... » ብለው ጠየቋቸው:: አስፍሐም ምንጊዜም ቢሆን አስደሳች መልስ ለመስጠት ብልህነታቸው የታወቀ ስለሆነ፣ የጌታቸውን ልብ በሚነካ መንገድ፣ « ..... በኢትዮጵያ ሁለት መንግሥት የለም:: የአንዲት ኢትዮጵያ መንግሥት መሪ ደግሞ አንድ ሰው ብቻ ነው:: እሱም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ይባላል ...... » አሏቸው:: ጃንሆይም « ...... መብሰል ይሉሀል እንደዚህ ነው:: ተረድቶ ስሕተትን ማረም ትልቅ ሞያ ነው ... » በሚል ቃል፣ በጣም መደሰታቸውን ገለጡላቸው::

ደጃዝማች አስፍሐ በአንዲት ኢትዮጵያ ሁለት መንግሥት የለም ብለው ይህን ውሳኔ በፓርላማ ሲያሳልፉ፣ ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ በሕይወት ቆይተው ስምተዋቸው ቢሆን ኖሮ፣ ምን ያህል በመረቋቸው ነበር ? ...... በ1950 ዓ.ም ኤርትራውያኖች ወደ ኢትዮጵያ እንዲቀላቀሉ የተወሰነው፣ የራሳቸው የሆነ መንግሥትና ባንዲራ ተሰጥቷቸው ነው ተብሎ ሲነገራቸው፣ « እንደዚህ ከሆነማ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀሉ ጥቅሙ ምንድን ነው ? » ብለው ላቀረቡት ጥያቄ፣ በዚያን ጊዜ የሚያጠግባቸው መልስ አላገኙም ነበር::

# ሶስተኛው ዘመነ አስፍሐ

## 1960 - 1962

በግንቦት 1960 ዓ.ም « ቺፍ ኤግዜኩቲፍ » በመባል ፋንታ «አስተዳዳሪ» በሚል መጠሪያ የተሰየሙት ደጃዝማች አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ በመስከረም 1960 ዓ.ም ለሶስተኛ ጊዜ ያዘጋጁት ጠቅላላ የፓርላማ ምርጫ በጣም ጥሩ ውጤት ሰጥቷቸዋል:: አዲሶቹ የሕዝብ እንደራሴዎች ክርስቲያኖቹም ሆኑ እስላሞቹ አስፍሐን አድናቂ በመሆናቸው፣ ተወዳጅ አስተዳዳሪያቸውን የመረጧቸው ሁሉም በአንድ ድምፅ ነው:: ስለ ምርጫው አፈጻጸምና ስለ አዲሶቹ የፓርላማ አባሎች መንፈስ፣ ደጃዝማች አስፍሐ ለጃንሆይ የጻፉት ደብዳቤ ሁኔታውን ያስረዳል::

*ግርማዊ ሆይ፤*

*...... በእምነትዎ ረድኤትና በግርማዊነትዎ ውሳኔ፣ የኤርትራ ምክር ቤት አባሎችና የአስተዳዳሪው ምርጫ ይህ ጉዳይ በሚገባ ወግና ማዕረግ ተፈጽሟል:: ...... በማንም ፊት በግልጽ እንደታየውና እንደተመሰከረው፣ የአሁኑ ምርጫ የኢትዮጵያዊነትን መንፈስ እጅግ የተጉናጸፈ ነው:: ከቀበሌ እስከ አውራጃ ውድድሩ ሲደረግ፣ አገሌ ከአገሌ የበለጠ ለንጉሠ ነገሥታችንና ለአገሩ ታማኝ ነው ወይ ? የሚል ጥያቄ እየቀረበ ነበር:: ...... ምርጫው አልቆ በሕጉ መሠረት ፓርላማው እንደተከፈተ፣ መማክርቶቹ እኔን አስተዳዳሪያቸውን የመረጡት፤ የንጉሠ ነገሥታችን ታማኝና ባለሟል ስለሆነ፣ በሙሉ ድምፅ እንቀበለው እየተባለ፣ ያለ አንዳች ተቃዋሚ ከፍ ያለ ጭብጨባ በማስተጋባት ነው:: እንግዲህ ጃንሆይ እንደሚያዩት ሕግና ደንብ ቢጠተሰም፣ ለወግ ማስፈጸሚያ መሣሪያነቱ ነው እንጂ፣ አባሎቹን የመረጡና እኔንም የሾሙ ግርማዊነትዎ ነዎት ለማለት እደፍራለሁ:: ...... ለእምነትና ለግርማዊነትዎ ውለታ መላሽ ለመሆን እንዲያበቃን እየተመኘሁ፣ በራሴና በሥራ ጓደኞቼ ስም፣ በአብራክ ሕሊና እጅግ ጥልቅ ትሑት መሆኔን አደርሳለሁ::*

*ትሑት አገልጋይዎ አስፍሐ ወልደሚካኤል*

ከዚህ በላይ እንደታየው የደጃች አስፍሐ ደብዳቤ ለሶስተኛ ጊዜ አዲስ የተመረጡት የፓርላማ አባሎች ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ያላቸውን ፍቅርና የኢትዮጵያዊነት ስሜት የሚገልጽ ነው::ጃንሆይም የመለሱላቸው፣«... የደከምክበትን ጉዳይ ነዋሪ የሚያደርገው በእኛና በኤርትራ ሕዝባችን መካከል ያለውን ፍቅር በማጉልመሱ ነው ...... » በሚል ቃል ነበር::

የንጉሠ ነገሥቱ ባለሟል፣ ከስምንት ዓመታት በፊት በምክትል እንደራሴነት አሥመራ ከገቡበት ዕለት ጀምሮ፣ ይህ ፌዴራሲዮን የተባለ ነገር ተሰርዞ፣ ከኢትዮጵያ ጋር በአንድ አስተዳደር እንዲጠቃለል ያለ ዕረፍት ሲታትሩ መኖራቸው የታወቀ ነው:: በነሐሴ 1955 ዓ.ም በተድላ ባይሩ ቦታ ሲመረጡ፣ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ፌዴሬሽኑን እንደሚያፈርሱ በሁሉም ዘንድ የሚጠበቅ እንደነበረ ይታወሳል:: አስፍሐ ግን፣ እሥልጣኑ ወንበር ላይ ሲወጡ፣ ነገሩን ሁሉ እውጭ ሆነው እንዳሰቡት አላገኙትም:: በመጀመሪያው የአንድ ዓመትና በሁለተኛው የአራት ዓመት የሥልጣን ዘመናቸው፣ የኤርትራን ባንዲራ ከመሰረዝና የፈረንጅ ቃል የሆነውን ቺፍ ኤግዜኩቲፍ፣ አስተዳዳሪ ብሎ ከመለወጥ በስተቀር፣ ሌላውን መንካት አልቻሉም:: የሁለተኛው የአራት ዓመት የሥልጣን ዘመን ሲጠናቀቅ የተጠበቀው ባለመፈጸሙ፣ ብዙ ሰዎች « ...... አስፍሐም እንደ ተድላ

የፌዴሬሽኑ ሕይወት ሳይስማማቸው አልቀረም ...... » የሚል ትችት መስጠት ጀምረው ነበር። አስፍሐም በበኩላቸው ለተሰነዘረባቸው ወቀሳ መልስ ከመስጠት አልተቆጠቡም። « ..... አስፍሐ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ ሥልጣን ላይ ወጥቶ አምስት ዓመት ሙሉ ምንም ሳይሠራ ተኝቷል ...... » እያሉ፣ የሚያሙኝ ሁሉ ጨዋነትና አርቆ ተመልካችነት የተሳናቸው ናቸው። በዚህ በአምስት ዓመት ውስጥ በእኔ መሪነት የተፈጸመው ሥራ፣ ኢትዮጵያዊት ኤርትራ ከእናቷ በምንም ያልተለየችና የማትለይ መሆኗን ያረጋገጠ ነው። አስፈላጊውን ድርጅት ሳያሟሉ፣ ፌዴሬሽኑን አፍርሶ መበረቅ ቁም ነገር አይደለም። ሕዝቡንና አስተዳደሩን አቀራርቦ ኢትዮጵያዊነትን መገንባት ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው። አንድ ትልቅ ሥራ ፍሬ ሊሰጥ የሚችለው፣ ከሥር ከመሠረቱ ሲገነባ ነው እንጂ፣ ከቁንጮው ሲጀመር አይደለም ...... » በማለት፣ ደጃዝማች አስፍሐ ወቀሳውን ሁሉ ለመደምሰስ ሞክረዋል።

ይሁን እንጂ ነገሩ ወደ ኋላ ተመልሶ ሲታይ በተድላ ባይሩ ጊዜ፣ የፌዴሬሽኑ አስተዳደር በቆየ መጠን ሕዝቡ እየተላመደው ይሄድና አንድ ቀን ይፍረስ ሲባል፣ መብቱ እንደተነካበት ቆጥሮት ችግር ሊፈጥር ይችላል እያሉ፡ ማስጠንቀቂያ ይደራርቡ ከነበሩት ሰዎች ዋናው ተቀዳሚ፣ ደጃዝማች አስፍሐ መሆናቸው ይታወሳል። ዛሬ ግን ፌዴሬሽኑ ሳይፈርስ መቆየቱ ኢትዮጵያዊነትን በይበልጥ ለማዳበርና፣ ከእናት የተለየ አስተዳደር የፈጠረውን ጉዳት፣ የኤርትራ ሕዝብ እንዲኰንበው ለማድረግ አስችሎናል ብለው ሲናገሩ፤ የትናንቱን ዲስኩራቸውን አስታውሶ መልስ የሰጣቸው የለም። አስፍሐ ወልደሚካኤል በተድላ ባይሩ አንፃር፣ ሠላምና መልካም ዕድል ያልተለያቸው ሰው ናቸው። ተድላ በስስቱ ዓመታት የሥልጣን ዘመናቸው እንደታየው፣ ከፖለቲካ ዘዴ እጥረት ጋር ብስጩና ቁጡ በመሆናቸው፣ ለጠላቶቻቸው ጥቃት ምቹ ነበሩ። አስፍሐ ግን ከንጉሠ ነገሥቱ ያገኙት ባለሟልነት፣ ከአንድነት ወገኖች ጋር የመሠረቱት መቀራረብና መልካም ወዳጅነት፣ በጠቅላላውም ከፓርላማው አባሎች ጋር የፈጠሩት መግባባትና መተማመን፣ ለጠላት ወይም ለተቃዋሚ ዕድል የሚሰጥ አልሆነም።

በታህሣሥ 1960 ዓ.ም ከመንግሥቱ ንዋይ ኩ ዴታ ጥቂት ቀን ቀደም ብሎ፤ ወደ ብራዚል ባመራው የንጉሠ ነገሥቱ ኦፊሴላዊ ጉዞ፣ ባለሟል አስፍሐ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የክብር ተከታይ ሆኑ። በዚህ በብራዚል ጉብኝት ላይ ባልታሰበ ቀን፣ የጃንሆይ መንግሥት በታማኞቻቸው በብሪጋድየር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ የተገለበጠ መሆኑ ሲሰማ፤ ደጃዝማች አስፍሐ ምን ዕድል ገጠመኝ ? ብለው ተጨንቀው ነበር። ደግነቱ፣ ጭንቁና ሥጋቱ ብዙ አልቀጠለም። በሶስተኛው ቀን ንጉሠ ነገሥቱ ከመናገሻ ከተማቸው ተመልሰው ዙፋናቸውን ያዙ።

የካቲት 14 ቀን 1961 ዓ.ም፣ ኩዴታውን ከጄኔራል መርዕድ መንገሻ ጋር ሆነው ያፈረሱት ዐቢይ አበበ፣ ሌፍተናንት ጄኔራል በኤርትራ የጃንሆይ እንደራሴነቱን እንደያዙ፤ የአገር ግዛት ሚኒስትር ሲሆኑ፤ ዕድለኛው አስፍሐም በዚያኑ ዕለት የቢትወደድነት ማዕረግ ተሰጣቸው። በዚህ ብቻ አልበቃም። ጄኔራል ዐቢይ በመንግሥቱ ንዋይ ኩ ዴታ የተናጋው የጃንሆይ መንግሥት እስኪረጋጋ ድረስ፤ በአገር ግዛት ሚኒስትርነት ለአንድ ዓመት አዲስ አበባ በቆዩበት ጊዜ፤ ቢትወደድ አስፍሐ በኤርትራ የንጉሠ ነገሥቱን እንደራሴነት ሥራ በተጠባባቂነት እንዲመሩ ተደረገ።

# የፌዴሬሽኑ መፍረስ አስፈላጊ ነበር።

አሰፍሐ ወ.ሚ

በአርእስቱ በተጠቀሰው ጉዳይ በተለያዩ ጊዜያቶችና በተለያዩ ሥፍራዎች፣ ከቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል ጋር በረዥሙ ተነጋግሬአለሁ። በተለይ በአዲስ አበባ እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር በነሐሴ ወር 1993 ዓ.ም ላቀረብኩላቸው ልዩ ልዩ ጥያቄዎች በሰፊው አብራርተው የገለጹልኝ አስተያየቶች የሚከተሉት ናቸው።

<u>ጥያቄ-</u>

ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ለብዙ ዓመታት ያ ሁሉ ጥረት የተደረገው፣ ለሕዝቡም ሆነ ለመንግሥት ምን ጥቅም ይስጣል ተብሎ ነው ?

<u>መልስ-</u>

የፌዴራሲዮኑን መፍረስ አስፈላጊነት ደህና አድርጐ ለመረዳት ከአገሩ ታሪክ ጋር እያይዞ መመዘን ያስፈልጋል። ....... የኤርትራ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ በሆነው በረዥም ታሪኩ ውስጥ፣ በተለያዩ ጊዜያቶች በውጭ ጠላት የተጠቃና መከራን ሲቀበል የኖረ መሆኑን መዘንጋት አይቻልም። የአገሩ የጂዎግራፊ አቀማመጥና በተለይም የባሕር በር ያለው መሆኑ ስለአመቻቸ፣ ከሌላው ኢትዮጵያ ክፍል የተደራረበ ጥቃት የደረሰበት የኤርትራ ሕዝብ ነው። ከአሥራ ስድስተኛው መቶኛ ዓመት ጀምሮ ለሶስት ክፍለ ዘመናት ያህል ቱርኮች ምፅዋን ይዘው የቆላውን ሕዝብ በማስጨነቅና በማስገበር በደል ሲፈጽሙበት ኖረዋል። ከአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ ደግሞ፣ ኮሎኒያሊስት ጣልያን መላው ኢትዮጵያን ለመውረር በነበረው ሰፊ ዕቅድ፣ መጀመሪያ እግሩን ለማስገባትና ጦሩን ለማዘጋጀት የቻለው ምፅዋን ይዞ ነው። ከዚያም መላ ኤርትራን በቅኝ ግዛት ከያዘ በኋላ፣ ወደ ማዕል ኢትዮጵያ ጦሩን አስልፎ ሲገዝ፣ አድዋ ላይ ምኒልክ ቅስሙን ሰብረው አዋርደው መለሱት። <u>በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጣልያን አልገዛም ብሎ ባደረገው ተጋድሎ ታሪካዊ የሆነ ድል ቢጐናጸፍም፣ የመረብ ምላሽ ወንድሞቹን ከቅኝ ገዥው ቀንበር ለማላቀቅ አልቻለም።</u> በዚህ ጉዳይ የትናንትናዎቹም ሆኑ የዛሬዎቹ ታሪክ ጸሐፊዎች፣ « ..... ኢትዮጵያ በታሪኳ ምን ጊዜም ለኮሎኒያሊስት አላደረችም። የሞከራት ጣልያንም ተዋርዶ ተመልሷል .. » እያሉ ሲተርኩ፣ ጣልያን ከእናት አገሯ ነጥሎ በቅኝ ግዛት የያዛት ኤርትራ፣ የኢትዮጵያ አካል መሆኗን ረስተዋል። ከኢትዮጵያ ቤተሰቦች አንዷ የሆነችው <u>ኢትዮጵያዊት ኤርትራ በቅኝ ግዛት ተይዛ መኖርዋ፣ የኢትዮጵያን ነፃነት የተሟላ ሊያደርገው አለመቻሉን፣ የታሪክ ጸሐፊዎች በቸልታ በማለፋቸው የማይወገዙ ናቸው።</u> የኤርትራ ሕዝብ በጣልያን ቅኝ አስተዳደር በኖረበት በሃምሣ ዓመታት ውስጥ፣ ከሌላው ኢትዮጵያ ወንድሞቹ በመለየቱ ሀዘን ቢያጠቃውም፣ ኢትዮጵያዊ ስሜቱን፣ ባሕሉንና ሥርዓቱን ጠብቆ መኖሩ የተመሰከረለት ነው። ጣልያን ከተባረረ በኋላ፣ ከ1941ዓ.ም ጀምሮ በእንግሊዞች ወታደራዊ አስተዳደር በቆየበት ዘመን፣ ምን መሆን ትፈልጋለህ ? ተብሎ ከአንድም ሁለት ጊዜ ሲጠየቅ የአብዛኛው ኤርትራዊ መልስ፣ <u>ኢትዮጵያ ወይ ሞት</u> መሆኑን የሚከድ



ንጉሠ ነገሥት ከኤርትራውያን ባላባቶች ጋር፡ የካቲት 1954

የለም፡፡ ለሁላችንም እንደሚታየን የዴሞክራሲ ትርጉሙ የአብዛኛውን ሕዝብ ፍላጐት መፈጸም ከሆነ፣ አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ሙሉ ኢትዮጵያዊነትን እንጂ፣ በፌዴራሲዮን ተለይቶ መተዳደርን እንኳንስ በውኑ፣ በሕልሙም ታይቶት አያውቅም፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድም ለሰባት ዓመታት ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር የገጠሙት ሙግት ይህንኑ የኤርትራን ሕዝብ ጥያቄ ለማስፈጸም እንደነበረ፣ ሁላችንም እናስታውሳለን፡፡ ነገር ግን፣ የዓለም መንግሥታት ማህበር ዳኝነት የሚካሄደው፣ በኮሎኒያሊስቶችና በጥቁር ሕዝብ ተቀናቃኞች ስለሆነ፣ ለኢትዮጵያ ትክክለኛ ጥያቄ ፍርድ በመንፈግ፣ የአብዛኛውን የኤርትራ ሕዝብ ፍላጐት በመጣስ፣ ኢትዮጵያዊት ኤርትራን ከእናቷ እራርቆ የሚያኖር፣ ይህን ፌዴራሲዮን የተባለ አስተዳደር በግዴታ እንድንቀበል ተፈረደብን፡፡ ይህ ፌዴራሲዮን የተባለው አስተዳደር፣ አንድ ዓይነት ዘር በሆኑት፣ አንድ ዓይነት ባሕልና ታሪክ ባላቸው ሕዝቦች መካከል መለዮ የሚፈጥር በመሆኑ፣ አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ፣ ምን ያህል እንዳዘነና ምን ያህል እንዳለቀሰ የሚያስተውልለት ዳኛ ሳያገኝ ቀረ፡፡

የፌዴራሲዮን አስተዳደር፣ ለሌሎቹ ለኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች፣ ለሸዋው ሆነ ለወሎው፣ ለወለጋው ሆነ ለጐጃሙ፣ ለጐንደሩ ሆነ ለትግሬው፣ ለሐረሩ ሆነ ለከፋው ተዋቅሮ የሚሠራበት ቢሆን ኖሮ፤ የኤርትራ ሕዝብ ልዩ ነገር ተደረገብኝ ብሎ አያዝንም ነበር፡፡ ...... በአንዲት ኢትዮጵያ የሚያምንና፣ በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ ሕዝብ፣ ሠላምና ፀጋ ሊያገኝ የሚችለው፣ በአንድ አስተዳደር ተዋህዶ የአገሩን ደስታ ሆነ ችግር፣ ከወንድሞቹ ጋር እኩል የመካፈል ዕድል ሲኖረው ነው እንጂ፣ ተለይቶ የራሱን ጉዳይ ለራሱ ብቻ እሳቢ ሲሆን አይደለም፡፡ እኛም የኢትዮጵያዊት ኤርትራ ልጆች የተዋጋነውና የተሰዋነው ለኢትዮጵያዊነትና ለአንድነት ስለሆነ፣ ይህን ሳንወድ በግድ የወደቀብንን የፌዴራሲዮን አስተዳደር ማፍረስ ተግባራችን ብቻ ሳይሆን ግዴታችንም ነበር፡፡ ...... የፌዴራሲዮኑን አስተዳደር ለመሰረዝ ስንወስን፣ <u>እነዚህን የዘረዘርኳቸውን መሠረታዊ የሆኑ ታሪካችችንን እና፣ የሕዝቡን ፍላጐት በመመርኮዝ ብቻ ሳይሆን፣ በውጭ ጠላቶቻችንም በኩል የሚጠመድብንን አደጋ ለመከላከል አስበንበት ነው፡፡</u>......

..... ኤርትራ የእስላም አገር ነች እያሉ ዓረቦች በኮሎኔል ናስር መምህርነት ሽፍታ በማሠልጠን፣ መሣሪያ በማስታጠቅ፣ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል የሚያደርጉት የጠላትነት ሥራ በየቀኑ እየከፋ መጣ፡፡ ጃንሆይም በ1959 ዓ.ም እና በ1961 ዓ.ም የግብጹን ዲክታተር ኮሎኔል ናስርን ሁለት ጊዜ በማነጋገር የዲፕሎማሲ ጥረት ቢያደርጉም፣ ምንም ለውጥ ሳይመጣ ቀረ፡፡ በተለይ ኋላቀር የሆኑት የነዳጅ ዘይት ሀብት ያስከራቸው ዓረቦች፣ ኤርትራን በሀይማኖት መሣሪያ ከኢትዮጵያ ለመገንጠ ል የሚያፈሱት ገንዘብ ወሰን አጣ፡፡ ኢትዮጵያ እነዚህን ጠላቶቿን ለመቋቋም፣ የግዛቶቿንና የሕዝቦቿን አንድነት ከማጠንከር በስተቀር ሌላ ምርጫ እንደሌላት የታወቀ ሆነ፡፡ እንግዲህ እኛም በግዴታ ዓረቦች ናችሁ ተብለን ሤራ የሚዘጋጅብን ኤርትራውያኖች፣ ፌዴሬሽኑን አፍርሰን ከእናታችን ከኢትዮጵያ ጋር ሙሉ መዋሀድ ካደረግን በኋላ፣ ዓረቦች በገንዘብ ኃይል እስቲ ከእናታችን እጅ ፈልቅቀው ሲወስዱን እናያለን ? ብለን ቆረጥን፡፡

ጥያቄ-

ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ፣ በተለይ እርስዎ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የተቀበሉት አደራና መምሪያ በምን መልክ ነበር ?

መልስ-

መቸም የጃንሆይን መልካም ፈቃድ ሳንቀበል፣ በኛው ኃላፊነት ብቻ ፌዴሬሽኑን አፍርሰናል ብለን ብንፎክር የሚያምነን የለም:: ሀሳባችንን ለመፈጸም መልካም ፈቃዳቸውንና አባታዊ ምርቃታቸውን መቀበላችንን አንክድም:: ሆኖም የማፍረሻውን ቀበብ ስናዘጋጅ፣ በእኛ በኩል ጃንሆይን ምክር ስጡን ብለን አለመጠየቃችንን፣ ጃንሆይም በውስጥ ሥራችን ገብተው መምሪያ አለ መስጠታቸውን ስንናገር መታመን አለብን:: በዚህ ጉዳይ ብዙ ሰዎች የተሳሳቱትን ማረም ያስፈልጋል:: ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ «ፌዴሬሽኑን አፍርሱ» ብለው፣ ለማናችንም በቀጥታ ትእዛዝ ሰጥተው አያውቁም:: እርግጥ የፌዴሬሽኑን አስተዳደር እንደማይወዱት ሁላችንም በትክክል እናውቃለን:: በደጃች ተድላ ጊዜ አውጥተው ባይናገሩትም፣ የፌዴሬሽኑ አሠራር እየጐላ መሄዱ አስግቷቸው እንደነበረ ሁላችንም አይተናል:: በዚህ ጉዳይ ጭንቁ ተቃሎላቸው ሠላም ሊያገኙ የቻሉት እኔ ከተመረጥኩ በኋላ ነው:: በቅርብ ስለሚያውቁኝና ስለሚያምኑኝ፣ ጊዜው ሲያመች ፌዴሬሽኑን አስርዤ ፍጹም መዋሀድ ለማስደረግ እንደምችል የተረጋገጠ ተስፋ ነበራቸው:: ይሁን እንጂ ስለ አፈራረሱ ዝግጅትና አፈጻጸም፣ ኃላፊነቱን ለእኔ ከመተው በስተቀር በዝርዝር ጉዳይ ገብተው፣ አንድም ጊዜ ይኸ ይሁን፣ ይኸ ይደረግ፣ ይኸ ይቅደም ይኸ ይከተል የሚል መምሪያ ሰንዝረው አያውቁም:: ሌላው ቀርቶ ፌዴሬሽኑ በሚፈርስበት ዕለት ለፓርላማ የምሰጠውን መግለጫ እንኳን አላማከርኳቸውም:: ... በጠቅላላው እኛ ኤርትራውያኖች ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ የቆረጥነው፣ የጃንሆይ ትእዛዝ ሳይጫነን፣ የሀሳቡ ባለቤቶች እኛው ራሳችን ሆነን፣ የሕዝብ እንደራሴዎች መክረውበትና ሙሉ ስምምነት ተደርጐበት ስለሆነ፣ በሠራነውና በፈጸምነው እንኮራበታለን::

ጥያቄ-

ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ በፌዴሬሽኑ መፍረስ ጉዳይ ምን አስተያየት ነበራቸው ?

መልስ-

ጸሐፌ ትእዛዝ አክሊሉ የኤርትራ ፌዴሬሽን መፍረስ የለበትም ብለው ሲሞግቱን የቆዩ ናቸው:: ነገር ግን እኛ አንድነቶች አሸንፈን የሕዝቡን ፍላጐት ስንፈጽም፣ እሳቸው ተቃዋሚነታቸውን በመቀጠላቸው አዝኜባቸው እኖር ነበር:: ያዘንኩትም፣ ለኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ በዓለም ማህበር በብርቱ የተዋጉና ብዙ የሚያኮራ ሥራ የፈጸሙ ሲሆኑ፣ በመላው የኤርትራ ሕዝብ እንደራሴዎች ሙሉ ድምፅ ፌዴሬሽኑን ስርዘን አንድነቱን ስናዋህድ፣ ለዲፕሎማሲ እንኳን ብለው የደስታችን ተካፋይ ባለመሆናቸው ነው:: ፌዴሬሽኑ በፈረሰበት ዕለት፣ ከልዑል አልጋ ወራሽ፣ ከፓትርያርኩ፣ ከመሣፍንቱ፣ ከሚኒስትሮቹ፣ ልዕልቶቹም ጭምር « ..... እሰፍሐ እንኳን ድካምህ ፍሬ ሰጠ:: እንኳን ሁላችንንም ደስ አለን ...... » የሚል የደስታ መግለጫ ሲያጐርፉልኝ፣ ከኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አንዲት ቃል

አልደረሰኝም። በዚህ በጣም ቅር ብሎኝ ለጄኔራል ዐቢይ ሳጫውታቸው፣ የሰጡኝን አስተያየት ምን ጊዜም አልረሳውም። « ..... ቢትወደድ ! አሉኝ ....እጅግም ጸሐፊ ትእዛዝን አይቀየሟቸው። እኔ በሰፊው አነጋግሬአቸዋለሁ። እሳቸው <u>የፌዴሬሽኑ መፍረስ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ብዙ ጣጣ ያስከትላል። የውጭም ጠላት ያጠቃናል</u> ብለው ያምናሉ። እርስዎና እኔ ደግሞ የኢትዮጵያ አንድነት ሲጠነክር፣ <u>በውስጣችን ሠላም ለመመሥረት፣ ከውጪ ለሚመጣብን ጠላት ለመመከት፣ ያስችለናል እንላለን።</u> በጸሐፊ ትእዛዝና በእኛ መካከል ባለው ልዩነት፣ <u>መጨረሻው እውነቱ የማን እንደሆነ፣ ጊዜና ታሪክ ወደፊት ይገልጠዋል።</u> ..... አሁን ሁላችንም በየዕምነታችን መቆም ነው እንጂ፣ ቅያሜ አያስፈልግም ..... » አሉኝ። የጄኔራል ዐቢይ አስተያየት በጣም ነካኝ። የፍርድ ሚኒስትር ተብዬ ከሁለት ወር በኋላ አዲስ አበባ ስሄድ፣ በልቤ ይዤው የነበረውን ቅሬታዬን ለጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ አልገለጥኩላቸውም። በተገናኘን ጊዜ የሞቀ ሰላምታ ከመለዋወጥ በስተቀር፣ ስለ ፌዴሬሽኑ አፈራረስ፣ አሁን ስለአለው ሁኔታ፣ ወደፊትም ምን እንደሚሻል፣ እሳቸውም ሳይጠይቁኝ እኔም ሳልናገር እንደዚሁ ቀረ።

<u>ጥያቄ-</u>

ጄኔራል ዐቢይ የተናገሩት የሚደነቅ ነው። በሰለጠነው ዓለም ለአገርና ለሕዝብ አስተዳደር በሚሰለፉ የፖለቲካ ሰዎች መካከል፣ የሀሳብ ልዩነት መኖሩ የማይቀር ነው። በሀሳብ የሚለያዩ ሰዎች በግል አይቀያየሙም። በኤርትራ ጉዳይ ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉን ከርስዎ የተሻለ የሚያውቃቸው የለም። በዚያ በትግሉ ዘመን ከእሳቸው ጋር በቅርብ ሠርተዋል። <u>በርስዎ ትክክለኛ አስተያየት፣ ለምን ይመስልዎታል ?</u> አክሊሉ ሀብተወልድ <u>የፌዴሬሽኑ አስተዳደር መነካት የለበትም</u> ብለው እስከ መጨረሻው ሀሳባቸውን ሳይለውጡ የቆዩት ?

<u>መልስ-</u>

ቀደም ብዬ እንደተናገርኩት፣ ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ገና ከድሮው የኤርትራን ፌዴሬሽን እንኳንስ መፍረሱን ይቅርና አንዳንዱ ሕግ ይሻሻል፣ ይለወጥ ብለን ስናቀርብ እንኳን፣ ምክንያት እየፈጠሩ ሲያግዱን የኖሩ ናቸው። ለምሣሌ በደጃች ተድላ ቦታ ተመርጠው ሥራ በጀመርኩ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ፣ አብዛኛዎቹ የፓርላማ አባሎች መክረው ጃንሆይ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ይሹሙልን ብለው ያቀረቡትን ሀሳብ ጠቃሚ አይደለም ብለው ያሳገዱት እሳቸው ናቸው። ከዚያም በኋላ ከዚህ ከፌዴሬሽን አስተዳደር ለመገላገል ከማንም በኩል ሀሳብ ሲቀርብ፣ የአክሊሉ ሀብተወልድን ድጋፍ ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑ የታወቀ ነበር። <u>ጸሐፊ ትእዛዝ፤ የኤርትራ ፌዴሬሽን መፍረስ የለበትም ብለው የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች ብዙዎች ናቸው።</u> በተለይ ሁለቱን ደህና አድርጌ አስታውሳቸዋለሁ። የመጀመሪያው፣ ሱማሌ ከጣልያን የሞግዚት አስተዳደር ነፃ ስትወጣ፣ የኤርትራን ፌዴራሲዮን ሞዴል በማየት ወደ ኢትዮጵያ ለመቀላቀል ሊማርካት ይችላል የሚል ነበር። በ1960 ዓ.ም ሱማሌ ነፃ ስትወጣ፣ እንኳንስ በፌዴራሲዮን ከኢትዮጵያ ልቀላቀል ብላ ልትጠይቅ ይቅርና፣ እንዲያውም አልፋ ተርፋ ከኢትዮጵያ ግዛት እንዲሰጣት ጠያቂ ሆነች። በዚህ በኩል ጸሐፊ ትእዛዝ እንደአሰቡት አልሆነም። ቀጥሎ ደግሞ የሚሰጡት ምክንያት፣ የኤርትራ ፌዴሬሽን

ሬፈራንዶም ሳይደረግ፣ በፓርላማ አባሎች በሚደረግ ስምምነት ብቻ ቢፈርስ፣ የተባበሩት መንግሥታት ያወግዘናል:: ታላላቅ መንግሥታቶች ያጠቁናል እያሉ ነበር:: እኛ እንደ እሳቸው ከሶርቦን (SORBONNES) በሕግ የተመረቅን ባንሆንም፣ ብዙ ተመራምረን የሚጠቅመንን እና የሚጐዳንን ለይተን አውቀናል:: ኸረ ለመሆኑ፣ በ1952 ዓ.ም ይህንን በተባበሩት መንግሥታት የተዘጋጀውን የፌዴሬሽን ሕገ መንግሥት፣ መርምሮ ያጸደቀው ማን ነው ? ተብሎ ቢጠየቅ፣ <u>የኤርትራ ሕዝብ መርጦ የላካቸው የሕዝብ ወኪሎች ናቸው</u> የሚለው መልስ ቁልጭ ብሎ ይቀርባል:: ከአሥር ዓመት በኋላ ደግሞ፣ይኸንን የፌዴራሲዮን ሕገ መንግሥት፣ አልጠቀመንም አልረዳንም ብሎ ያፈረሰው ማነው ? ሲባል፣ <u>አሁንም የኤርትራ ሕዝብ የመረጣቸው የሕዝብ እንደራሴዎች ናቸው</u> የሚለው መልስ ብቅ ይላል:: እንግዲህ የተባበሩት መንግሥታት በየትኛው ሕግና በየትኛው መብቱ ኢትዮጵያን ያወግዛል ? ብለን ስንጠይቅ፣ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር የተሰለፉት የሕግ አዋቂዎች እነ ሥዩም ሐረጐት ጭምር መልስ መስጠት አልቻሉም:: እኛ ግን ገና ከጥንቱ በአመንበት ጸንተን ፌዴራሲዮኑን ስናፈርስ፣ ተደጋግሞ እንደተነገረን ማስፈራሪያ፣ የተባበሩት መንግሥታት አላወገዘንም:: ኃያላን መንግሥታቶችም አላጠቁንም::

<u>ጥያቄ-</u>

በዚህ አኳኋን፣ ስለ ኤርትራ ፌዴሬሽን ጉዳይ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የነበራቸው አቋም፣ ሁሉም ስህተት ነበር ማለት ነው ?

<u>መልስ-</u>

የለም:: ሀሳቤ በትክክል አልተጨበጠልኝም:: ዛሬ እሳቸው በሞት ቀድመውኛል ብዬ እስከዚህ አልዳፈርም:: ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ በታላላቆቹ መንግሥታቶች ዘንድና በዓለም ጉባኤ ላይ ከጠላቶቻችን ጋር ተሟግተው ድል ያመጡትን አክሊሉ ሀብተወልድን ለምን ጊዜውም የማከብር ነኝ:: በእሳቸውና በእኔ መካከል የተፈጠረው ልዩነት ፌዴሬሽን ይሰበር አይሰበር ነው:: እሳቸው የፌዴሬሽኑ አስተዳደር መኖር የሁለቱን ሕዝቦች ፍቅርና አንድነት አይቀንሰውም የሚል ዕምነታቸውን ሳይለውጡ አልፈዋል:: እኔ ደግሞ በእናትና ልጆች መካከል፣ ለእናት ለብቻ፣ ለልጅ ለብቻ፣ መተዳደሪያ ሕግ መኖር የለበትም ብዬ፣ የሠራሁትንና ያመንኩበትን ሳልለውጥ ይህን ዓለም ለመልቀቅ ቀኔን እጠብቃለሁ:: ......

<u>ጥያቄ-</u>

ጄኔራል ዐቢይ፣ እርስዎ ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉን እንዳይቀየሟቸው ምክር ሲሰጡ፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩና በእናንተ መካከል ላለው የሀሳብ ልዩነት፣ እውነት እማን ዘንድ እንደሆነ ወደፊት ታሪክ ይገልጠዋል ብለዋል:: ጄኔራል ይህንን የተናገሩት በኅዳር 1962 ዓ.ም ነው:: ዛሬ ከሠላሳ ዓመታት በኋላ ኤርትራ ነፃ መንግሥት ሆና ከኢትዮጵያ ስትገነጠል፣ ጄኔራልና ጸሐፊ ትእዛዝ በሕይወት ባለመኖራቸው አላዩም:: እርስዎ ግን ታሪኩን ከመሠረቱ ሲመለከቱት፣ አክሊሉ ሀብተወልድ ፌዴሬሽን

**እንዳይፈርስ ያለማቋረጥ የታገሉት፣ ዛሬ የደረሰው ሁኔታ እንዳይደርስ አስበው ይመስልዎታል ወይ ?**

መልስ-

ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ እንደነበራቸው ሀሳብ ፌዴሬሽኑ ባይፈርስ ኖሮ የኤርትራ ጉዳይ እስከ ነፃነት አያመራም ነበር የሚሉ ብዙ ሰዎች መኖራቸውን አውቃለሁ:: ይቅርታ ይደረግልኝ እና እኔ በዚህ አላምንም:: እዚህ ላይ አንድ ነገር አተኩሮ ማየት የሚያስፈልገው ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ነፃነቷን ያወጀችው፣ ፌዴሬሽኑ ከፈረሰ ከሠላሳ ዓመታት በኋላ መሆኑን ነው:: በነዚህ በሠላሳ ዓመታት ውስጥ ምን ስህተት ቢደረግ ? ምን በደል ቢፈጸም ? ኤርትራውያኖች ከእናታቸው ከኢትዮጵያ መለየትን መረጡ ? ብሎ ማጥናት ያስፈልጋል:: ..... ለማናቸውም በእኔ በኩል የምሰጠው አስተያየት የታሪክ ተመራማሪ ይፍረደው፣ ተመልካች ይተቸው ብዬ ነው:: እኔ በሠራሁት እምነቴ የጸና ነው:: በዘመኔ የደከምኩበት ሁሉ ለኢትዮጵያ አንድነት ስለሆነ፣ ሕሊናዬ ንጹሕ ነው:: ፈጣሪ ይመስገን እንቅልፍ አልነሳኝም::

ከዚህ በላይ እንደታየው፣ ቢትወደድ አስፍሐ የፌዴሬሽኑ መፍረስ፣ አስፈላጊና ተገቢ ነበር ብለው የሚያምኑበትን ዘርዝረው ሲያስረዱ፣ በእሳቸው በኩል የተወሰደው እርምጃ ለኤርትራ የነፃነት ንቅናቄ መነሻ ሆኗል የሚባለውን አይቀበሉም:: ቢትወደድ ከልባቸው የሚያምኑት፣ የኤርትራ ጉዳይ የተበላሸው ፌዴሬሽኑ በመፍረሱ ምክንያት ሳይሆን፣ ከፈረሰ በኋላ ለአገሩ አስተዳደር የተወሰዱት እርምጃዎች ናቸው ብለው ነው::

## የመፍረሻው ዝግጅት እንዴት ነበር ?

(የአስፍሐ ማስታወሻ)

« ...... ለሶስተኛ ጊዜ አዲስ የተመረጡት የፓርላማ አባሎች ሁሉ፣ የኢትዮጵያዊነት መንፈሳቸው እጅግ የሞቀና በእኔም በአስተዳዳሪያቸው ላይ ሙሉ እምነት ያሳደሩ በመሆናቸው፣ ከዚህ ከፌዴሬሽን ሕግ ለመገላገል ወቅቱ የሚያመች መሆኑ ግልጽ ነበር:: ...... ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ጄኔራል ዐቢይ ለአንድ ዓመት አዲስ አበባ ቆይተው የአገር ግዛት ሚኒስቴርን በሚመሩበት ጊዜ፣ ተጠባባቂ እንደራሴነቱንም ደርቤ እንድሠራ በመደረጉ፣ ፋታ አልነበረኝም:: በእውነቱ የፌዴሬሽኑን ማፍረስ ዝግጅት ሥራዬ ብዬ የጀመርኩት፣ እንደራሴው ወደ አሥመራ ከተመለሱ ከጥር ወር 1962 ዓ.ም ጀምሮ ነው ማለት ይቻላል:: ወዲያውም በየካቲት ወር የግርማዊት እቴጌ መነን እረፍት ሆነ:: ቀጥሎም ሚያዝያ ላይ ልዑል ሣህለሥላሴ ሲሞቱ፣ በዚህ በተደራረበ ሀዘን ሰሞን፣ ብዙ ጉዳዮችን ለማያያዝ አልተመቸኝም ነበር::



ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የሣህል ባላባት የሆኑትን ከንቲባ ያስማንን ሲቀበሉ፣

(ከንቲባ ያስማን የሀገር ፍቅር አንድነት ታጋይ የነበሩ ናቸው::)

...... በግንቦት 1962 ዓ.ም ጃንሆይ ኤርትራን ለመጎብኘት መጥተው በስነበቱበት ጊዜ፣ ስጨነቅበት የቆየሁትን ሀሳብ ወደ ማብሰል ደረጃ ለማድረስ፣ አንዳንድ ነገሮች ተገልጠውልኝ ነበር:: የየዓመቱ ልማድ እንዳይቀርበት፣ ከከባድ ሀዘናቸው ላይ ተነስተው ሊጎበኙት የመጡትን ንጉሠ ነገሥት፣ የሚወዳቸው የኤርትራ ሕዝብ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ፣ በጋለ መንፈስና ፍቅር ተቀበላቸው:: የጊኒው መንግሥት መሪ የሴኩቱሬ አፌሲል ጉብኝትም፣ በአሥመራ ላይ እንዲፈጸም ጃንሆይ ስለፈቀዱ፣ የኤርትራ ሕዝብ እጅግ አድርጐ ተደሰተ:: ቀጥሎም የጃንሆይ መልካም ፈቃድ ሆኖ ከባላምባራስነት እስከ ደጃዝማችነት ድረስ ያለው ልዩ ልዩ የማዕረግ ስም፣ በእኔ አቅራቢነት ለፓርላማው አባሎች፣ ለአገሬ ገዥዎችና ለመንግሥት ሹማምንቶች በርከት ያለ ሹመት ተሰጠ:: ...... በኤርትራውያኖች ላይ በሰሞኑ የሚታየው የኢትዮጵያዊነት ፍቅርና መንፈስ፣ ከወትሮው እጅግ የጋለ ሆኖ በመገኘቱ፣ መላከሠላም ዲሚጥሮስ አንድ የተቀደሰ ሀሣብ ተገለጠላቸው:: « ...... ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በዚህ በኤርትራ ሕዝባቸው መካከል በተገኙበት ሰሞን፣ ፓርላማው ለአንድ ሰዓት ስብሰባ አድርጐ፣ ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ በሙሉ ድምፅ ውሳኔ ቢያደርግና ንጉሠ ነገሥቱ እንዲያጸድቁለት ቢጠይቅ አይሻልም ወይ ? » አሉኝ:: በጥቂት ሰዓቶች ውስጥ ነገሩን ደህና አድርጌ ሳጠናው ሀሳቡ ግሩም ሆኖ ታየኝ:: ወዲያው፣ ከቆለኞቹ ወዳጆቼ ከሼህ ዓሊ ራዳይና፣ ጃንሆይ ከአንድ ቀን በፊት « ደጃዝማች » ብለው ከሾሟቸው ከፓርላማው ፕሬዚዳንት ከሐሚድ ፈረጅ ሐሚድ ጋር ስወያይ፣ የመላከሠላምን ሀሳብ በሁለት ቀናቶች ውስጥ ማዘጋጀት እንደሚቻል ተስማማን:: እዚህ ላይ የፈረንሣይ ተረት ትዝ አለኝ:: « ብረቱ ሲግል በቶሎ መጨፍለቅ ነው » እንደተባለው ይህ ሳናስበው በተዓምር የጋለልን መንፈስ ሳይበርድ፣ ቁም ነገር ብንሠራበት ይሻላል አልኩና፣ መሸት ሲል ከገኔራል ዐቢይ ጋር ሆነን ስጃንሆይ ውጥናችንን ነገርናቸው:: በጥሞና ካደመጡን በኋላ፣ አስበንበት መልሱን ጠዋት እንነግራችኋለን ብለው አሰናበቱን:: እናስብበት ሲሉን፣ ለካስ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉን በስልክ ጠርተው ምን ታስባለህ ? ለማለት ኖርዋል:: እንደተለመደው አክሊሉ ሀብተወልድ የማስረዳትና የማሳመን ልዩ ተሰጥዎ ስላላቸው፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ለወጧቸው::

« ...... እርስዎ ራስዎ ኤርትራ ሄደው ፌዴሬሽኑን እንዲፈርሱት ተቃጥሮ በዓለም ላይ ይወቀሳሉ:: ይኼ ጉዳይ በጣም ከባድ ስለሆነ፣ ጃንሆይ ሲመለሱ ዐቢይና አስፍሐ አዲስ አበባ መጥተው ጥናት ቢደረግ ይሻላል ...... » ይሏቸዋል:: ጃንሆይም በዚህ ሀሳብ ወዲያው ይስማሙና፣ ገኔራልንና እኔን ጠርተው አዲስ አበባ በቶሎ መጥታችሁ ስለቀረበው ሀሳብ ጥናት እንዲደረግ ያስፈልጋል ብለው ትእዛዝ ሰጡን:: እኔ መቸም ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ተከራክሬ የማሻሽለው ነገር እንደሌለ ስለማውቀው፣ ወሬው እንዳይዛመት እንደራሴው ብቻቸውን ሄደው ቢነጋገሩበት ይሻላል ስል፣ ጃንሆይ ቀስብ አድርገው ግለፊያ ነው አሉ:: በሐምሌው መጨረሻ ግድም ይመስለኛል፣ ገኔራል ዐቢይ አዲስ አበባ ሄደው በተደረገው ስብሰባ ላይ ቢሟገቱልንም፣ የኛን ሀሳብ የሚደግፍ ጠፍቶ እንደራሴው ወደ አሥመራ ተመለሱ::

ጥያቄ-

ስብሰባው በምን ደረጃ ተደረገ ? ፌዴሬሽኑ እንዳይፈርስ የናንተን ሀሳብ የተቃወሙት እነማን ነበሩ ?

<u>መልስ-</u>

ጄኔራል ዐቢይ እንደነገሩኝ ጉዳዩ የተጠናው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት ጄኔራል ዐቢይ፣ ጄኔራል መርዕድ መንገሻ የመከላከያ ሚኒስትር፣ አቶ ይልማ ዴሬሣ የገንዘብ ሚኒስትር፣ አቶ አበበ ረታ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር፣ አቶ አብተው ገብረየሱስ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት ሹም፣ ባሉበት ነው:: እንደተለመደው ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ « .... የኤርትራን ፌዴራሲዮን ማፍረስ የኤርትራውያኖችን ኢትዮጵያዊነት የበለጠ ሊያደርገው አይችልም ... » የሚለውን እምነታቸውን ሲናገሩ፣ ሁሉም ደግፈዋቸዋል:: እንዲያውም ጄኔራል መርዕድና አቶ ይልማ፣ የኤርትራ ፌዴሬሽን ሞዴል ለሌላውም ጠቅላይ ግዛት ሊተላለፍ የሚገባ ስለሆነ፣ መፍረስ የለበትም የሚል ሀሳብ ሰጥተዋል ይባላል:: የአቶ አበበ ረታም አስተያየት ከዚህ የባሰ እንደነበረ ሰምቼ ተገርሜያለሁ::

<u>ጥያቄ-</u>

አቶ አበበ ረታ ምን አሉ ?

<u>መልስ-</u>

« .... <u>የኤርትራ ሕዝብ በሕግ ተሰጥቶት ሲጠቀምበት የቆየው፣ አቶኖሚ ሲፈርስበት የበለጠ ኢትዮጵያዊ ይሆናል ..... » ብለው የሚያልሙት ሰዎች የማሰብና የማስተዋል ችግር የተጫናቸው ናቸው ..... »</u> ብለው ሰድበውናል አሉ:: የአቶ አበበ ፊሎዞፊ ከጉዳዩ ቁም ነገር ጋር አብሮ አይሄድም:: በእኛ ወኩል የሕዝብ መብት ይሰረዝ አልተባለም:: እኛ ያልነው፣ የአንድ አገር ፍሬዎች በሆኑ ሕዝቦች መካከል፣ አንዱን ክፍል ከሌላው የሚለይ አስተዳደር እንዲኖር ማድረግ፣ አንድነትን አይጠቅምም ነው:: ይህንንም ያልነው የሕዝቡን ስሜትና ፍላጐት ተመርኩዘን ነው:: ሽማ በየፈርጁ ይለበሳል እንደሚባለው፣ እኔ በዚያች ቀን ተገኝቼ ቢሆን ኖሮ፣ ይህን አለአግባብ የተሰነዘረ ትችት፣ አምጭው መልሶ እንዲወስደው አደርግ ነበር::

<u>ጥያቄ-</u>

የጄኔራል ዐቢይ ሚሲዮን መጨረሻው ምን ሆነ ?

<u>መልስ-</u>

..... መጀመሪያ እንዳልኩት፣ ጄኔራል ዐቢይ ብቻቸውን በመሆናቸው፣ ምንም ሊያደርጉ አልቻሉም:: <u>ከጃንሆይ ጋር በቆይታ በተነጋገሩ ጊዜ፣ በዚህ በፌዴራሲዮን ጉዳይ በጣም አስቸጋሪው ጠቅላይ ሚኒስትሩ መሆናቸውን ተወያይተውበታል::</u> ሆኖም ፌዴራሲዮኑ እንዲሰረዝ ለመፍቀድ፣ ጃንሆይ ብቻቸውን ሆነው ስለተቸገሩ፤ <u>ለጊዜው ይቆይ</u> የሚል ትዕዛዝ ይዘው ተመለሱ::

<u>ጥያቄ-</u>

ከዚያስ በኋላ ?

መልስ -

..... እኔ በጠባዬ እልህ አስጨራሽ ነኝ:: ያሰብኩትን ሳላደርስ ተሸንፌ መንገድ ላይ አልቆምም:: ከመስከረም እስከ ኅዳር መግቢያ ድረስ (1962 ዓ.ም) ከመላከ ሠላም ዲሚጥሮስና ከሌሎቹም ዋና ዋና የአንድነት ሰዎች ጋር ሆነን ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ የምክር ቤቱን አባሎች በሙሉ አስተባበርን:: በፓርላማው ውስጥ አንድም ተቃዋሚ ሳይኖር፣ የሁሉም ስምምነት ከተጨበጠ በኋላ፣ ጄኔራል ዐቢይ አዲስ አበባ ሄደው፣ ውሳኔያችንን ለጃንሆይ ብቻ እንዲያቀርቡልን አደረግን:: ለጃንሆይ ባዘጋጀነው ማስታወሻ፣ « ..... ይህንን ከኢትዮጵያ አካሎች ውስጥ ብቸኛ አድርጐ የሚያሳየንን፣ ፌዴሬሽን የተባለ ሕግ እቁርሰን ሙሉ የአስተዳደር ውህደት ለማድረግ፣ በአኛ በኩል ቁርጥ ውሳኔ ስለአደረግን፤ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችንን መልካም ፈቃድ በአክብሮት እንጠብቃለን:: ይህን፣ ጃንሆይን የምንጠይቀው ፈቃድ በግርማዊነትዎ ብቻ እንዲወሰንልን እንለምናለን:: ...... » በሚል ቃል ስልሣ ስምንት (68) የምክር ቤት አባሎች ተስማምተው ከፈረሙበት ማስረጃ ጋር ለጃንሆይ ተላከ:: ቀኑ በፈረንጅ አቆጣጠር ኅዳር 13 ቀን 1962 ዓ.ም ይመስለኛል:: እንደራሴው ጄኔራል ዐቢይ አበበ በአየር ኃይል ልዩ አውሮፕላን አዲስ አበባ ሄደው፣ በጃንሆይ ቢሮ፣ በር ተዘግቶ ለሁለት ሰዓት ሙሉ ብቻቸውን ከተነጋገሩ በኋላ፣ የጠየቅነው ተፈቅዶ በዚያኑ ዕለት አሥመራ ተመለሱ::

ከዚህ በላይ እንደታየው፣ አስፍሓ ወልደሚካኤል ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ የኤርትራን ፓርላማ አባሎች ትብብር ካረጋገጡ በኋላ፣ ማንም አማካሪ ሳይገባበት ንጉሠ ነገሥቱ ብቻቸውን እንዲፈቅዱላቸው የጠየቁት ተፈጽሞላቸዋል::

በዚህ ጉዳይ፤ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የጠቅላይ ሚኒስትራቸውን አስተያየት ቢጠይቁ፣ ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠንቶ ይቅረብልን ብለው ቢያዙ፣ « ፌዴሬሽኑ መፍረስ የለበትም » የሚል ተቃዋሚ በዝቶ፣ ያሰቡት እንደሚሰናከልባቸው፣ ቢትወደድ አስፍሐ ቀደም አድርገው ተገንዝበውታል::

# ባይ ባይ ፌዴሬሽን

ከ1952 ዓ.ም ጀምሮ ለአሥር ዓመታት በሕይወትና በሞት መካከል ሲያጣጥር የኖረው የኤርትራ ፌዴሬሽን፣ ረቡዕ ኅዳር 15 ቀን 1962 ዓ.ም በከፍተኛ ሥነ ሥርዓት ግብዓተ መሬቱ ተፈጸመ::

ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት ጀምሮ የፓርላማው የመሰብሰቢያ አዳራሽ፣ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አሸብርቆ፣ ወንበሮቹ ተወልውለውና አምረው ይጠብቃሉ:: የሕዝቡ እንደራሴዎች የማዕረግ ልብሳቸውን ለብሰው፣ ታሪካዊውን ውሳኔ ወደሚፈጽሙበት አዳራሽ ሲገቡ፣ ከወትሮው በተለየ አኳኋን፣ ከበር ላይ ሆነው በፈገግታና በጋለ የደስታ መንፈስ የሚቀበሏቸው የፓርላማው ምክትል ፕሬዚዳንት መላከሠላም ዲሚጥሮስ ገብረማርያም ናቸው:: ከስድስት ወራት በፊት ጃንሆይ አሥመራ በነበሩ ጊዜ፣ ከባላምባራስነት እስከ ደጃዝማችነት ድረስ፣

ለኤርትራውያኖች የተሰጠው የማዕረግ ስም እጅግ ብዙ ስለሆነ፣ በተለይ ከስልሣ ስምንቱ (68) የፓርላማ አባሎች መካከል፣ "አቶ" ሆኖ የቀረ ያለ አይመስልም:: መላኩሠላም፣ አቀባበሉን ለማድመቅና ለማሞቅ፣ እያንዳንዱን የሕዝብ እንደራሴ የማዕረግ ስሙን እየጠሩ ሰላምታ ሲሰጡ፣ ቀኛዝማቾቹና ግራዝማቾቹ፣ ተደባልቀውባቸው ነበር::

ምክንያቱ ለምን እንደሆነ ሳይገለጽ በፓርላማው አዳራሽ እንዲገኙ የተጠሩት የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች፣ የከተማው ነዋሪ ታላላቅ ሰዎችና ነጋዴዎች፣ የውጭ አገር መንግሥታት ቆንስሎች፣ የተመደበላቸውን ቦታ ይዘው ይጠባበቃሉ:: በአራት ሰዓት ተኩል የኤርትራ ጠቅላይ አስተዳዳሪ ቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ በስድስቱ የካቢኔ አባሎቻቸው ታጅበው ሥፍራቸውን ሲይዙ፣ በአዳራሹ ስገነት ላይ ያ በሩቁ ጐልቶ የሚታየው የተከበረ ትልቅ ወንበር ባዶ ሆኖ ታየ:: አንድ ትልቅ ሰው ጐድሏል:: ማን እንደጐደለ ለመረዳት የሚሳነው የለም:: መላኩሠላም ዲሚጥሮስ በየሰከንዶቹ ሰዓታቸውን ይመለከታሉ:: አስተናባሪዎች ወዲያና ወዲህ ይሯሯጣሉ:: የቢትወደድ ዲስኩር ይጀመራል ተብሎ በውስጥ ፕሮግራም የታቀደው ሰዓት አለፈ:: ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው በዓሉ ለምን እንደተዘጋጀ የተጠሩት እንግዶች አያውቁም:: አንዳንዶቹ በኤርትራ ባሕር አካባቢ የአሜሪካን ኩባንያ የነዳጅ ዘይት ማግኘቱን ለማብሰር ነው ይላሉ:: ሌሎች ደግሞ አስፍሐ ወልደሚካኤል ራስ ቢትወደድ ተብለው፣ በኤርትራ የጃንሆይ እንደራሴ ሆነው ስለተሾሙ፣ የአስተዳዳሪነቱን ሥልጣን መልቀቃቸውንና ቦታው ለተወዳዳሪዎች ክፍት መሆኑን ለመግለጽ ነው ብለው ያስባሉ:: ከውጭ አገር እንግዶች መካከል፣ የአሜሪካ፣ የእንግሊዝና የፈረንሣይ ቆንስሎች ግን፣ ፌዴሬሽኑ አንድ ቀን እንደሚፈርስ እርግጠኞች ቢሆኑም፣ አፈራረሱ ንጉሡ ነገሥቱ ባሉበት ይከናወናል እንጂ በአስፍሐ ዲስኩር ብቻ ይወሰናል ብለው አይጠብቁም::

- እረ ለመሆኑ ያ የጐደለው ሰው ማን ነው ?
- የፓርላማው ፕሬዚዳንት ደጃዝማች ሼህ ሐሚድ ፈረጅ ሐሚድ ናቸው::
- ምን ደረሰባቸው ?
- ሌሊቱን ታመው አድረው መነሣት አቃታቸው::
- ምን ነካቸው ?
- በግራው ጐናቸው ውጋት ቀስፎ ያዛቸው::
- ዋናው ነገር ቀኙ ጐናቸው ደህና ከሆነ፣ ለግራው መድኃኒት ይገኝለታል .....

በመማክርቶቹ መካከል ሹክሹክታው በዚህ ዓይነት ሲቀጥል፣ አንዲት ግማሽ ገጽ ወረቀት ተጣጥፋ በአንድ አስተናባሪ ለቢትወደድ ቀረበች:: ምን ትሆን ? ቢትወደድ፣ ትክ ብለው አነበቧት:: « ..... አላህ ምስክሬ ነው ትኩሳቱ አይለሁብኝ መነሳት አቅቶኝ ነው:: ትናንት አብሬአችሁ እንደነበርኩት፣ ዛሬም ነገም ከእናንተ አልለይም:: ...... » ይላል:: ፊርማው የደጃዝማች ሐሚድ ፈረጅ ሐሚድ ነው:: ቢትወደድ ለመላኩሠላም አስነበቧቸው:: አስፍሐ ለሕመምተኛው ሲያዝኑ፣ ዲሚጥሮስ ተበሳጩ:: በዚች ታሪካዊ ቀን፣ እያጣጣሩም ቢሆን መገኘት ነበረባቸው አሉ:: ልክ አምስት ሰዓት ሲሆን ቆፍጣናው ቄስ ዲሚጥሮስ በታመሙት ፕሬዚዳንት ቦታ ተተክተው በትግርኛ ቋንቋ « ...... አሁን የኤርትራ ዋና አስተዳዳሪ ክቡር ቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል የሚሰጡትን ከፍ ያለ መግለጫ

እናጻምጥ ...... » ብለው የሊቀመንበሩን ደወል ሲመቱ፣ መማክርቶቹ በአንድነት የቀሰቀሱት ጭብጨባ እየተቀጣጠለ በመላው አዳራሽ ማስተጋባት ጀመረ:: ቢትወደድ ከመናገሪያው መድረክ ቆመው ዲስኩራቸውን እስከጀመሩ ድረስ ጭብጨባው አላቋረጠም ነበር:: አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ የመጨረሻው የኤርትራ ፌዴሬሽን መንግሥት መሪ፣ በፓርላማው ለመጨረሻ ጊዜ ባደረጉት ዲስኩር የገለጹት ሀሳብና፣ የሕዝቡ እንደራሴዎች እንዲያጸድቁት ያቀረቡላቸው ታሪካዊ ውሳኔ የሚከተሉት ናቸው::

« ...... አንድ ሕዝብ የአገሩ ባለቤት ሆኖ፣ በኤኮኖሚና በማህበራዊ ኑሮ በኩል መሻሻል የሚችለው፣ ከሁሉ በፊት የርስ በርስ አንድነቱ ሲጠነክር ብቻ ነው::

...... በአንድ አገር ውስጥ ሁለት የተለያየ አስተዳደር እንዲኖር ሲደረግ፣ በኤኮኖሚም ሆነ በሰላል በኩል፣ ለመሻሻል አስናካይ መሆኑን ሁላችንም እንገነዘባለን::

...... ከንጹሕ ሕዝብ የፈለቀውን ምኞትና ፈቃድ፣ በንጹሕ ሕሊና ሳቀርብላችሁ፣ እግዚአብሔርንና ታሪክን ምስክር በማድረግ ነው:: ......

..... በየጊዜው የሚጐርፍልኝን የኤርትራን ሕዝብ ሀሳብና ምኞት ተመርኩዤ፡ የአሁኑ የአስተዳደር ሁኔታችን ሰው ሰራሽ ከመሆኑ በቀር፣ በታሪካችን ያልነበረና ከሚሰጠው ጥቅም ይልቅ የሚያስከትለው ችግር መብለጡን ተረድቼ፡ የሚከተለውን ሀሳብ ለማቅረብ ከፊታችሁ እገኛለሁ:: እናንተም የሕዝባችንን ምኞትና፣ ያገር ስሜቱን ገላጮች፡ የጥቅሙንና የደህንነቱን ፈላጊዎች፡ የታሪኩ እና የመሠረቱ ጠባቂዎች ስለሆናችሁ፡ በሙሉ ድምፅ እንደምትቀበሉት እተማመናለሁ::

ውሳኔ - ሞሽን

...... የፌዴሬሽን አስተዳደር ስሙም ሆነ ግብሩ፣ ከታሪካችንና ከባሕላችን የራቀ፣ ለጠላት መግሪያ ከመሆኑ በቀር፣ ለሕዝባችን የማይጠቅም መሆኑን ተረድተን፣ ለሀገራችን የመሻሻል እርምጃ፣ ኃይላችንን ሁሉ በአንድነት አስተባብሮ መሥራት ሲገባ፣ በድጋሚ አንድ የሆኑ ድርጅቶች በሁለት ቦታ ማቋቋም፣ በስሙም ሆነ በሀብት ረገድ ከንቱ ማባከን ማስከተሉን ተገንዝበን፣ ...... አንድ ኢትዮጵያ የሆነ ሕዝብ፣ ሰው ሰራሽ በሆነው ባዕዳዊ ድርጅት መመራት አንድነቱን ከመሠረቱ የሚጐዳው መሆኑን ተረድተን፡ ...... የሕዝባችንን ሀሳብና ምኞት ገላጮች ሆነን፡ ፌዴሬሽን የተባለውን ስሙንም ግብሩንም ከላያችን ላይ እንስተነዋል:: ...... ከዛሬ ጀምሮም ከእናታችን ከኢትዮጵያ ጋር በሙሉ አስተዳደር ተዋህደናል::

የመጨረሻው የኤርትራ ፌዴሬሽን መንግሥት መሪ፣ ..... ከዛሬ ጀምሮ ከእናታችን ከኢትዮጵያ ጋር ...... የሚለውን ቃል ተናግረው ሳይጨርሱ፣ በአዳራሹ ውስጥ የፈነዳው ጭብጨባና ጩኸት ሕንፃውን ያናጋው ይመስል ነበር:: መላከሠላም ዲሚጥሮስ ከፕሬዚዳንቱ ወንበር ብድግ ብለው መማክርቶቹ ማህል በመግባት፣ አንገት ለአንገት እየተቃቀፉ ከደስታ ብዛት የመነጨ እንባቸውን ሲረጩ፣ ሌሎች ደግሞ ከመቀመጫ ቸው እየተነሱ ቢትወደድ አስፍሐን ለመሳም ሲረባረቡባቸው ይታይ ነበር:: ለሠላሣ ደቂቃዎች ያህል ፓርላማውን ያጥለቀለቀው የደስታ ማዕበል ትንሽ መብረድ ሲጀምር፣ የዕለቱ ሊቀመንበር መላከሠላም

ዲሚጥሮስ ገብረማርያም፣ ወደተከበረው ወንበራቸው ተመልሰው፣ ስለ ፌዴሬሽኑ መፍረስ የቀረበውን ውሳኔ መማክርቶቹ እንዲያጸድቁት ሲጠይቁ፣ ሁሉም «ተቀብለናል» የሚል ጩኸት ከማሰማት በስተቀር አንድም ተቃዋሚ አልቀረበም:: በዚህ አኳኋን ረቡዕ ኅዳር 15 ቀን 1962 ዓ.ም የኤርትራ ፓርላማ የመጨረሻ አገልግሎቱን የሚሰጠው፣ « ኤርትራ ከእናቷ ከኢትዮጵያ ጋር ሕይወቷን እዋህዳ እንድትኖር ፌዴሬሽኑን ማፍረስ ነው » ተብሎ ተወሰነ::

ፓርላማው ይህን ውሳኔ ካሳለፈ በኋላ፣ መማክርቶቹና የአስፍሐ ካቢኔ አባሎች፣ በእንደራሴው በጄኔራል ዐቢይ አበበ አማካይነት ንጉሠ ነገሥቱ እንዲያጸድቁላቸው ለመጠየቅ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሄዱ:: እንደሚታወቀው ማንኛውም ነገር ቀደም ብሎ የተዘጋጀ ስለሆነ፣ ከአዲስ አበባ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሚሰጡት መልስ ጊዜ አልወሰደም::

« ..... ፌዴሬሽኑ ለአሥር ዓመታት ሲሠራበት ያስከተለውን ጉድለት በመመልከት፣ የኤርትራ ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ወንድሞቹ ጋር በፍጹም ተዋህዶ እድገቱን ለማፋጠን እንዲችል፣ በእንደራሴዎቹ በኩል ያቀረበልንን ውሳኔ አጽድቀን በሥራ ላይ እንዲውል ፈቅደናል ..... » ሲሉ፣ አባ ጠቅል የሰጡት መግለጫ፣ የመጨረሻው ውሳኔ ሆኖ፣ ኤርትራ፣ አሥራ አራተኛዋ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛት ተብላ ተሰየመች::

ኅዳር 15 ቀን 1962 ዓ.ም በመላ ኤርትራ « ሙሉ ኢትዮጵያዊነት የተፈጸመበት ቀን » ስለተባለ፣ ከየአውራጃው ግዛት የተመደቡ ያገር ሽማግሌዎች በሕዝቡ ስም ሆነው ደስታቸውን ለንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ለመግለጥ ወደ ቤተ መንግሥቱ እንዲመጡ ተደረገ:: ብዙዎቹ ይህ በድንገት የታወጀው በዓል ትክክለኛ ትርጉሙ ምን እንደሆነ አያውቁም:: ከየመኖሪያ አገራቸው ወደ አሥመራ ሲጓዙ፣ ድሮ ምን ነበርን ? አሁን ደግሞ ምንድን ነው የሆንነው ? እያሉ ሲጠያየቁ ነበር::

ፌዴሬሽኑ ከፈረሰበት ዕለት ጀምሮ ለሶስት ቀናት የእንደራሴው ዋና ሥራ፣ ከልዩ ልዩ ቦታዎች የሚመጡትን ያገር ሽማግሌዎችንና የየድርጅቱን መሪዎች፣ በየተራ እየተቀበሉ የሚያደርጉትን ንግግር ማዳመጥና፣ በጃንሆይ ስም የምስጋና አጭር መልስ መስጠት ነበር:: በጠቅላላው በብዛት የቀረቡት የደስታ መግለጫ ዲስኩሮች ሁሉ ተመሳሳይ በመሆናቸው፣ ከንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ የሚሰጠውም መልስ ለሁሉም አንድ ዓይነት ቃል መሆን ነበረበት:: በዚያን ጊዜ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ተልኬ አሥመራ የተገኘሁት ጋዜጠኛ እኔ ብቻ ስሆን፣ በቴክኒክ በኩል ለሬዲዮ ፕሮግራም የሚያስፈልገውን ሁሉ ለመቅዳትና ለማቀናበር ከእኔ ጋር አብሮኝ የመጣው የቴሌኮሙኒኬሽን ባልደረባ አቶ ተስፋዬ ኃይሌ ነበር::

ይህ በቤተመንግሥቱ የሚካሄደው የደስታ መግለጫ መቀበያ ፕሮግራም በሚፈጸምበት ዕለት፣ ዓርብ ኅዳር 17 ቀን 1962 ዓ.ም እኩለ ቀን ላይ፣ አንድ ቁመናቸውና ጸጉር ልብሳቸው ከፍ የሚማርክ ያገር ሽማግሌ፣ ከእንደራሴው ፊት ቀርበው የማይጠበቅ ኃይለኛ የሆነ ንግግር አደረጉ:: የእዛውንቱ ዲስኩር ከትግርኛ ወደ አማርኛ ይተረጉም ስለነበረ፣ በራሴ ማስታወሻ የያዝኳቸው ዋና ዋና ሀሳቦች የሚከተሉት ነበሩ::

« ...... የዛሬ አሥር ዓመት በዚች ቦታ፣ ለስልሣ ዓመት ተለያይተው የኖሩ እናትና ልጆች ኢትዮጵያና ኤርትራ ተገናኙ ብለን፣ ወሰን የሌለውን ደስታችንን ገልጠን ነበር። ከአሥር ዓመት ጀምሮ ነፃነታችን ተመልሶልን፣ ኢትዮጵያዊ ልብሳችንን ለብሰን፣ በሠላምና በደስታ ለፈጣሪያችን ምሥጋና እያቀረብን ኖርን። ዛሬ ደግሞ ከአሥር ዓመት በኋላ፣ ኢትዮጵያና ኤርትራ በሙሉ ስለተቀላቀሉ መጥታችሁ ደስታችሁን ግለጡ ተባልን። በሕጋችንም ሆነ በባሕላችን፣ የአስተዳዳሪዎች ትእዛዝ ቢከፋም ቢለማም መከበር ስለአለበት፣ ትእዛዙን አክብረን መጥተናል። በምንወክለው ሕዝብና በራሳችን ስም ሆነን፣ ለንጉሠ ነገሥታችን እንደራሴ መግለጥ የምንፈልገው፣ እኛ የምናውቀው ኢትዮጵያና ኤርትራ የተዋሀዱት የዛሬ አሥር ዓመት መሆኑን ነው። <u>በዚያን ጊዜ ቅልቅሉ የተደረገው በከፊል ነው። ሌላ ጊዜ ሙሉ ቅልቅል ተደርጐ ይከበራል ተብሎ አልተነገረንም።</u> እኛም ይህን አሥር ዓመታት ያሳለፍነው በኢትዮጵያዊነት ስሜት ነው። ይኸ ጐደለ ይኸ ቀረ የምንለው ነገር አላጋጠመንም። ....... ነገር ግን፣ <u>ዛሬ አዲስ የተፈጸመ ከዚህ በፊት ያልነበረ የእናትና ልጆች ግንኙነት ተደረገ ብላችሁ፣ ይህን በዓል በማዘጋጀት፣ እናንተ በምታውቁት ምሥጢር ደስ ካላችሁ፣ እኛም ባልተረዳነው ጉዳይ እናንተን እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት አንቸገርም</u> ..... »

ይህ አስደናቂ ንግግር እንደተፈጸመ፣ ስሌሎቹ ሲደረግ እንደነበረው፣ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ መልስ መስጠታቸው ቀርቶ፣ ቢትወደድ አስፍሐና መላከሠላም ዲሚጥሮስ እየተቀባበሉ፣ በትግርኛ ቋንቋ ከአዛውንቱ ጋር ሰፋ ያለ ክርክር ገጠሙ። የሚለዋወጡት ሀሳብ ምን እንደሆነ በትክክል ሊገባኝ ባይችልም፣ ጉዳዩ የጠብ መልክ የያዘ መሆኑ ተሰምቶኛል። ለማናቸውም በዚህ ፕሮግራም ላይ የሚደረጉት ዲስኩሮች ሁሉ በድምፅ መቅጃ ስለሚቀረጹ፣ ተተርጉሞ ዝርዝሩን መረዳት ይቻላል ብዬ ስዝናና እንደራሴው ጠሩኝ። « ...... ወዱ ! ይኸ አሁን የተደረገው ንግግር እንዳይወጣ። በቴፕ ተቀርጾም እንደሆነ ወቶሎ ይደምሰስ ..... » ብለው፣ ከልማዳቸው ውጭ፣ እጅግ ቁጡ በሆነ መንፈስ ተናገሩኝ። በበኩሌ በአሠሩት መሠረት በራዲዮም ሆነ በጋዜጣ እንደማንጠቀምበት ካረጋገጥኩላቸው በኋላ፣ የቴፑን ክር መደምሰሱን ጉዳይ ችላ አልኩት። በመሠረቱ ገኔራል ዐቢይ ትዕዛዝ ባይሰጡኝም፣ በዚያን ዘመን በነበረው የማስታወቂያ ሚኒስቴር አሠራራችን ይህን የመሰለውን ያፈነገጠ ሀሳብ የያዘ ዲስኩር ለሕዝብ አናቀርበውም ነበር። ሆኖም የተደረገው ንግግር ዶክመንት ሆኖ እንዲቀመጥ፣ የተናጋሪውን አዛውንት ስምና የመጡበትን አውራጃ ወይም ወረዳ ማወቅ ፈለግኩ። ወዲያው አጠገቤ የነበሩትን ኮሎኔል አሠጋኸኝን (ኋላ ዳጃዝማች) ጠየቅኳቸው። ...... እርስዎ ደግሞ ደህና ደህና ነገር መስማት ትተው ይኸንን ለምን ይፈልጋሉ ? ...... ብለው ተቆጡ። ትንሽ ተገርሜ ጥያቄዬን ወደ ቀኛዝማች ስለሞን ተክሌ አዛወርኩ። እሳቸውም ጤነኛ ሆነው አላገኘኋቸውም። ..... እኔ ዲስኩር የሚያደርጉትን ሰዎች ስም መዝጋቢ አይደለሁም ..... » አሉኝ። ወዲያው፣ ገኔራል ተድላ ዕቁቢትን ጠጋ ብዬ እባክህ ንገረኝ አልኩት። ...... ሰዎቹ የራቢጣ ወገን የነበሩ ስለሆኑ ዝርዝሩን ደህና አድርጐ የሚያውቀው ኤክስፐርት ተስፋዮሐንስ በርሄ ስለሆነ፣ እሱን ጠይቅ ..... ብሎ አሾፈብኝ። የእንደራሴው ጽሕፈት ቤት ሹም የሆኑትን ልጅ ቂምላቸውን ጠየቅኳቸው። የተናጋሪውን ስም አላውቀውም። የመጡት ከአካለ ጉዛይ ነው። የነ ራስ ተሰማ አስበሮም ወገኖች ይመስሉኛል አሉኝ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፣ በዚያን ሰዓት በሥነ ሥርዓቱ ላይ ያልነበሩት የእንደራሴው ጽሕፈት ቤት የፕሬስ ሹም፣ ወዳጄ ቀኛዝማች ዓለማየሁ ኪዳኔ ከውጭ ሲመጡ፣ የደረሰውን አጫወትኳቸው። እሳቸውም ግዴለም፣ በትግርኛ ቋንቋ ዲስኩሩ ሲደረግ ተናጋሪው የማን አውራጃ ወይም ወረዳ መሆናቸውን ስለሚገልጹ፣ በተቀረጸው ቴፕ ውስጥ

እናገኘዋለን ብለው እርግጠኛ ሆኑ። የዕለቱ ፕሮግራም እንደተፈጸመ፣ ይህንን ተፈላጊ የሆነ ቴፕ ለመውሰድና ለማስተርጐም ስጠይቅ፣ የቤተመንግሥቱ የቴክኒክ ኃላፊ ነው ተብሎ የተመደበ አንድ ከላባ ጣልያን፣ ትእዛዝ ከማን እንደተቀበለ አይታወቅም የተደረገውን ዲስኩር ስርዞት ተገኘ። ወዲያው፣ ወዳጄ ቀኛዝማች ዓለማየሁ ኪዳኑ በጣም ተናደው፣ ጣልያኑ በተንኮል ያደረሰውን ጉዳት ለእንደራሴው አመለከቱ። ጄኔራሉ በቢይ በፈገግታ ካዳመጧቸው በኋላ፣« ..... ይህ መዘዘኛ ዲስኩር መደምሰስ አለበት ብዬ ለዘውዴ ረታ ነግሬው ነበር። ተሰርዞም ከተገኘ ማለፊያ ነው ...... » ብለው የፕሬስ ሹማቸውን ወደ ሥራህ ተመለስ አሏቸው።

የእኝህ የሕዝብ መልዕክተኛ ንግግር ወደ አማርኛ ሲተረጐም እኔ የያዝኩት ማስታወሻ እንደሚያመለክተው፡ የተቃዋሚዎች ሀሳብ ነው ማለት አይቻልም። ከነ መላኩሣም ዲሚትሮስ ጋር የተደረገው የከረረ ክርክርና መፍጨፍጨፍ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ለማወቅ ያደረግኩት ሙከራ አልተሳካልኝም። በሌላ ጊዜ ቢትወደድ አስፍሐን ብጠይቃቸው፡ « ቁም ነገር የሚሰጠው አይደለም » ብለው አሩኩሱብኝ። በእኔ አስተያየት ከንግግሩ ውስጥ አስደናቂ ሆኖ የሚታየው፡ ...... ከአሥር ዓመት በፊት ኤርትራ ኢትዮጵያ ሆነች ተብሎ ያ ሁሉ በዓል ከተደረገ በኋላ፡ ዛሬ ደግሞ በድጋሚ ኢትዮጵያዊ ሆናችኋልና ደስታችሁን ግለጡ ብላችሁ ያዘዛችሁን፡ እናንተ በምታውቁት ምሥጢርና እኛም ባልተረዳነው ጉዳይ ስለሆነ፡«እንኳን ደስ ያላችሁ» የሚለው ቃል ነው። በመሠረቱ አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ የፌዴሬሽኑ መፍረስ በዓል ሲከበር፣ ትክክለኛው ትርጉም ምን መሆኑ እንዳልተብራራለት በዚያን ሰዓት ጉልህ ሆኖ ይታይ ነበር።

ኅዳር 14 ቀን 1962 ዓ.ም ከጠዋቱ በአራት ሰዓት ጃንሆይ ቢሮ ተጠርቼ ስቀርብ፣ « ..... በል አሁኑኑ ተነስተህ አሥመራ ሂድ። በዚያም በቢይና አስፍሐ የሚሰጡህን ሁሉ ሰብስበህ ሥራውን ደህና አድርገህ መፈጸም ነው...... » አሉኝ። የጌቶቹ ትእዛዝ ግልጽ ነው። ነገር ግን አሥመራ ምን እንደተፈጠረ አልገባኝም። ወዲያው ከግቢ ሳልወጣ፣ ወዳጄ አቶ መብዓሥላሴ ዓለሙ በዚያን ጊዜ የግርማዊነታቸው ልዩ ካቢኔ የፕሬስ ዋና ዲሬክተር ቢሮ ሄጄ፣ ለማስታወቂያ ሚኒስትሩ ለበላታ ግርማቸው ተክለሐዋርያት ስልክ ደውዬ ከጌቶቹ የተሰጠኝን ትእዛዝ ነገርኳቸው።

-- ታዲያ እኔ ደግሞ በፋንታዬ ለጌታዬ ምን ልታዘዝ ? አሉኝ።

-- ነገሩ ማሾፍ መሆኑ ቢገባኝም፣ ከቁም ነገሩ እንዳልወጣ አሥመራ ምን እንደደረሰ ጌታዬ እንዲነግሩኝና በተጨማሪ የሆቴል ወጪ እንዲያዙልኝ ነው፣ አልኳቸው።

-- መቸም እንደምታውቀው የእኔ የማስታወቂያ ሚኒስትርነት ለስም ብቻ ነው። የቤተመንግሥቱ ባለሟል አንተ ነህ። የታዘዝከው ለምን ጉዳይ እንደሆነ እዚያው ጠይቀህ መረዳት ነበር እንጂ፣ እኔን ባይተዋሩን በማላውቀውና ባልሰማሁት ጉዳይ ለምን ታስጨንቀኛለህ? ብለው ስልኩን ዘጉት።

የብላታ ግርማቸው ቅሬታ አላስገረመኝም:: እኔ የእሳቸው ጭፍራ ስለሆንኩ፣ ትእዛዙ በእሳቸው በኩል መድረስ ነበረበት:: ይህን የመሰለውም ነገር በየጊዜው የሚደርስ ስለሆነ፣ እንደ አዲስ ሁኔታ አላስጨነቀኝም:: ከቤተመንግሥት በቀጥታ ወደ ቤቴ ሄጄ ሻንጣዬን ሳዘጋጅ ስልክ ተደወለ:: የማስታወቂያ ሚኒስትሩ ናቸው::

« ...... ገነራል ዐቢይን አሁን በስልክ አነጋገርኩት:: የምታርፈው እዚያው እቤተመንግሥቱ ውስጥ ስለሆነ፣ የሆቴል ወጭ የለብህም ብሏል:: ሆኖም ለመጠባበቂያ እንዲሆንህ በሰነድ ተይዞ ኋላ ሂሣቡ የሚወራረድ፣ አምስት መቶ ብር አሁን ይደርስሀል:: ሌላ የማደርገው ነገር ካለ ንገረኝ....» አሉኝ::

-- በጣም ካመሰገንኩ በኋላ፣ አሥመራ ምን እንደደረሰ ጌታዬ ቢነግሩኝ፣ አእምሮዬን ለሥራው ለማዘጋጀት ይረዳኛል አልኳቸው::

-- በእኔ ደረጃ ገነራል ዐቢይን አነጋገሬው ምሥጢር ነው ብሏል:: በአንተ ደረጃ ወደ ላይ ከፍ ብለህ ብትጠይቅ፣ ሳይገለጽልህ አይቀርም ..... ብለው አፌዙብኝ::

-- ለማናቸውም: ጉዳዩ ከፍ ያለ ሳይሆን አይቀርም ብዬ፣ ከቴሌኮሙኒኬሽን፣ በራዲዮ ቴክኒክ እቀናባሪነት ከመልካም ጠባይ ጋር ጥሩ ችሎታ ያለው አቶ ተስፋዬ ኃይሌ አብሮኝ እንዲሄድ ጠይቄ እየተዘጋጀ ነው አልኳቸው::

-- የክብር ተከታይ ያስፈልግህ ኖርዋል ወይ ? አሉኝ::

-- የለም ለሥራው በጣም አስፈላጊ ስለሆነ ነው አልኳቸው::

-- እኔም ያልኩት እኮ በዚሁ መንፈስ ነው:: የክብር ተከታዮች የሚመደቡት በእኔ ግምት ለሥራ ይመስለኛል:: ...... ለማናቸውም ከቴሌኮሙኒኬሽን አብሮህ ሰው እንደሚመጣ ለገኔራል ዐቢይ እነግራለሁ:: ...... የመጠባበቂያውም ገንዘብ አንድ ሺህ ብር እንዲሆን አዝልሃለሁ:: ...... በል እንግዲህ መልካም መንገድ ያድርግልህ:: <u>በአሥመራ ከተማ « "ባይ ባይ ፌዴሬሽን" እያልክ እስክስታውን አሳምረህ ተመለስ ......</u> » ብለው ስልኩን ቶሎ ዘጉት::

ብላታ ግርማቸው ግልጽ የሆነ ፍንጭ ሰጥተውኝ ነበር:: በመጀመሪያ ደረጃ ግልጽ ሆኖ አልታየኝም:: ለካስ ወደ አሥመራ የምጓዘው፣ የፌዴሬሽኑን ስንብት በዓል ለመተረክ ኖርዋል:: ይህን ምዕራፍ « ባይ ባይ ፌዴሬሽን » ብዬ የሰየምኩት፣ ግርማቸው ተክለ ሐዋርያትን እስታውሼ ነው::

## ክፍል ስምንት

## ከፌዴሬሽኑ በኋላ

## (ጥር - ሰኔ 1963)

ገጽ


4. ፌዴሬሽኑ በፈረሰ ማግሥት .................... 510
5. የተድላ ዕቁቢት ትራጄዲ .................... 517
6. መጨረሻው? .................... 527

# ፌዴሬሽኑ በፈረሰ ማግሥት፤

« ...... መሬቱ የሚቀበለውን ትቶ አራሹ የሚፈልገውን ዘራ ...... »
አ.ወ.ሚ

የኤርትራ ሕገ መንግሥት በሥራ ላይ መዋል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ፣ የአንድነት ወገኖች ያለማቋረጥ ሲታገሉ የኖሩት፣ ፌዴሬሽኑን አፍርሶ አስተዳደሩን ከኢትዮጵያ ጋር ለማዋሀድ መሆኑን ያለፉት ታሪኮች በዝርዝር አስረድተዋል። ለአሥር ዓመታት፣ ያ ሁሉ ጥረት ተደርጐ በመጨረሻው ፌዴሬሽኑን ማፍረስ ከተቻለ በኋላ፣ አስተዳደሩ ከአዲስ አበባ ጋር በምን አኳኋን እንደሚከናወን፣ በሰው ኃይል በኩል ሆነ በሥራ አፈጻጸም ረገድ፣ የሚያስፈልገው ምን እንደሆነ አይታወቅም ነበር።

ወደ ኋላ መለስ ብለን ብንመለከት፣ በመስከረም 1954 ዓ.ም ተድላ ባይሩ « ፌዴሬሽኑ ቢፈርስልኝ ? » የሚል የምኞች ንግግር ባደረጉ ጊዜ፣ ምናልባት አንድ ቀን ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ጨክነው የስነዘሩትን ሀሳብ ቢፈጽሙ፣ ኢትዮጵያ አስተዳደሩን ለመረከብ አልተዘጋጀችም ሲሉ ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ የሰጠ ·ትን አስተያየት ማስታወስ ያስፈልጋል። በዚያች በመስከረም 12 ቀን 1954 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥቱ ባደረጉት ታላቅ ስብሰባይ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ የፌዴሬሽኑ መፍረስ አይጠቅምም ብለው ሲሟገቱ፣ አብረዋቸው የቆሙላቸው የጽሕፈት ሚኒስትሩ ብቻ ነበሩ። በጉባኤው መጨረሻ ላይ፣ የኤርትራ ሕዝብ ፌዴሬሽኑን አፍርሶ እንዋሀድ ቢል፣ በኢትዮጵያ በኩል አስተዳደሩን ለመቀበል መዘጋጀት ስለሚያስፈልግ፣ በጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ ሰብሳቢነት አንድ የሚኒስትሮች ኮሚቴ እንዲያጠናው ተወስኖ ነበር። በእኔ በኩል እስካሁን ባደረግኩት ምርምር፣ ይኸው የታሰበው ጥናት መደረግ አለመደረጉን ለማወቅ አልቻልኩም። በህዳር 15 ቀን 1962 ዓ.ም የኤርትራ ፌዴሬሽን ሲፈርስ በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በኩል አስተዳደሩን ለመረከብ የተደረገ ጥናትም ሆነ ዝግጅት አለመኖሩ ግልጽ ሆኖ ታይቷል።

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድና አብዛኞዎቹ ሚኒስትሮች፣ የኤርትራ ጉርላማ ፌዴሬሽኑን ያፈረሰ መሆኑን የሰሙት፣ ውሳኔው በንጉሠ ነገሥቱ እንዲጸድቅ በቀረበበት ዕለት ኅዳር 15 ቀን 1962 ዓ.ም ነበር። በጣም ጥቂቶች የሆኑ ሚኒስትሮች፣ ጉዳዩን ቀደም ብለን አውቀነው ነበር እያሉ ቢናገሩም፣ እነሱ ለመስማት የቻሉት የፌዴሬሽኑ አፍራሾች የግልና የቅርብ ወዳጆች በመሆናቸው ነው እንጂ፣ በካቢኔ አባልነታቸው ሊያውቁት ይገባል ተብሎ ተነግሯቸው አይደለም። እንደ ደንቡ ከሆነ፣ የኤርትራን ፌዴሬሽን ለማፍረስ ሲወጠን፣ የንጉሠ ነገሥቱ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊመክርበትና፣ በፖለቲካም ሆነ በአስተዳደር ረገድ ለሚያጋጥሙት ችግሮች፣ መፍትሔዎቹን አስቀድሞ ማዘጋጀት ይገባው ነበር። እርግጥ ነው የኤርትራን ፌዴሬሽን ለማፍረስ፣ ከብዙ ዓመታት ጀምሮ ውስጥ ውስጡን የሚደረገውን ሙከራ አልሰማሁም የሚል ሚኒስትር የለም። ሆኖም ይህን የመሰለው ትልቅ ጉዳይ በምክር ቤቱ እንዲጠና ከንጉሠ ነገሥቱ ካልታዘዘ፣ ጭምጭምታ ተሰምቶ ዝግጅት መደረግ ነበረበት አይባልም። ከኅዳር 15 ቀን 1962 ዓ.ም በኋላ፣ የኤርትራ አስተዳደር እንደ ሌሎቹ ጠቅላይ ግዛቶች በአገር ግዛት ሚኒስቴር ሥልጣን ውስጥ ይቀላቀላል ? ወይስ በንጉሠ ነገሥቱ የሚታዘዝ የተለየ አመራር ይደረግለታል ? ...... የትኛው እንደሆነ

መለየት አልተቻለም። በአሥመራ ከተማ እንድነቶች ያዘጋጁት የፌዴሬሽን ማስናበቻ በዓል በደመቀበት ሰሞን፡ በየጋዜጦቹ ላይ የሚጻፉት ርዕስ አንቀጾች ሁሉ፣ ከኢትዮጵያ ጋር አስተዳደሩ በመዋሀዱ፣ የኤርትራ ሕዝብ የኤኮኖሚና የሰሻል ሕይወት የተፋጠነ ዕድገት ለማግኘት እንቅፋቱ ተወገደለት እያሉ ነው።

ፌዴሬሽኑ ከተሰረዘ ከአንድ ወር ተኩል በኋላ፣ ንጉሠ ነገሥቱ አሥራ አራተኛውን ጠቅላይ ግዛታቸውን ለመጐብኘት አሥመራ ሲደርሱ፣ እንደጠበቁትም ባይሆን፡ ሕዝቡ በየዓመቱ ያስለመዳቸውን መልካም አቀባበል አላጓደለባቸውም። በመስከረም 1952 ዓ.ም የመረብን ወሰን ከደመሰሱ በኋላ፣ ረዥም በሆነ በአውቶሞቢል ጉዞ አሥመራ ቤተመንግሥት እስከደረሱበት ጊዜ ድረስ፣ የኤርትራ ሕዝብ ከልብ የመነጨ ደስታውን የገለጠላቸው፣ በእልልታና በሆታ ብቻ ሳይሆን፣ ፊቱን በእንባ እያራሰ ነበር። ለስልሣ ዓመታት በቅኝ ግዛት አስተዳደር ሲሰቃይ የኖረ ሕዝብ፣ ነፃነቱን አግኝቶ ከአፄ ዮሐንስ ዘመን በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱን ለመቀበል በመቻሉ፣ ለደስታው ገደብ አልሰጠውም። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም፣ በመስከረም 1952 ዓ.ም የኤርትራ ሕዝብ ያሳያቸውንና የገለጠላቸውን የደስታ መንፈስ ጥሩ አድርገው ያስታውሳሉ። ዛሬም ከአሥር ዓመት በኋላ፣ በኤርትራ የነበረው ፌዴሬሽን የተባለው አስተዳደር ተሰርዞ፣ ከኢትዮጵያ ጋር ሙሉ አንድነት በመፈጸሙ፣ ሕዝቡ የበለጠ ተደስቶ የበለጠ ስሜቱን አግሎ ይጠብቀኛል ብለው እባ ጠቅል ተስፋ ሳያደርጉ አልቀሩም። ነገር ግን ሕዝቡ በየመንገዱ ተሰልፎ ንጉሠ ነገሥቱን የተቀበለው፣ የተለመደ አክብሮቱንና ፍቅሩን ለማሳየት ነው እንጂ፣ የፌዴሬሽኑ መፍረስ ትርጉሙና ጥቅሙ ምን መሆኑን ተረድቶ፣ የተለየ ስሜቱን ለመግለጥ አልነበረም። እንኳንስ አብዛኛው ጥሮ አዳሪው ሕዝብ ይቅርና፣ ለእሱ እንወክልለታለን የሚሉት ያገር ሽማግሌዎች እንኳን፣ ፌዴሬሽን በመኖሩ የተጐዳነው እንዴት ነበር ? እሱ ሲቀር ደግሞ የምናገኘው ምንድን ነው ? ብለው፣ እያከታተሉ ላቀረቡት ጥያቄ፣ የሚያጠግብ መልስ አለማግኘታቸውን አልደበቁም።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፡ ኤርትራ አሥራ አራተኛዋ ጠቅላይ ግዛት ሆና ከተሰየመች በኋላ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በሚያደርጉት ጉብኝት፣ ጠቅላይ ሚኒስትራቸውንና ሚኒስትሮቹን አስከትለው በመምጣት፣ እያንዳንዱም ሚኒስትር በሚኖረው ኃላፊነት የአገሩን አስተዳደር ጉዳይ በጥልቅ እንዲረዳው ማድረግ ይጠቅማል ብለው፣ ቢትወደድ አስፍሐ ለጃንሆይ ማስታወሻ አቅርበው እንደነበረ ነግረውኛል። ነገር ግን የአስፍሐ ሀሳብ በንጉሠ ነገሥቱ ስላልተፈቀደ፡ ከንጉሣውያን ቤተሰብና ከተለመዱት የግቢ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖች በስተቀር፣ አንድም የካቢኔ ሚኒስትር የጃንሆይ ተከታይ ሆኖ አስመራ አልሄደም። እንግዲህ ለአዲሱ የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት አስተዳደር፣ የሚያስፈልጉትን ዋና ዋና ባለሥልጣኖች ለመምረጥና ለመደልደል፣ ጃንሆይ ብቻቸውን ይሆናሉ ማለት ነው።

ለፌዴሬሽኑ መፍረስ፣ ከብዙ ዓመታት ጀምሮ የታገሉትና የማፍረሻው መሀንዲሶች፣ ቢትወደድ አስፍሐና መላከሠላም ዲሚጥሮስ ናቸው ቢባልም፣ የጄኔራል ዐቢይ አበበ ትጊነትና መሪነት ለአፈጻጸሙ ወሳኝ መሆኑ የታወቀ ነው። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም ይህን ታሪካዊ ጉዳይ ለፈጸሙላቸው ለእነዚህ ለሶስት ሰዎች እንደየደረጃቸው ምን ዓይነት ሹመትና ሽልማት መስጠት እንዳለባቸው፣ ለጥቂት ቀናቶች ብቻቸውን ማሰቡና መጨነቁ ራስ ምታት ሳይሆንባቸው አልቀረም።

...... ዐቢይ አበበን ከኤርትራ አንስተው አንዱን የካቢኔ ሚኒስትርነት ቦታ ቢሰጧቸው፣ ሹመት ሆኖ እንደማይቆጠር ያውቃሉ:: ጄኔራል ዐቢይ የንጉሠ ነገሥቱ ሚኒስትር መሆንን ከወጣትነት ዘመናቸው ጀምሮ የለመዱት ስለሆነ፣ ከፍተኛ ሹመት ሊሆናቸው አይችልም:: በተለያዩ ጊዜያቶች የጦር ሚኒስትር፣ የፍርድ ሚኒስትር፣በመጨረሻም የገር ግዛት ሚኒስትር ነበሩ:: ስለዚህ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ዐቢይ አበበን በሹመት በጣም ማሳደግ ያስፈልጋል ከተባለ፣ « ጠቅላይ ሚኒስትር » ካልሆኑ በስተቀር ሌላ ከፍተኛ ቦታ የለም:: ይህንን ደግሞ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በጦር ኃይሎች ካልተገደዱ በስተቀር፣ በራሳቸው መልካም ፈቃድ አክሊሉን ሽረው ዐቢይን አይተኩም:: ከዚህ በላይ ደግሞ አንድ መረሳት የሌለበት ትልቅ ነገር፣ ከመንግሥቱ ንዋይ ኩዴታ በኋላ የንጉሠ ነገሥቱን ፕሮቶኮል አጣፍቶ በአንድ ጊዜ እጫፍ የደረሰ፣ የሚደመጥና የሚፈራ ትልቅ ሰው አለ .....
« ሌፍተናንት ጄኔራል መርዕድ መንገሻ የመከላከያ ሚኒስትር » አራት ዲቪዚዮን ጦር እያዘዙ በቀድሞው በራስ አበበ አረጋይ ቢሮ፣ ከሙሉ ልብ ጋር የተመቻቹ ሰው እያሉ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሾም ወደ አሥመራ አያመሩም:: ስለዚህ በዚያን ዘመን የነበረውን ሁኔታ ስንመለከተው፣ የጄኔራል ዐቢይ ጠቅላይ ሚኒስትርነት በብዙ ምክንያቶች የማይታሰብ ስለሆነ፣ የመጀመሪያው የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት እንደራሲ ብሉ፣ እዚያው እነበሩበት እንዲቆዩ ከማድረግ በስተቀር፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ሌላ መንገድ አልነበራቸውም:: ጄኔራል ዐቢይም በዘመኑ የነበረውን ሁኔታ ደህና አድርገው ስለሚያውቁት በዚያን ሰዓት ከጃንሆይ የሚጠብቁት የተለየ ሹመት አልነበረም::

ሁለተኛው ፕሮብሌም፣ ለአስፍሐ ወልደሚካኤልና ለመላከሡላም ዲሚጥሮስ ገብረማርያም ስለሚሰጠው ሹመት ነበር:: አስፍሐ ወልደሚካኤል ከልባቸው የተመኙትና የጠበቁት፣ በቢትወደድነት ላይ የራስ ወርቅ አስረው፣ የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት የመጀመሪያው እንደራሴ እሆናለሁ ብለው ነው:: ራስ ቢትወደድ ተብለው የእንደራሴነቱን ሥልጣን በሚረከቡ ጊዜ፣ ሁለት ምክትል እንደራሴዎች፣ ከክርስቲያን ወገን መላከሡላም ዲሚጥሮስ፣ ከእስላሞቹ ሼህ አሊ ሙሣ ራዳይ እንዲሆኑላቸው አቅደው ነበር:: ይህ የአስፍሐ ፕላን በራሳቸው ብቻ የተወጠነ ሳይሆን፣ አብዛኛዎቹ « የማህበረ ፍቅረ ሀገር » አባሎች፣ በጣም አስፈላጊነቱንና ተገቢነቱን አምነውበት በሙሉ ተስፋ ይጠብቁት የነበረ ጉዳይ ነው:: ሀሳቡን አስፍሐ ራሳቸው ለጃንሆይ ማቅረቡ ስለከበዳቸው፣ በወዳጃቸው በጄኔራል ዐቢይ አበበ በኩል እንዲፈጽምላቸው ጠየቁ:: አስፍሐ ይህን ሲጠይቁ፣ ጄኔራል ዐቢይ አዲስ አበባ ተጠርተው፣ ቢያንስ የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት ሥልጣን ይሰጣቸዋል እንጂ፣ እዚሁ ኤርትራ በድጋሚ እንደራሴ ይሆናሉ ብለው ጨርሶ አልጠረጠሩም:: ጄኔራል ዐቢይ ለቢትወደድ የተለየ አስተያየት ያላቸውና የቅርብ ወዳጅነታቸውን የሚያጠብቁ ቢሆኑም፣ የተረበው ሀሳብ የሚደገፍ ሆኖ አላገኙትም:: ከሀያ አምስት ዓመት በፊት፣ በፋሽስቱ የኢትዮጵያ ገዥ በዱካ ዳአስታ ዘመን ከፍተኛ ማዕረግ የነበራቸውና፣ በሮማ ዱቼ ሙሶሊኒ ዘንድ ቀርበው የ «ካቫሊየሬ» ደረጃ ኒሻን የተሸለሙትን ሰው፣ ዛሬ ራስ ቢትወደድ ብሎ የራስ ወርቅ እንዲያስሩ ማድረግ፣ የቤተ መንግሥቱን ሥርዓት ማቃለል ይሆናል ብለው አሰቡ:: ከዚህ በላይ ደግሞ በልማዱና በወጉ፣ በአንድ ንጉሠ ነገሥት ዘመን « የራስ ቢትወደድነት » ማዕረግ የሚሰጠው ለአንድ ሰው ብቻ ነው:: ይህም ተመርጦ የተሾመው ሰው በሕይወት እስካለ ድረስ፣ በድጋሚ ሌላ ራስ ቢትወደድ አይሾምም ይባላል:: በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን የመጀመሪያው ራስ ቢትወደድ ሆነው የተሾሙት፣ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መኩንን እንዳልካቸው ብቻ ናቸው:: አስፍሐ ይህን ሹመት በአለሙበት ጊዜ፣ ራስ ቢትወደድ መኩንን በሕይወት ነበሩ::

የሞቱት የአስፍሐ ራስ ቢትወደድነት አይሆንም ከተባለ ከአንድ ወር ከአሥር ቀን በኋላ፣ በየካቲት 1963 ዓ.ም ነው:: ገኔራል ዐቢይ የአስፍሐን ራስ ቢትወደድነት ያልደገፉት፣ ሰውየው በጠላት ዘመን ለወገኖቻቸው ለኢትዮጵያውያኖች የፈጸሙትን ሰብዓዊ ተግባርና፣ ከዚያም በኋላ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ አንድነት የደከሙትን ሁሉ በመዘንጋት አልነበረም:: የወሰዱት አቋም፣ የራስ ቢትወደድነት ማዕረግ ከአስፍሐ ወልደሚካኤል የሕይወት ታሪክ ጋር አይኳኋንም በማለት ብቻ ነው::

ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ አጅግ የደከሙትና ውጤቱን ያስገኙት በተለይ ቢትወደድ አስፍሐና መላከሠላም ዲሚጥሮስ፤ ሚሲዮናቸውን የፈጸሙ ስለሆነ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ከኤርትራ ጉዳይ መውጣት አለባቸው:: እነዚህ ሁለት ሰዎች የሚገባቸው ሹመት ተሰጥቷቸው ወደ አዲስ አበባ እንዲዛወሩ፤ አሁን ለኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ኃላፊነት እንዲቀበሉ የሚመረጡት ሰዎች ሌሎች እንዲሆኑ የንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ ሆነ:: ጥር 20 ቀን 1963 ዓ.ም ገኔራል ዐቢይ አበበ፤ የመጀመሪያው የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ እንዲሆኑ፣ በጃንሆይ ከተነገራቸው በኋላ፤

| | |
|---|---|
| -- ቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል | የፍርድ ሚኒስትር |
| -- መላከሠላም ዲሚጥሮስ ገብረማርያም | የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል፣ |

ሆነው መሾማቸው ከአሥመራ ቤተመንግሥት መግለጫ ተሰጠ::

ከዚህ በላይ እንደታየው የፌዴሬሽኑን መፍረስ ላከናወኑት ሰዎች የሥራ ድልድል ከተደረገ ከጥቂት ሰዓቶች በኋላ፤ ለሚቀጥሉት ሁለት ሰዎች ንጉሠ ነገሥቱ የሰጡት ሹመት፤ መላ የማህበረ ፍቅረ ሀገር አባሎችን ከመጠን በላይ አሳዘነ::

1. በዚያ በትግሉ ዘመን ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል የለባትም ብለው ይቃወሙ የነበሩት፤ ፊታውራሪ ተሰፋዮሐንስ በርሄ በሚኒስትር ደኤታ ማዕረግ <u>የጠቅላይ ግዛቱ ምክትል እንደራሴ፣</u>

2. የራቢጣ ኤል ኢስላሚያ ፓርቲ ወገን ሆነው የአንድነቶች ተቃዋሚ የነበሩትና፣ ኋላም የምዕራባዊው ቆላ አውራጃ ከሌላው የኤርትራ ግዛት ተገንጥሎ፣ ነፃነቱን እንዲያገኝ ሲጥሩ የቆዩት አሊ ሙሣ ራዳይ፤ በሚኒስትር ደኤታ ማዕረግ፣<u>የጠቅላይ ግዛቱ እንደራሴ አማካሪ፤</u> ሆነው ተሾሙ::

"ኢትዮጵያ ወይ ሞት" ብለው፣ ያንን ሁሉ መስዋዕትነት የተቀበሉት የአንድነት ወገኖች፣ እነሱ እንደተመኙትና እንደደከሙበት ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ውህደቱ ሲጀመር፣ አስተዳዳሪዎቻቸው ሆነው የሥልጣኑን ልጓም የሚጨብጡት፣ በሕይወታቸው ላይ የፈረዱባቸው ባለጋራዎቻቸው ሲሆኑ፣ ለምን አያዝኑም ? ለምንስ አይማረሩም ? ..... አንድነቶች አላማቸውን ከግቡ ለማድረስ በሚታገሉበት ዘመን፣ በባዕድ አስተዳዳሪዎች እየተጨቆኑ፣ ያለ ምክንያት ከሥራ እየተባረሩ፣ ያለ

ጥፋት እየታሰሩ፣ ያንን ሁሉ የግፍ በደል ሲቀበሉ፣ ራቢጣዎች የውጭ ጠላት በሚያፈስላቸው ገንዘብ ሕይወታቸውን በማንደላቀቅ ያሳለፉ ናቸው::

ኢትዮጵያዊነታችን ከተመለሰልን፣ በአገራችን ኮርተን በነፃነታችን ተከብረን እንኖራለን:: ኢትዮጵያዊነታችንን ከተከለከልን ግን፣ እንዳለፉት ዘመናት የኮሎኒያሊስቶች መጫወቻ ከምንሆን፣ ሞትን እንመርጣለን ብለው፣ ቆርጠው የተነሱትና ሞትን የተጋፈጡት የአንድነት ሕዝቦች፣ በመጨረሻው የሚጠብቃቸው ዕድል፣ በባለጋራዎቻቸው ሥልጣን ሥር መውደቅ መሆኑን ቢያውቁት ኖሮ፣ ለኢትዮጵያ ወይ ሞት ያን ሁሉ መከራ ለመቀበል ባልሞከሩት ነበር:: ኤርትራ ወደ እናቷ ወደ ኢትዮጵያ እንድትመለስ መስዋዕትነትን የተቀበሉ፣ በፌዴሬሽን የተደረገው ቅልቅል በአንዲት ኢትዮጵያ አስተዳደር እንዲለወጥ፣ ታግለው ድሉን ያገኙት አንድነቶች ብቻ መሆናቸው እየታወቀ፣ ሹመትና ሥልጣን ለራቢጣዎቹ ማሸከም ለምን እንዳስፈለገ፣ የሚያስረዳ አልተገኘም::

አንድነቶች በዚህ በተፈጸመባቸው በደል እጅግ አዝነው፣ እንደጉርፍ የወረደው እንባቸው፣ ቀስ በቀስ የኢትዮጵያዊት ኤርትራን የአንድነት ግንብ እያራሰ፣ ለማፍረስ እንደሚያበቃው አርቆ ያሰበ የለም:: በዚህ በጥር ወር 1963 ዓ.ም አሥመራ ላይ በንጉሠ ነገሥቱ የተሰጠው ሹመት እንኳንስ ለሩቅ ታዛቢዎች ቀርቶ ለቅርቦቹ እንኳን፣ ግቡ የማይታወቅ የተዳፈነ ምሥጢር ሆነ:: የቀድሞው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ተስፋዮሐንስ በርሄ በሚኒስትር ደታ ማዕረግ የመጀመሪያው የኤርትራ ምክትል እንደራሴነትን ሲቀበሉ፣ እጅግ የታወቁት የአንድነቱ አርበኛ መላከሠላም ዲሚጥሮስ ገብረማርያም ያለ አንዳች ማዕረግ ተራ ሴናተር ሆነው አዲስ አበባ እንዲዛወሩ ተደረገ:: «......ኢትዮጵያዊነታችንን ለማግኘት ብዙ ሥቃይ ተቀብለን ነበር:: አሁን ኢትዮጵያንም ካገኘናት በኋላ፣ ሥቃያችን እንዲቀጥል ንጉሠ ነገሥታችን አዘውናል..... » በሚል የመረረ ቃል በሠሩት ሁሉ የተጸጸቱና፣ ተስፋቸውን የቆረጡት የአንድነት ወገኖች፣ ጥቂቶች አልነበሩም:: በወከላቸው ሕዝብ ስም ሆነው ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ድምፃቸውን የሰጡት የፓርላማው አባሎች፣ ለጥቂት ዘመን ያልሠሩበትን ደሞዝ በየወሩ ሲቀበሉ ቢከርሙም፣ ለዘለቄታው አንድ ዓይነት ቋሚ ሥራ ሳይታሰብላቸው በመቅረቱና፣ ቀስ በቀስ ወደ ኋላም ጨርሶ በመረሳታቸው፣ ብስጭትና ጸጸት ሲያጠቃቸው ቆይቷል:: ለተስፋዮሐንስ በርሄ ተከምሮ የተሰጠውም ሥልጣን ለፌዴሬሽን አፍራሾች ውለታ ያስብላቸዋል ተብሎ አይጠበቅም:: በተለይ በኤርትራ ፖሊስ አዛዥ በብሪጋድየር ጄኔራል ተድላ ዕቁቢት ላይ የደረሰውን ብስጭትና ሀዘን መመልከት ይበቃል:: ኅዳር 15 ቀን 1962 ዓ.ም በአሥመራ ከተማ የፈነዳው የአንድነት ደስታ መንፈስ፣ ከሁለት ወር ተኩል በኋላ ጥር 30 ቀን በምሬትና በቁጭት ተለውጦ ማየት እጅግ ያሳዝን ነበር:: በዚህ ጉዳይ ከቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል ጋር በስፋው ተነጋግሬ፣ ይህ ሁሉ ሊደርስ የቻለው በምን ምክንያት እንደሆነ፣ የሰጡኝን አስተያየት እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ::

« ..... የፌዴሬሲዮኑ መፍረስ በደህና ከተፈጸመ በኋላ፣ ጃንሆይ አሥመራ መጥተው በሰነበቱበት ሰሞን ትልቅ ስህተት ሠሩ:: በኤርትራ ጉዳይ እስከ መጨረሻ የተሰዉትን ዲሚጥሮስንና አስፍሐን ወደ አዲስ አበባ አዛውረው፣ ለራቢጣው ለተስፋዮሐንስ ሹመትና ሥልጣን አሸከሙ:: በዚህ «መሬቱ የሚቀበለውን ትቶ አራሹ የፈለገውን ዘራ» የሚባለው ጥንታዊ ታሪክ ተፈጸመ:: ዩኒዮኒስት የተባሉት ለአንድነት፣ በአንድነት የተዋጉና የተሰዉ ሁሉ፣ በእኛ መገለልና በተስፋዮሐንስ ሹመት እጅግ አዝነው ዕለቱኑ ሸፍተው አደሩ:: ተቃዋሚዎቻችንም ለካስ እዚህ

ለመድረስ ኖርዋል ? ብለው መዘባበቻ አደረጉን። የኛ ተግባር ፌዴሬሽኑን ማፍረስ ብቻ ሳይሆን፣ ከፈረሰም በኋላ፣ የአስተዳደሩን መዋህድ አስተካክሎ ማላመድና ማጠንከር መሆን ነበረበት። ነገር ግን መላከሣላምና እኔ፣ ይህንን ተግባር እንድንፈጽም አልተመረጥንም። ፌዴሬሽኑን በማፍረስ ጉዳይ ዋና ዋና የሆኑት ሰዎች ለአዲሱ አስተዳደር አይሆኑም ተብሎ፣ እኛን ወደ አዲስ አበባ አዛወሩን። ምክንያቱ ይህ ከሆነ፡ ጄኔራል አቢይስ ከእኛው ጋር ተባባሪ አልነበሩም ? እሳቸውስ ለምን አልተዛወሩም ? ...... »

ጥያቄ -

ፊታውራሪ ተስፋዮሐንስ በርሄ ምክትል እንደራሴ እንዲሆኑ ሀሳቡ የመነጨው ከማን ነው ?

መልስ -

« ..... በችሎታው ይስማማኛል ብለው ሹመቱን ያስጡት ጄኔራል አቢይ አበበ ናቸው። ከጄኔራል አቢይ ጋር ለሶስት ዓመታት በመካከላችን እንከን ሳይገባ የልባችንን እየተገላለጥንና እየተመካከርን ስንሠራ ከኖርን በኋላ፣ በመጨረሻው ጊዜ ተስፋዮሐንስን ምክትል እንደራሴነት ለማሾም ለጃንሆይ ሲያቀርቡ አላማከሩኝም። በዚህ በኩል የተሰማኝን ቅሬታ ምንጊዜም ሳልረሳው እኖራለሁ። ጃንሆይ እንደወትሮአቸው ጠርተው ስለ ሹመቱ ምን ታስባለህ ? ብለው ጠይቀውኝ ቢሆን ኖሮ፣ ተስፋዮሐንስን ምክትል እንደራሴ ማድረግ ለኢትዮጵያ የተሰጡትን አንድነቶችን እንደ መግደል የሚቆጠር ነው እላቸው ነበር። ዋና እንደራሴነቱ ለጄኔራል አቢይ ከተሰጠ ፣ የቀረው ቢቀር የቆላውን ሕዝብ ለማስደሰትና ለማስተባበር ሼህ አሊ ራዳይን ምክትል ማድረጉ ይጠቅም ነበር። ምን ይሆናል? ሀሳቡን ለማቅረብ ዕድሉ አልተሰጠኝም። ፌዴሬሽኑን ካፈ ረሰን በኋላ ጃንሆይ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ሲመጡ፣ ጠቅላይ ሚኒስትራቸውንና ዋና ዋና ሚኒስትሮቹን ይዘው በመምጣት ለአገሩ የሚታሰበው አዲሱ አስተዳደር፡ በሚገባ እንዲመከርበትና እንዲወሰን ቀደም ብዬ ያቀረብኩት፡ ሀሳብ ይህን ከመሳሰለው የአሠራር ስህተት ሊያድን ይችል ነበር ብዬ አስባለሁ። ...... »

ጥያቄ -

ቢትወደድ ! ይቅርታ ቢያደርጉልኝ ወደኋላ ተመልሼ አንድ ነገር ላስታውስዎ እፈልጋለሁ። ይኸውም፣ በታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ ኤርትራ በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል በወሰነ ጊዜ፣ እርስዎ ለጃንሆይ በጽሑፍ ስለ አቀረቡት ስለ አንድነት ተቃዋሚዎች ወይም ራቢጣዎች ጉዳይ ነው። « ..... በአንጻራችን ቆመው የተዋጉን የተቃዋሚ ማህበሮች፣ በማፈርና በመፍራት እንዳይርቁና፣ ቀቢጸ ተስፋ ይዟቸው በጀመሩት የባዕድ መሣሪያነት እንዳይቀጥሉ፡ ከቀሩት ወንድሞቻቸው ጋር በእኩልነት በማየት የምናቅፋቸው እንጂ የምናርቃቸው አለመሆናችንን በተግባር መግለጽ አለብን ...... » ብለዋል። ይህ ሀሳብ በሌላ አነጋገር ራቢጣዎቹን በጠላትነት ማየት አያስፈልግም። መብታቸው ከሌላው እኩል የሚጠበቅላቸው መሆኑን አይስረዱ ማቅረቡ ይጠቅማል የሚል ነው። ይህን የርስዎን ሀሳብ መሠረት አድርገን ስንከተል፣ ራቢጣ የነበሩት ተስፋዮሐንስ በርሄ በተድላ ባይሩ መንግሥት ጊዜ ከፍተኛ

ኃላፊነት ተሰጥቷቸው እንደነበረ፣ በርስዎም ካቢኔ የፋይናንስ ሚኒስትር (ሚኒስትር) የነበሩ ሥራቸውን አይተናል። ስለዚህ እናንተ የአንድነት ሰዎች እኚህን የቀድሞ ራቢጣ በፓርላማን እያሳደጋችሁ ያመጣችኋቸው ስለሆነ፣ ገኔራል በቢይ ምክትል እንደራሴ እንዲሆኑ በማሾማቸው፣ ለምንድን ነው እስከዚህ ድረስ የሚያሳዝን ሆኖ የታያችሁ ?

መልስ-

« ...... ይህን ጥያቄ በሁለት መልክ መክፈል ያስፈልጋል። የመጀመሪያው በ1950 ዓ.ም ለጃንሆይ ስለአቀረብኩት ሀሳብ ነው። የተነበበልኝ ደብዳቤ እርግጥ እኔ የጻፍኩት ነው። እኔም ኮፒው አለኝ። ሌላው ኮፒ እንተ ዘንድ እንዴት እንደደረሰ፣ ምርምሩን ትቼ፣ ተዓምር ነው በማለት ባልፈው ይሻለኛል። ..... አንተ እንደጠ ቀስከው ለጃንሆይ የጻፍኩት ደብዳቤ፣ የተባበሩት መንግሥታት የኤርትራን ጉዳይ ሕገቡ የጠየቀውን ችላ ብሎ፣ ድርጅቱ በፈለገው ዓይነት ከፈረደ በኋላ፣ የአገራችንን የውስጥ ፖለቲካ ጉዳይ በምን መልክ እንደምናዘጋጅ ሀሳብ የሚሰጥ ነው። ይኸውም፣ በኤርትራ ውስጥ ባሉት የፖለቲካ ማህበሮች መካከል ያ ሁሉ ትግልና ፍጅት ተደርጎ በተገኘው ውጤት፣ አንድነቶች አሸናፊዎች በመሆናቸው፣ በተቃዋሚዎቻቸው ላይ ጥቃት እንዳያደርሱ ጥንቃቄ እንዲደረግ ነው። እንድነቶችና የተቃዋሚው ክፍሎች፣ አሸናፊዎችና ተሸናፊዎች ተብለው ወገን እንዲለዩ የተደረገ እንደሆነ፣ የውጭ ጠላትም መግቢያ በር ስለሚያገኝ፣ በኤርትራ ውስጥ ምንጊዜም የማያቋርጥ የርስ በርስ ጦርነት ሊቀጥል ይችላል። ይህ እንዳይደርስ እኛ የአንድነት ወገኖች፣ ልበ ሰፊዎችና አርቆ ተመልካቾች ሆነን ተቃዋሚዎቻችን በተሸናፊነታቸው አፍረው፣ የውጭ መጠጊያ ሆነው የጠላትነት ሥራ እንዳይቀጥሉ፣ 1ኛ/ መብታቸው ከሁሉም ጋር እኩል እንደሚጠበቅላቸው፣ 2ኛ/ በሥራም ሆነ በግል ኑሮአቸው ምንም ዓይነት ልዩነት እንደማይደረግባቸው፣ በተግባር የሚታይ ዋስትና ይሰጣቸው እልክ እንጂ፣ አንድነቶች ታግለውና አሸንፈው ያገኙትን የሥልጣን ወንበር ለራቢጣዎቹ መልቀቅ ያስፈልጋል አላልኩም። ተስፋዮሐንስ በርሄን፣ ደጃች ተድላም ሆኑ እኔ፣ በችሎታው ተገቢ በሆነ ሥራ ላይ እዋልነው እንጂ፣ እሥልጣን ቁንጮ ላይ ወጥቶ አንድነቶችን የሚያጠቃበት ዕድል አልሰጠነውም። ተስፋዮሐንስ በርሄን ችሎታውን በማየት ብቻ ከሚገባው በላይ ከፍተኛ ሥልጣን መስጠት፣ የእንድነት ወገኖችን ምን ያህል እንደሚያሳዝን መታወቅ ነበረበት። ...... »

የታወቁት ራቢጣ ተስፋዮሐንስ በርሄ፣ በደጃዝማች ተድላ ባይሩ በተለይም በቢትወደድ እስፍሐ ወልደሚካኤል ካቢኔ፣ ከፍተኛ ኃላፊነት የተሰጣቸው በሥልጣን ማደጋቸው አልተካደም። ይሁን እንጂ በአንድነቶች በኩል ትልቁ ቅሬታና ሀዘን የተፈጠረው፣ ተስፋዮሐንስ የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ምክትል እንደራሴ ሆነው መሾማቸው ነው ተብሏል። ይህ እንዳይደርስ፣ በንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፍቃድ የተስፋዮሐንስ በርሄ በምክትል እንደራሴነት ሹመት ከመታወጁ በፊት፣ የጃንሆይ ባለሟል የሆኑት የቢትወደድ እስፍሐ ወልደሚካኤል አስተያየት ሳይጠየቅ መቅረቱ፣ እጅግ አስገራሚ ሆኖ ይታያል።

# የተድላ ዕቁቢት ትራጄዲ

በደጃዝማች ተድላ ባይሩ መንግሥት ጊዜ የኤርትራ ፖሊሲ የሚመራው በእንግሊዞች አዛዥነት ነበር። በመስከረም 1955 ዓ.ም አስፍሐ ወልደሚካኤል ቺፍ ኤግዜኩቲፍ በሆኑ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ፡ በእንግሊዙ በኮሎኔል ራይት (WRIGHT) ቦታ ሻለቃ ተድላ ዕቁቢት የተባለውን የሠራዊ ተወላጅ፡ የኤርትራ ፖሊስ ዋና አዛዥ አድርገው ሾሙት። በእንግሊዞች አስተዳደር ዘመን በፖሊስነት ሞያ የሰለጠነው ሻለቃ ተድላ፣ ትጋቱና ዲሲፕሊኑ በበላዮቹ ዘንድ ስለታወቀለት፡ ለኤርትራ ፖሊስ አዛዥ በፓርላማው የተወሰነውን የኮሎኔልነት ማዕረግ ለማግኘት የተፋጠነ ዕድገት ተደርጐለታል።

ተድላ ዕቁቢት፡ የአንድነት ያገር ፍቅር ማህበር አባልና ታጋይ መኰንን ተብሎ የተመሰከረለት ስለሆነ፣ በቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል የአስተዳደር ዘመን ለኤግዜኩቲፉ ሥልጣን በጣም ቅርብና እምነት የተጣለበት ሰው ነበር። ይህ ወጣት መኰንን በፖሊስ አዛዥነቱ፡ ጃንሆይ ወደ ኤርትራ በተጓዙ ቁጥር የሚያደርግላቸው የአጠባበቅ ዝግጅትና፡ የሚያሳያቸው የነቃ መንፈስ፣ መልካም አስተያየትና አድናቆት ስለአሳደረባቸው፣ አዲስ አበባ በማዘዋር መጥቶ እንዲስተናገድ ከማድረጋቸው በላይ፡ አንድ ግልጽ አውቶሞቢልና በሚወዷቸው ልጃቸው በልዑል መኰንን የተሰየመ ልዩ ሽጉጥ ሸልመውታል።

በሰኔ 1962 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥቱ ኤርትራን ለመጐብኘት ሲሄዱ፣ በሥራውና በአንድነት መንፈሱ ለተደሰቱበት ለተድላ ዕቁቢት፣ «የብርጋድየር ጄኔራልነት ማዕረግ» እንዲሰጠው ራሳቸው አሰበው፡ የክብር ልብሱም በኢትዮጵያ የፖሊስ ጄኔራሎች ፎርም በልዩ ዘዴ ተሰፍቶ ከሹመቱ ጋር እንዲሰጠው ወሰኑ። በዚያን ሰሞን አሥመራ ላይ ይካሄድ የነበረው የጊኔ ሬፑብሊክ ፕሬዚዳንት የአህመድ ሴኩቱሬ አፊሴል ጉብኝት ከተፈጸመ በኋላ፣ ሰኔ 26 ቀን 1962 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥቱ በቤተመንግሥቱ ቢሮአቸው ላይ እንደተገኙ፣ ኮሎኔል ተድላ ተጠርቶ የታሰበለት ሹመት እንዲሰጠው፣ እንደራሴያቸውን አዘዙ። ጄኔራል ዐቢይም በበኩላቸው ምክትል እንደራሴውን አስፍሐን ጠርተው ተድላ ዕቁቢትን ለሹመቱ እንዲያስጠሩት ነገሯቸው። በዚህ ጊዜ ምክትል እንደራሴ አስፍሐ ይበሳጩና፣ በኤርትራ ዋና አስተዳዳሪነት ሥልጣናቸው፡ ለተድላ የሚሰጠው ሹመት ተገቢ አይደለም በማለት ንጉሠ ነገሥቱን ማነጋገር አለብኝ አሉ። በዚያች ሰዓት፣ እኔ የማስታወቂያን ሥራ በሚመለከት ጉዳይ፣ ከአለቃዬ ከብላታ ግርማቸው ተክለሐዋርያት ጋር ጃንሆይ ቢሮ ስለነበርኩ፡ ቢትወደድ አስፍሐ በድንገት ዘው ብለው ገብተው፣ ለኤርትራ ፖሊስ አዛዥ ለመስጠት የታሰበውን የብርጋድየር ጄኔራልነት ማዕረግ በኤርትራ አስተዳዳሪነቴ አልቀበልም ብለው ሲሟገቱ፣ የነበረውን ሁኔታ የማየት ዕድል አጋጥሞኛል። አስፍሐ ወልደሚካኤል በአነጋገራቸውም ሆነ በአቀራረባቸው ጃንሆይን ሲዳፈሩ ያየሁት ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሆነ፡ ንጉሠ ነገሥቱ ምንም እንኳን የኤርትራን አስተዳዳሪ በቀጥታ ለመሻር ሥልጣን ባይኖራቸውም፣ በጃንሆይ መልካም ፈቃድ የተሰጣቸው የቢትወደድነት ማዕረግ ተገፎ፡ «አቶ» እንዲባሉ ይወስኑባቸዋል ብዬ ሰግቼ ነበር። አስፍሐ ወልደሚካኤል በመጀመሪያ ለተድላ የታሰበው የብርጋዲየር ጄኔራልነት ማዕረግ ተገቢ አለመሆኑን ለማስረዳት፣ ሶስት ምክንያቶች ደረደሩ።

1. የኤርትራ ፖሊስ አዛዥ በኮሎኔል ደረጃ እንዲሆን በፓርላማ የተወሰነ ስለሆነ፣ ጃንሆይ ሕገ መንግሥቱ በማይፈቅድልዎ የውስጥ ጉዳይ ገብተው ደንቡን ቢሽሩት፣ መማክርቶቼን በጣም ቅር ያሰኛቸዋል:: ከዚህም በላይ የጃንሆይን ስም የሚያስነሳ ፕሮፓጋንዳ ለመንዛት፣ ለጠላቶቻችን ዕድል ይሰጣል::

2. ተድላ ዕቁቢትን ከሻለቃነት ደረጃ አንስቼ የፖሊስ ዋና አዛዥ ሳደርገው፣ የኮሎኔልነትን ደረጃ ያገኘው በተፋጠነ ዕድገት ስለሆነ፣ ዛሬ ለጄኔራልነት ማዕረግ አልደረሰም::

3. ግርማዊነትዎ የጄኔራልነት ማዕረግ ይገባዋል ብለው ከወሰኑ፣ ተድላ እቁቢት ብርጋድየር <u>ጄኔራልነቱን ተቀብሎ አዲስ አበባ መዛወር አለበት እንጂ፣ የኤርትራ ፖሊስ አዛዥ ሆኖ መቀጠል አይችልም</u> ....... ብለው አስረዱ::

ጃንሆይ ቱግ አሉ:: « ..... የፓርላማውን አባሎች፣ አንተም እያመለከትከን እኛም እያስብንላቸው፣ ራስ ደጃዝማች ፊታውራሪ ቀኛዝማች ...... እያልን ስንሾም ኖረን የለም ወይ ? በዚሁ አኳኋን ለፖሊሱ አዛዥ የማዕረግ ዕድገት በመስጠታችን ፓርላማዎቹን ቅር የሚያሰኛቸው ምኑ ነው? ..... ይኸ አንተ ራስህ የፈጠርከው ፍሬ የሌለው ምክንያት ስለሆነ አልተቀበልነውም ... » ብለው፤ በቁጣ ተናገሩ:: ወዲያው ጄኔራል ዐቢይ ነገሩን ለማብረድ ወደ አስፍሐ መለስ ብለው፣ « ..... ቢትወደድ ! የፓርላማው አባሎች የጃንሆይን ሀሳብ እንዲረዱት ለማድረግ፣ እርስዎ ባለዎት ጥበብና ዘዴ መሞከር አይችሉም ወይ ? ...... » ብለው ጠየቋቸው:: ጃንሆይ የበለጠ ተናደዱ:: ወደ ጄኔራል ዐቢይ ፊታቸውን መልሰው፤ « ..... አንተ ደግሞ ምን ታስታምማለህ ? የፓርላማውን ነገር የፈጠረው እሱ ራሱ ስለሆነ አንቀበለውም ብለነዋል ...... ትዕዛዛችን አሁን መፈጸም አለበት ..... » ብለው፤ ከወንበራቸው ብድግ አሉ:: ዓይናቸው አስፍሐ ላይ ተተክሎ ቀረ:: በዚህ ጊዜ ቢትወደድም በጣም ደነገጡ:: « ..... የጃንሆይ ትእዛዝማ መከበር አለበት:: ለዚህ ጥያቄ አይቀርብበትም:: እኔ ታማኝ አገልጋይዎ ለጃንሆይ ሀሳቤን ሳልደብቅ እንድናገር ያስለመዱኝ እርስዎ ነዎት:: ስለዚህ፤ የሚመስለኝን ገለጥኩ እንጂ፣ የጃንሆይን ትእዛዝ አላከብርም አላልኩም ... » ብለው እጅ ሲነሱ፣ ሠላም ሆነ::

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፣ ኮሎኔል ተድላ እንደራሲው ቢሮ ተጠርቶ፣ በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድና ትእዛዝ <u>የብርጋድየር ጄኔራልነት ማዕረግ</u> የተሰጠው መሆኑ ተነገረው:: ወዲያውም ከአዲስ አበባ፣ በጄኔራል ድረሴ ዱባለ የኢትዮጵያ ፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ ዩኒፎርም ዓይነት፣ የተዘጋጀለትን የማዕረግ ልብስ፣ ከብላታ አድማሱ ረታ የጃንሆይ ልዩ ግምጃ ቤት ሹም ተቀብሎ ለበስ:: በአዲሱ የማዕረግ ልብሱ ጃንሆይን ጪማ ስሞ ሲወጣ፤ ከጄኔራል ዐቢይ በፊት ሮጦ ሄዶ አንገታቸው ላይ ተጠምጥሞ ደስታውን የገለጠው ለቢትወደድ አስፍሐ ነበር:: ያለ ጥርጥር ሹመቱ የጃንሆይ ቢሆንም፣ ለዚህ ደረጃ ያበቁኝ ቢትወደድ አስፍሐ ናቸው ብሎ፤ በማመን ነው::

ተድላ እቁቢት ብርጋድየር ጄኔራል ተብሎ፤ የኢትዮጵያን ፖሊስ ሠራዊት ጄኔራሎች ዩኒፎርም ከለበሰ ከአምስት ወር በኋላ፣ ፌዴሬሽኑ ሲፈርስ ከቢትወደድ አስፍሐና ከአንድነቶች ጋር የቅርብ ተባባሪ ከመሆኑም በላይ፣ የተሰማው ደስታ



የኤርትራ ፖሊስ አዛዥ ሻለቃ ተድላ ዕቁቢት
(ኋላ ብሪጋድየር ጄኔራል)

*« ....... የዛሬው በዓላችን፣ ትልቋ ኢትዮጵያ እንደገና መጣች። የአክሱም ታሪካችን እንደገና መጣች። ....... ከዛሬ ጀምሮ በማህል ምንም ነገር የሌለበት ሁሉም ሰው ኢትዮጵያ ብቻ ሆኖ እንዲኖር ተደረገ እያልን የምናስበው ቀን ነው ....... »*

(ተድላ ዕቁቢት ኅዳር 16ቀን 1962 ዓ.ም
ፌዴሬሽን በፈረሰ ማግሥት የሰጠው አስተያየት።)

ወሰን አልነበረውም። ፌዴሬሽኑ በፈረሰ ማግሥት ሐሙስ ኅዳር 16 ቀን 1962 ዓ.ም የግርማዊነታቸው እንደራሴ በቤተመንግሥቱ ባደረጉት የምሣ ግብዣ ላይ፣ ለእኔ ወንበር የተሰጠኝ ከጄኔራል ተድላ ዕቁቢት አጠገብ ነበር። በዚያን ቀን በተድላ ላይ ያየሁትን የደስታ ስሜት ምንጊዜም አልረሳውም። በመካከላችን ወዳጅነትና መቀራረብ ስላለ፣ አንድ ነገር ልጠይቀው ብዬ አሰብኩ። « ጄኔራል ! ለዚህ በዓላችን ምን ስም እንስጠው ? .... የታላቁ አንድነት ቀን » ብንለው ምን ይመስልሃል ? ..... ብዬ ጠየቅኩት። « .... የለም .... የለም .... የአንድነት ነገር ድሮም አንድ ነን። የዛሬ አሥር ዓመትም ለአንድነት በጣም አክብረናል። ስለ አንድነትም በጣም ተናግረናል። የዛሬ ጉዳያችን፣ ትልቋ ኢትዮጵያ እንደገና መጣች። የአክሱም ታሪካችን እንደገና መጣች። አሁን ከዛሬ ጀምሮ በማህል ምንም ነገር የሌለበት ሁሉም ሰው ኢትዮጵያ ብቻ ሆኖ እንዲኖር ተደረገ፣ እያልን የምናስበው ቀን ነው ..... » አለኝ። አነጋገሩ በጋለ ስሜትና ቆጣ ባለ መንፈስ ስለሆነ፣ ሌላ ጥያቄ አልጨመርኩም። በሰጠኝ አስተያየት አድናቆቴን ገልጬ ጭውውታችንን ወደ ሌላ ጉዳይ አዛወርኩት።

የፌዴሬሽኑን መፍረስና የአስተዳደሩን ከኢትዮጵያ ጋር መዋሀድ ከልቡ ያመነበትና ያንን ያሀል ደስታ የተሰማው ሰው፣ ከጥቂት ወራቶች በኋላ ሕይወቱን ለማጥፋት ያደረሰው ምክንያት ምን እንደሆነ፣ ከቢትወደድ አስፍሐ ያገኘሁትን አስተያየት እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

## ተድላ ሕይወቱን ያጠፋው በተስፋዮሐንስ በርሄ ምክንያት ነው

(አስፍሐ ወ/ ሚካኤል)

« ...... ጥር 20 ቀን 1963 ዓ.ም የፍርድ ሚኒስትርነት ተሾሜ ከቤተመንግሥቱ ስወጣ፣ ከመውጫው በር ላይ የኤርትራን ፖሊስ ዋና አዛዥ አገኘሁት። ቀዝቀዝ ያለ ሰላምታ ሰጥቶኝ ዝም አለኝ።

-- ምነው ጄኔራል እንኳን ደስ አለህ አትለኝም ወይ ? ..... አልኩት።

-- እያወቀ፣ ምን ሆነዋል ? አለኝ።

-- የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የፍርድ ሚኒስትር ሆንኩ፣ አልኩት።

-- ሳቅ አለና ..... እራሱን እየነቀነቀ፣ እኛ ነን እንጂ አገሬ፣ አንድነቴ፣ ወገኔ፣ ስንል የነበርን፣ እነሱማ (አማሮች) ወንበሬ የሚዛት ወንበሬ በማለት ላይ እንደነበሩ አሳዩን አለኝ።

-- ከተድላ የማልጠብቀው አነጋገር ስለሆነ፣ በጣም ደነገጥኩ። ይህን የገነፈለ አስተያየቱን ለመለወጥ አንዳንድ ምክር ለመስጠት ሞከርኩ። እምብዛም የሚዳመጥ ፍላጎት አይታይበትም ነበር። ..... ደግሞስ ይህን ራቢጣ ተስፋዮሐንስን፣ ምክትል እንደራሴ ያስደረጉ እርስዎ ነዎት ? ብሎ ጠየቀኝ።

-- « ..... አንተ ተድላ ምነው ማስብ ተሳነህ ? በንጉሥ እንደበት እየተነገረ ነው እንጂ፣ ሹመት እኮ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው ..... » አልኩት፡፡

-- « ..... ይህን ራቢጣ ምክትል እንደራሴ ለማለት እግዚአብሔር ሥራ አላጣም ..... » ብሎኝ ከፊቴ ዘወር አለ፡፡

ከአንድ ሳምንት በኋላ፣ እቤቴ መጥቶ ትንሽ በረጋ መንፈስ አነጋገረኝ፡፡ « ...... በአሁኑ ሰዓት እርስዎን ከኤርትራ አንስተው ወደ አዲስ አበባ መውሰዳቸው፣ የሸዋ ሰዎች ብልሆች እንዳልሆኑ ተጋለጡ፡፡ በኤርትራ ሕዝብ ዘንድ እርስዎ ምን ያህል ተወዳጅ እንደሆኑ፣ አገሩንም ለተጀመረው የፍጹም አንድነት ጉዳና፣ መሠረቱን ማስያዝ የሚችሉ እርስዎ መሆንዎን፤ ጃንሆይ የሚያውቁ ይመስለኝ ነበር፡፡ በጣም ተሳስቼአለሁ፡፡ <u>የኤርትራን ሕዝብ ጉዳይ ጃንሆይ አልተከተሉትም፡፡</u> እሳቸው በሥልጣን ታውረዋል፡፡ <u>የፌዴሬሽኑ ሕግ ስለተቀደደ ብቻ ሁሉም ችግር ያለቀ መስሏቸዋል፡፡</u> በዚህ ምክንያት ብዙ ስህተት ሠሩ፡፡ በተሠራውም ስህተት ይህ አገር ከአንድ ዓመት በኋላ አገር አይሆንም... » አለኝ፡፡ እኔም ይህን ሰምቼ ዝም ማለት አልቻልኩም፡፡ ምክሬን ቀጠልኩ፡፡ « ..... ስማ ተድላ ! አባክህ አትበሳጭ፡፡ እንደድሮህ ተግተህ ሥራ፡፡ ታማኝነትህን አታጓድል፡፡ ጃንሆይ ምን ያህል እንደሚወዱህ ታውቃለህ፡፡ አንድ ነገር ቢደርስብህ አዲስ አበባ መጥተህ ብሶትህን ትነግራቸዋለህ፡፡ እኔም በማናቸውም ጉዳይ ካንተ ጋር ነኝ፡፡ ... » አልኩት፡፡ « ..... እባክዎ! ታማኝነትም ሆነ ትጋት በሸዋ ሰዎች ዘንድ ዋጋ እንደሌለው፣ አሁን በተደረገው ተገንዝቤአለሁ፡፡ ለወደፊቱ ተስፋ የሚባል ነገር የለም፡፡ <u>እናንተም ዝም ብላችሁ፤ እያወቃችሁና ዓይናችሁ እያየ፣ ለራቢጣዎች አስረክባችሁን መሄዳችሁ ነው፡፡</u> ከእንግዲህ ወዲህ ጊዜው የራቢጣዎች ስለሆነ፤ የኛም የአንድነቶች ጉዳይ የጨለመና ቀኑን የሚጠብቅ ነው ..... » ብሎኝ ከቤቴ ወጣ፡፡

እኔ ከአሥመራ ወደ አዲስ አበባ ከመነሣቴ በፊት፣ እንደራሴውና ተድላ እልህ ተገባብተው አይቼ በጣም ሰጋሁ፡፡ ጊዜ ሳላጠፋ ጄኔራል ዐቢይን በተለየ ቀጠሮ ጠይቄ ስለ ተድላ የማስበውን ነገርኳቸው፡፡ « ..ተድላ ዕቁቢት በተስፋዮሐንስ እየታዘዘ መኖርን አይቀበልም፡፡ ለኤርትራ ኢትዮጵያነት በተደረገው ትግል፣ ተድላ ዕቁቢት ብዙ የሠራና የተከበረ ታሪክ ያለው ነው፡፡ ፈቃድዎ ቢሆን ለእኛ እንደተደረገው ለእሱም በደረጃው ወደ አዲስ አበባ ተዛውሮ እንዲሠራ ቢደረግ ትልቅ ግልግል ነው፡፡ ይኸ የማይቻል ከሆነ፣ የኤርትራ ፖሊስ አዛዥ ቀጥታ በእርስዎ የሚታዘዝ እንዲሆን ያድርጉ እንጂ፣ በተስፋዮሐንስ ሥልጣን ውስጥ አይመድቡት .... » ብዬ ለመንኳቸው፡፡ በንግግራችን ላይ ጄኔራል ዐቢይ የተድላን ወደ አዲስ አበባ መዛወር ጉዳይ እንዳልጣማቸው ታውቆኛል፡፡ ነገር ግን ፕሮብሌሙን እያወቁ፣ ተድላ በተስፋዮሐንስ ሥር እንዲታዘዝ ያደርጋሉ ብዬ አልጠረጠርኩም ነበር፡፡ በዚህ ጄኔራል ዐቢይ በሰጡት ውሳኔ የሁለቱ ሰዎች ጠብ እጅግ እየከረረ ሄደ፡፡ ተድላ በተስፋዮሐንስ ላይ ጥላቻውን በግልጽ አሳየ፡፡ እንደራሴው፣የፖሊስ አዛዥ አቋም ከዲሲፕሊን የወጣ ነው አለ፡፡ በዚህ ጊዜ ግልፍተኛው ተድላ ሁሉም ነገር ጨለመበት፡፡ ተስፋዮሐንስ ከአናቱ ላይ ሆኖ የደገነብኝን መሣሪያ፣ ጠላቶቼ እየተቀባበሉ ያጠፉኛል የሚል ስሜት አደረበት፡፡ የኤርትራ ፌዴሬሽን እንዲፈርስና ፍጹም ውህደት እንዲሆን ያደረግሁት ተጋድሎ ሁሉ፣ በመጨረሻው በጠላቶቼ እጅ ይጥለኛል ብዬ አላሰብኩም ነበር ብሎ፡ እጅግ

ተዘዉተ:: በዚህ አኳኋን የራቢጣ ሥልጣን ከሚገድለኝ፡ እኔ ቀድሜ ከሕይወቴ ልገላገል ብሎ፣ ፌዴሬሽኑን ባፈረሰን ልክ በስባተኛው ወር፣ በሰኔ 1963 ዓ.ም ራሱን ገደለ:: የዚህ የአንድነት ታማኝ መኮንን ራሱን መግደል አዲስ አበባ እንደተሰማ፡ ጃንሆይ ጠርተው አስተያየቴን ጠየቁኝ:: « ...... ተድላ ዕቁቢት ራሱን የገደለው፣ ጃንሆይን ወይም ኢትዮጵያዊት ኤርትራን ከድቶ አይደለም:: ተድላን በተስፋዮሐንስ ሥልጣን ሥር እዚያው እሥራው ላይ ከማቆየት፣ ወደ አዲስ አበባ ማዛወሩ እንደሚሻል ያቀረብኩት ሀሳብ አልተደመጠልኝም:: አሁን ያለፈው አልፏል:: ለዛሬው የሚሻለን፣ በእኔ አስተያየት ተድላን በጄኔራልነት ማዕረግ ቀብሩን ማሳመርና ቤተሰቡን መርዳት ነው:: በቀብሩ ላይ ለመገኘት ጃንሆይ እኔን ቢልኩኝ፣ የተገባ ይመስለኛል ...... » ብዬ ሀሳቤን ሳልደብቅ ነገርኳቸው:: ጃንሆይ በተድላ አሳዛኝ ሞት መነኪታቸው ይታይ ነበር:: ሆኖም ስለአቀረብኩት ሀሳብ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ፡ ጄኔራል በቢይን መጠየቅና እሱ ምን እንደሚያስብ ማወቅ ያስፈልጋል አሉ:: « .... ተድላ ራሱን የገደለው ከእኔ በላይ ባለሥልጣን የለም ብሎ ነው:: ይህ ምሥጢር አይደለም:: ማንም ያውቀዋል:: ስለዚህ በጄኔራልነት ማዕረግ ልዩ ቀብር አያስፈልግም ...... » ብለው ጄኔራል በቢይ አስተያየታቸውን ሰጡ:: ስለ ቀብሩ የእኔ ሀሳብ ተቀባይነት ባያገኝም፣ የሟቹ የጡረታ መብት ለቤተሰቡ እንዲከበርና፣ መንግሥት ሰጥቶት ይኖርበት የነበረውንም ቤት፡ ቤተሰቦቹ እንዲጠቀሙበት ጃንሆይን አስፈቅጄ፡ በዚሁ ተፈጽሟል ...... »

ተድላ ዕቁቢት በተፈጥሮው በጣም ግልፍተኛ እና በሥራውም ጨካኝ እንደነበረ በሰፊው ይነገርለታል:: የኤርትራንና የኢትዮጵያን አንድነት የሚቃወሙትን ሁሉ፣ በመብራት እያሳደደ ያጠፋቸው ነበር:: የተድላ አስተያየት በተለይ ክርስቲያኖች የሆኑት ተቃዋሚዎች፥ በውጭ ጠላት የተገዙና ለውጭ ጠላት ያደሩ ስለሆኑ፣ መራራት አያስፈልግም የሚል ነበር:: ለምሳሌ የቲሰማ አስበሮም ቤተሰቦች፣ ለጥቅማቸው ኤርትራን አንድ ጊዜ ለጣልያን ሌላ ጊዜ ለእንግሊዝ እያፈራረቁ ሲሸጡ ሲለውጡ ኖረዋል:: ተስፋዮሐንስ በርሄ ከእነዚህ የኢትዮጵያ ጠላቶች ከሆኑ ቤተሰቦች አንዱ ነው:: በጠቅላላው እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ፣ የኢትዮጵያ ጠላቶች ተብለው መጋለጥ እንደሚገባቸው፡ ተድላ ዕቁቢት ከልቡ የሚያምን መሆኑን፣ ቢትወደድ አስፍሐ በሰፊው አስረድተዋል::

ለሠራዬ አውራጃ የማህበረ ፍቅረ ሀገር ፕሬዚዳንት የነበሩት የራስ ኃይሌ ተስፋማርያም ልጅ፡ ፊታውራሪ ኪዳነማርያም ኃይሌ፣ ሐምሌ 7 ቀን 1993 ዓ.ም አዲስ አበባ ተገናኝተን ስለ ተድላ ዕቁቢት ጉዳይ የነገሩኝ፣ በብዙ ረገድ ከቢትወደድ አስፍሐ መግለጫ ጋር የሚመሳሰል ነው::

ጄኔራል ተድላ ዕቁቢት ራሱን ከመግደሉ ከጥቂት ቀናቶች በፊት፣ እንደራሴውን ጄኔራል በቢይን በልዩ ቀጠሮ አነጋግሮ ሲመለስ አግኝቼው ስሜቱን የገለጸልኝ፡ እጅግ በመረረ ብስጭት ነበር::

« ..... ክቡር ጄኔራል ! ኢትዮጵያን ጣልያን በወረራት ጊዜ፣ እርስዎ ለአገርዎ ነፃነት የተዋጉና የተሰደዱ ነዎት:: እኔም ከብዙ ኤርትራውያኖች ጋር « ኢትዮጵያ ወይ ሞት » ብዬ የታገልኩና የተሰቃየሁ አርበኛ ነኝ:: በኢትዮጵያ ባንዳ ነግሶ አርበኛን እየለቀመ እንዲያጠፋ ሥልጣን አልተሰጠውም:: በኤርትራ ግን



ግራዝማች ተስፋዮሐንስ በርሄ
(ኋላ ፊታውራሪ፣ ደጃዝማች)

የተድላ እና የአስፍሐ ካቢኔ አባል፣ የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ምክትል እንደራሴ፣
ቀደም ሲል የኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ተቃዋሚ የነበሩ፣ የራስ ተሰማ
አስበሮም ቤተሰብ ናቸው።

ራቢጣ ንግሶ አንድነቶች እንዲገደሉ ሲፈረድባቸው አያለሁ:: የአንድነቶች ጠላት ተሰፋዮሐንስ በርሄ፣ ክርስዎ ከንጉሡ ነገሥታችን እንደራሴ የበለጠ ሥልጣን ተቀብሎ፣ የሚፈጽምብንን ግፍ እርስዎ ተረድተውታል ሕ ወይስ አውቀው ትክክል ነው ብለው አምነውበታል ሕ ለዚህ ክቡር ጄኔራል የሚሰጡኝ መልስ፣ ለራሴና ለሕይወቴ ውሳኔ በጣም ይጠቅመኛል ..... » ብዬ ለመንኳቸው:: « ..... ፊታውራሪ ተሰፋዮሐንስ በርሄ፣ በጠባያቸውም ሆነ በችሎታቸው ምን ዓይነት ሰው መሆናቸውን ለማወቅ፣ ለብዙ ዓመታት የፊናንስ ሴክሬተሪና የቅርብ ረዳታቸው አድርገው ያሳደጓቸውን ቢትወደድ አስፍሐን ማነጋገር ይጠቅማል:: ፊታውራሪ ተስፋዮሐንስን እኔ የማውቃቸው በሥራ ብቻ ነው:: እስካሁን እንደአየኋቸው፣ ሕግን የሚያከብሩና ኃላፊነታቸውን በትክክል የሚፈጽሙ ጠንካራ ሠራተኛ ሆነው ነው:: በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ ምክትል እንደራሴ ሆነው መሾማቸውን አልቀበልም ብለህ ያስቸገርከ አንተ ነህ:: በእሳቸው በኩል ግን ጄኔራል ተድላ ከሥልጣኑ ይነሳልኝ፣ ወይም አጠፋ ይቀጣ ብለው ያቀረቡልኝ ነገር የለም:: ስለ አንተም አንስተው አንድም ቀን የከፋ አስተያየት ሲናገሩ አልሰማሁም:: ..... ኢትዮጵያ በጠላት በተያዘች ጊዜ ስለነበሩት ባንዶችና፣ እናንተም መካከል በትግሉ ጊዜ ራቢጣ የነበሩ ናቸው፣ ስለሚባሉት ሰዎች የጠቀስከው ታሪክ፣ የአስተዳደሩን ሥርዓት እየጣስክ የበላይህን ትዕዛዝ አልቀበልም፣ ለምትለው ጉዳይ አይረዳህም:: እኔ በአስተዳደጌም ሆነ በውትድርና ሞያዬ በዲሲፕሊን ስለማምን፣ አለአግባብ የምክትል እንደራሴውን ሥልጣን ስትጋፋ፣ ካንተ ጋር አልቆምም:: ነገር ግን፣ ምክትል እንደራሴው አንተን ለማጥቃትና ሥራህን ለመበደል ሲሞክሩ ካየኋቸው ካንተ ጋር እቆማለሁ:: ..... አሉኝ:: የጄኔራል ዐቢይ አነጋገር ትርጉሙ፣ አንተን ከጠላትህ ከተስፋዮሐንስ ለማላቀቅ አልችልም ማለታቸው ስለሆነ፣ ሕይወቴን ከተስፋዮሐንስ መላቀቅ ያለብኝ እኔው ራሴ ነኝ ..... » ብሎኝ፣ ከአጠገቤ ራቀ:: እኔም ተከትዬ ለማጽናናትና ለመምከር ብሞክር አላዳምጥም አለኝ:: ወዳጆቹ እንዲመክሩትና እንዲያበርዱት ለብዙዎቹ ወዳጆቹ ነገርኩ:: እነሱም አልቻሉም:: አንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የተድላ ሕይወት ማለፉን ስሰማ እጅግ ተጸጸትኩ:: ..... ተድላ ዕቁቢት በሥልጣኑ ዘመን ያንን ሁሉ ጠላት ያፈራው በጨካኝነቱ ነው ብለው፣ የሚያምኑት ሰዎች ጥቂቶች አለመሆናቸውን አውቃለሁ:: የአንድነት ተቃዋሚዎቹን እያሳደደ ያለ ርህራሄ ማስቃየቱን እኔም አልክድም:: ይሁን እንጂ ይህን ሁሉ የፈጸመው በአረመኔነት ጠባይ ሳይሆን ለአንድነት ሲል ነው ...... » ብለው፣ ፊታውራሪ ኪዳነማርያም ጎይሌ አስተያየታቸውን ሰጥተውኛል::

ኤርትራ፣ አሥራ አራተኛዋ ጠቅላይ ግዛት ሆና ከታወጀች ከሰባት ወራት በኋላ፣ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ አንድነት፣ በታጋይነቱና በኃይለኛነቱ እጅግ የታወቀው፣ ብርጋድየር ጄኔራል ተድላ ዕቁቢት በገዛ ራሱ ሕይወቱን አሳለፈ ተብሎ፣ በኢትዮጵያ ራዲዮ ሲነገር፣ ከፍ ያለ ድንጋጤ ያልደረሰበት የለም:: ሕይወቱን በገዛ ራሱ ለማጥፋቱም ተጠራጣሪዎቹ ጥቂቶች አልነበሩም::

በኢትዮጵያ አቆጣጠር ረቡዕ ሰኔ 5 ቀን 1955 ዓ.ም (በአውሮፓ አቆ. 12-06-63) ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ፣ የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ ሚኒስትር ዶ.ታ ደጃዝማች ከፍሌ ዕርገቱ እኔ ቢሮ ስልክ ደውለው፣ « ..... የኤርትራ ፖሊስ አዛዥ ጄኔራል ተድላ ዕቁቢት በዛሬው ዕለት ሕይወቱን በገዛ ራሱ አሳልፏል ...... » ተብሎ በራዲዮ ይነገር አሉኝ:: በዚያን ጊዜ እኔ የኢትዮጵያ ራዲዮ የብሔራዊው ፕሮግራም ኃላፊ ነበርኩ:: በበኩሌ የደረሰው አደጋ ምን ያህል አስደንጋጭና የማይጠበቅ መሆኑን ለደጃዝማች ከፍሌ ከገለጽኩላቸው በኋላ፣ እጅግ የታወቀው

የኤርትራ ፖሊስ አዛዥ እንዲሁ በደፈናው ራሱን ገደለ ብሎ ማውራቱ፣ በሕዝብ ዘንድ ብዙ ትርጉም ስለሚፈጥር፣ የአሟሟቱ ሁኔታ ምን እንደሆነ ቢገለጽ ይሻላል አልኳቸው:: ደጃዝማች ጥቂት ካዳመጡኝ በኋላ፣ « ..... ሀሳብህን እደግፋለሁ:: ግን የአሟሟቱን ምክንያት መግለጽ ሳያስቸግር አይቀርም:: እስቲ .... ለማናቸውም ..... አሥመራ ደውልና ጄኔራል ዐቢይን አማክረው ...... » አሉኝ:: ወዲያው አሥመራ ቢተመንግሥት ደውዬ ይህንኑ ሀሳብ ለእንደራሴው አመለከትኩ:: « ...... የኤርትራ ፖሊስ አዛዥ ለበላዩ ባለሥልጣን አልታዘዝም ብሎ ስለአስቸገረ፣ ከቦታው መዛወር እንዳለበት ነግሬው ነበር:: ይህንንም አልቀበልም ብሎ ለማመፅ መዘጋጀቱ ተደረሰበት:: በዚህ ጊዜ የዲሲፕሊን እርምጃ የሚወሰድበት መሆኑን ሲያውቀው፣ በቢሮው ውስጥ ሆኖ በመሣሪያ ሕይወቱን አሳለፈ:: ታሪኩ ባጭሩ ይኸው ነው:: ከመሞቱ በፊት ለዚህ የበቃበትን ምክንያት በጽሑፍ የተወው ማስታወሻ እንዳለ፣ ወይም ለቅርብ ጸሐፊው የተናገረው ቃል መኖር አለመኖሩን ለማወቅ ምርመራ በመደረግ ላይ ነው:: ..... በእኔ በኩል፣ ዛሬ ማታ በራዲዮ የሚነገረው፣ በገዛ ራሱ ሕይወቱን ማጥፋቱንና፣ የአሟሟቱንም ምክንያት ለማወቅ የፖሊስ ምርመራ መቀጠሉን ብቻ ነው ...... » ብለው፣ ሌፍተናንት ጄኔራል ዐቢይ አበበ የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ በነገሩኝ መሠረት፣ ዜናው ባጭሩ ለሕዝብ ተገለጸ::

በዚህ አኳኋን፣ የጄኔራል ተድላ ከዚህ ዓለም መለየት በራዲዮ ከተነገረ በኋላ፣ ስለአሟሟቱ በሕዝቡ ዘንድ የሚሠራጩት ልዩ ልዩ የተተራመሱ ዜናዎች፣ አሥመራንና አዲስ አበባን አጥለቀለቁት:: ከነዚህም ውስጥ፣ በሁለት ዓይነት የቀረቡት ወሬዎች ወደ እውነቱ ይጠጋሉ ተብለው ተገመቱ:: የመጀመሪያው፣ ተድላ ዕቁቢት በፌዴሬሽኑ መፍረስ በጣም ተቆጭቶ ራሱን ገደለ ሲል፣ ሁለተኛው ደግሞ፣ እንዲታሰር ወታደር በተላከበት ጊዜ፣ እጄን አልሰጥም ብሎ ሲታኮስ ተገደለ የሚለው ነው::

ብዙውን ጊዜ በአገራችን፣ አንዳንድ የታወቁ ሰዎች በድንገት ሲሞቱ ወይም ሲታሰሩ፣ እውነተኛው ጉዳይ ተገልጦ በራዲዮ ስለማይነገር፣ ሕዝቡ የሚመስለውን እየፈጠረ ማውራቱ አዲስ ነገር አይደለም:: በመሠረቱ፣ የኤርትራ ፖሊስ አዛዥ አሟሟት ትክክለኛው ዜና፣ እንደራሴው ለኢትዮጵያ ራዲዮ የብሔራዊ ፕሮግራም ሹም የገለጹት ነው:: እርግጥ፣ ተድላ ዕቁቢት ሕይወቱን ከማጥፋቱ በፊት፣ በጣም ተበሳጭቶ ቢሮውን ሲዘጋ፣ « ..... የኤርትራን ሕዝብ አሳስተነዋል:: የሠራነው ሁሉ ልክ አይደለም ...... » የሚል ቃል መናገሩ ታውቋል:: ይሁን እንጂ ሕይወቱን የሰዋበት ዋናው ምክንያት፣ እሱ ራሱ ዋና አርበኛ በሆነበት በፌዴሬሽኑ መፍረስ ተበሳጭቶ ነው ማለት አይቻልም::

የምክትል እንደራሴውን ሥልጣን አልቀበልም በማለቱ ወደ አዲስ አበባ እንዲዛወር መወሰኑን የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ከነገሩት በኋላ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ከማንም ጋር አልነጋገርም ብሎ፣ ከቢሮው ገብቶ በሩን ዘጋ:: ይህ እርምጃ የአመፅ ተግባር ሆኖ ስለተቆጠረ፣ እንዲታሰር ተወሰኖ፣ የሚይዙት ወታደሮች ወደ ፖሊሱ አዛዥ ቢሮ ተላኩ:: ሰውየው ቢሮውን ዘግቶ ያደፈጠ ስለሆነ፣ የተላኩት ወታደሮች ሁኔታው አስግቷቸው የታዘዙትን ሳይፈጽሙ ተመለሱ:: በዚህ ጊዜ፣ ጄኔራል ዐቢይ ሀሳብ ገባቸው:: ተድላን በስልክ አነጋግረው መንፈሱን ለማብረድ ደጋግመው ሙከራ ቢያደርጉም፣ ተድላ አላነጋግርም አላቸው:: ቢቸግራቸው፣ የጽሕፈት ቤቱን ኃላፊ ክንፈ ተስፋጋብርን ጠርተው፣ እባክህ ምከረውና እኔም ላነጋግረው ብለው ጠ

የቆት:: ክንፈም በበኩሉ ሞክሮ አልተሳካለትም:: ተድላ ቢሮውን ዘግቶ አሻፈረኝ አለ::

ከጥቂት ሰዓቶች በኋላ፣ ኮሎኔል ከበደ ያዕቆብ (ኋላ ሜጀር ጄኔራል) የሁለተኛ ክፍለ ጦር ከፍተኛ መኰንን፣ ከኤርትራ ፖሊስ ምክትል አዛዥ ከኮሎኔል ዘርዓማርያም አዛዚ እና ከተድላ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ከክንፈ ተስፋጋብር ጋር ሆነው፣ ወደ ተድላ ዕቁቢት ቢሮ አመሩ:: ምን ለማድረግ? ..... ተድላን መክሮ እጅህን በሠላም ስጥ ለማለት:: አሻፈረኝ ቢል ? ..... ሌላው እርምጃ በእንደራሴው ይወሰናል:: ...... በኮሎኔል ከበደ ያዕቆብ የሚመሩት መልዕክተኞች ከፖሊሱ አዛዥ ጽሕፈት ቤት ሳይቃረቡ፣ አንድ ትልቅ የመሣሪያ ድምጽ ተሰማ:: ተድላ ቢሮውን ዘግቶ ባነገበው ኡዚ ሕይወቱን አሳልፎ ጠበቃቸው::

ተድላ ዕቁቢት ወደ አዲስ አበባ እንዲዛወር መወሰኑን ጄኔራል ዐቢይ ሲነግሩት፣ ከችግሩ ተገላገልኩ ብሎ ደስ ይለዋል እንጂ፣ በዚህ፣ ብስጭቱ ግሉ ሕይወቱን እስከ ማጥፋት ያደርሳል ብለው አላሰቡም:: ቀደም ሲል ተድላ ዕቁቢት በተስፋዮሐንስ ሥልጣን በሚበሳጭበት ጊዜ፣ «አንተንና ሥራህን የሚበድል ነገር ሲሠሩ ካየኋቸው ካንተ ጋር እቆማለሁ» ሲሉ ጄኔራል ዐቢይ የሰጡት ቃል ይታወሳል:: በመጨረሻው የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ እንደወሰኑት፣ ዝውውሩን ተቀብሎ አዲስ አበባ ቢመጣ ኖሮ፣ ንጉሠ ነገሥቱ በጣም ስለሚወዱት፣ ብዙ ደስ የሚለው ነገር እንደሚያገኝ የታወቀ ነበር:: ምን ይሆናል ? አልኸኛና ትዕግሥት የሌለው ሰው በመሆኑ፣ ብቻውን ሲያስብ በማናቸውም በኩል የወደፊት ሕይወቱ ጭለማ ሆነበት::

ያ-- የኢትዮጵያንና የኤርትራን ፍጹም አንድነት ከልቡ የሚያምን ጉበዝ፣

ያ-- ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ከፈጣሪ ጋር እያወዳደረ የሚያመልክባቸው ሰው፣

ያ-- የኤርትራንና የኢትዮጵያን አንድነት የሚቃወሙትን ሁሉ በወረንጦ እየለቀመ የሚያጠፋ ኃይለኛ መኰንን፣

<u>በተወለደ በሃምሣኛው ዓመት፣ እሱ ራሱ ብዙ የለፋበት የኤርትራና የኢትዮጵያ ፍጹም ውህደት በተፈጸመ በሰባተኛው ወር፣ መጨረሻው እንደዚህ አሳዛኝ ትራጄዲ በመሆኑ፣ በተለይ ከአንድነት ወገኖች ያላዘነለትና ያልተፀፀተ የለም::</u>

ለተድላ ሞት ዋና ምክንያት ናቸው የተባሉት ተስፋዮሐንስ በርሄ ግን፣ ፌዴሬሽኑ ከፈረሰ በኋላ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ታማኝ ሆነው፣ <u>የኤርትራ ምክትል እንደራሴነቱን ሥልጣን ለአሥራ ሁለት ዓመታት እንደያዙ ቆዩ::</u> በዚህ ብቻ አልቆመም:: በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ ላይ ለጥቂት ወራቶች ተቋቁመው ለነበሩት ለልጅ እንዳልካቸው መኰንን እና፣ ለልጅ ሚካኤል እምሩ ካቢኔዎች፣ ተስፋዮሐንስ በርሄ የማዕድን ሚኒስትር ሆነው ነበር::

# መጨረሻው ?

ማንም ሰው እንደሚያውቀው የኤርትራ ጉዳይ መጨረሻው ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ ነፃ መንግሥት መሆን ነው:: በመቅድሙ ላይ እንደተገለጸው ይህ መጽሐፍ የሚያቀርበው ዝርዝር ታሪክ፣ ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ የተደረገውን ረዥም ጉዞና የአሥሩን ዓመታት የፌዴሬሽን ሕይወት ብቻ ነው::

በተባበሩት መንግሥታት የተወሰነው የፌዴሬሽን አስተዳደር፣ የኤርትራ ሕዝብ ያልጠየቀውና የቀዳማዊ ኃይለሥላሴም መንግሥት በደስታ ያልተቀበለው በመሆኑ፣ አንድነቶች የማፍረሻውን ጥናት የጀመሩት ሕገ መንግሥቱ በሥራ ላይ እንዲውል በጸደቀ ማግሥት ነበር:: ከአሥር ዓመታት በኋላ ፌዴሬሽኑ ፈርሶ አስተዳደሩ ሲዋሀድ፣ ኢትዮጵያዊነት የበለጠ ይጠነክራል፣ የአንድነት ሕይወት ይዳብራል፣ የልማት ዕድገት ይፋጠናል፣ ብለው ያሰሙት ሰዎች በመጨረሻው የጠበቁትን አላገኙም::

መስከረም 11 ቀን 1952 ዓ.ም በፌዴሬሽን የመቀላቀሉ በዓል ሲከበር፣ የመረብ ምላሽ ሕዝብ ያንን ሁሉ የጋለ ስሜቱን የገለጸው፣ ከአሥመራ እስከ አዲስ አበባ « ተዘወሪ መኪና » እያለ ያዜመውና ከደስታው ብዛት ተንስቅስቆ ያለቀሰው፣ ከባዕድ አገዛዝ ወጥቼ፣ ኢትዮጵያዊነቴን አገኘሁ ብሎ ነው:: በዚያን ጊዜ ይህ ሕዝብ፣ ፌዴሬሽን የተባለው ቃል ምን ትርጉም እንዳለው፣ ከሌላው ከኢትዮጵያ ሕዝብ አስተዳደር የሚለየው በምን ጉዳይ እንደሆነ፣ የሚያውቀው ነገር አልነበረም:: ለሕዝቡ የተነገረውና ሕዝቡም ከልቡ ያዳመጠው፣ ኤርትራ አቀድሞው ታሪኳ ተመልሳ፣ ኢትዮጵያዊነቷንና ነፃነቷን አገኘች የተባለውን የምሥራች ቃል ነው::

የኤርትራ የወደፊት ዕድል፣ በአራቱ ኃያላን አገሮችና በዓለም መንግሥታት ማህበር በሚመረመርበት ጊዜ፣ ኢትዮጵያን አንፈልግም ያሉት የፖለቲካ ማህበሮች፣ መቀላቀሉ በፌዴሬሽን እንዲሆን ከተወሰነ በኋላ፣ እነሱ የሚወዱት ባይሆንም ተቃውሞአቸውን ለመቀጠል አላመቻቸውም:: « ..... በዓለም ማህበር ፍርድ ተወስኖ የተሰጠን የአቶኖሚ መብት በትክክል በሥራ ላይ እንዲውል ከተደረገልን ተቃዋሚነታችን ምንም ትርጉም አይኖረውም .... » ብለው፣ ከአስተዳደሩ ጋር ለመተባበር አንገታቸውን ደፍተው ነበር:: ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ብዙ አልዘለቀም:: የአጥባቂ አንድነት ወገኖች፣ የፌዴሬሽኑ መንፈስ ሥር ሳይሰድ ባጭሩ እንቅጠፈው ብለው በተነቃነቁ ጊዜ፣ ተቃዋሚዎቹ፣ በተለይ የእስላም ሊግ አባሎች፣ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና ለአራቱ ኃያላኖች፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን እየወነጀሉ ማመልከታቸውን ቀጠሉ::

በዚያን ሰዓት የተድላ ባይሩ መንግሥት፣ አንድ ጊዜ ከአንድነቶች ጋር ሆኖ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ የሚፈልግ ሲመስል፣ ሌላ ጊዜ ከፌዴራሊስቶቹ ጋር ተሠልፎ አቶኖሚውን ለማጠንከር ሲሞክር፣ አፍራሾቹ የሚመኙትን ለማድረግ ሳይመቻቸው ሶስት ዓመት አለፈ:: እንደ እውነቱም ከሆነ፣ በተድላ ባይሩ አስተዳደር ዘመን፣ አጥባቂ አንድነቶች ፌዴሬሽኑን አፍርሰውት ቢሆን ኖሮ፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ላይ የሚነሱት ጠላቶች ጥቂቶች አይሆኑም ነበር:: ፌዴሬሽኑ አይጠቅመንም ብለው የሚያፈርሱት እራሳቸው ኤርትራውያኖቹ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃ ቢቀርብ እንኳ፣ ኃያላን አገሮች ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ከደሙ ንጹሕ

ናቸው ብለው፣ እንደማይምሯቸው የታመነ ነው:: የተባበሩት መንግሥታትም፣ የዓለም ሸንጐ የሰጠው ውሳኔ አልተከበረም ብሎ፣ ኢትዮጵያን ለሌሎቹ ለድሆች አገሮች መቀጣጫ ለማድረግ፣ ኃይሉንና አቅሙን ከማሳየት ወደ ኋላ አይልም ነበር::

በመሠረቱ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና መንግሥታቸው፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለኤርትራ ያዘጋጀውን የኦቶኖሚ አስተዳደር በተግባር እንዲቀጥል አያደርጉም ተብለው የተጠረጠሩት፣ ጠቅላላው ጉባኤ የመጨረሻውን ፍርድ ከመስጠቱ በፊት ነው:: ታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም፣ የሃምሣ ዘጠኝ አገሮች እንደራሴዎች የኤርትራን ፌዴራል አክት እንዲያጸድቁ ሲጠየቁ፣ በጣልያን ፕሮፓጋንዳ ተመስጠው፣ በኃይለሥላሴ መንግሥት ላይ ዕምነት የለንም በማለት ለመቃወም የተዘጋጁት አገሮች ጥቂቶች አልነበሩም:: በአምስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ታሪክ ውስጥ በአጭሩ እንደተገለጸው፤ የጃንሆይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ የቀረበው ሬዞሉሽን በተቃዋሚዎቹ ዲስኩር ከመበላሸቱ በፊት፤ የመጀመሪያው ተናጋሪ ሆነው የሰጡት መግለጫ፣ « ..... ለኮሌክቲቭ ሴኪውሪቲ ያላትን ዕምነት ሳታወላውል ጠብቃ የምትኖረው ኢትዮጵያ፣ ለኤርትራ አስተዳደር የተባበሩት መንግሥታት የሚጥልባትን አደራ በትክክል ለመፈጸም ተዘጋጅታለች ...... » ብለው በማረጋገጣቸው፤ የብዙዎቹን አገሮች አስተያየት እንዳሻሻለው ይታወሳል:: ሆኖም አንዳንድ ታላላቅ አገሮች በተለይም እንግሊዝና ፈረንሣይ ድጋፋቸውን ቢሰጡም፣ ስለ አፈጻጸሙ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ላይ ያደረባቸውን ጥርጣሬ አላስወገዱም::

የኤርትራን ሕገ መንግሥት ያዘጋጀው የመንግሥታቱ ድርጅት ኮሚሽነር አንሴ ማቲየንሶ፤ (ANZE MATIENZO) ሥራውን በፈጸመ ማግሥት፣« .... የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ካቢኔ ይህን ኦቶኖሚ አክብሮ ያቆየዋል ብዬ አላምንም ...... » ሲል፣ ለኃያላን መንግሥታቶች በምሥጢር ራፖር አስተያየቱን ሰጥቷል:: የፌዴሬሽኑ አስተዳደር እንደተጀመረም፣ አሥመራ ላይ ያሉት የታላላቆቹ መንግሥታት ቆንስሎችና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ወኪል፣ የኢትዮጵያን መንግሥት አሰራር በጥብቅ መከታተል ጀምረው ነበር:: በተለይ እንግሊዝና ፈረንሣይ ጣልያኖች በሚሰጧቸው መረጃ እየተመሩ፤ የማህበረ ፍቅሪ ሀገር አባሎች ፌዴሬሽኑን ለመሰረዝ የሚያደርጉት ሙከራ፣ ከገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት እየተገፋ ነው በማለት፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ከማስጠንቀቅ አልተቆጠቡም:: ፌዴሬሽኑ ቢፈርስ አደገኛነቱንና በኢትዮጵያም ላይ የሚያስከትለውን ጣጣ ጃንሆይ እንዲገነዘቡት በግልጽ አስረድተዋል:: ንጉሠ ነገሥቱም በበኩላቸው፣ <u>የኤርትራን ፌዴሬሽን፣ ጥቅሙንና ጉዳቱን ለይተው ለማኖርም ሆነ ለማፍረስ፣ ኃላፊነቱም ሆነ መብቱ የኤርትራ ሕዝብ እንደራሴዎች እንጂ፣ እሳቸውን በቀጥታ የሚመለከት አለመሆኑን፤</u> በየጊዜው እያስረዱ፣ የሚቀርብላቸውን ማስፈራሪያ ከመመከት አልተበገሩም:: በዚህ አኳኋን ጊዜው እየጨመረ ሲሄድ፣ የኃያላን አገሮችና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ማስፈራሪያ ስለተዳከመ፤ ከአሥር ዓመታት በኋላ ፌዴሬሽኑ ሲፈርስ፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ላይ እንኳንስ ጥቃት፣ ጥያቄ እንኳን አልቀረበም:: ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም በኅዳር 15 ቀን 1962 ዓ.ም ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ የኤርትራ ፓርላማ ያሳለፈውን ውሳኔ ካጸደቁ ከስድስት ወር በኋላ፣ <u>በግንቦት 25 ቀን 1963 ዓ.ም የአፍሪካን አንድነት ቻርት አዲስ አበባ ላይ በማስፈረማቸው፤ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ብቻ ሳይሆኑ የአፍሪካውያኖችም አንድነት መሥራች አባት ተብለው በመላው ዓለም ተሞገሱ::</u> ስለ ኤርትራ ፌዴሬሽን መፍረስ ብዙ ኤርትራውያኖች ሲናገሩ፣ ሥልጣናቸውን ለማስፋፋት ትልቁን

ስህተት የፈጸሙት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ናቸው ይላሉ:: ትክክለኛውን አስተያየት ለመስጠት ጉዳዩን ጠለቅ አድርጐ መመልከት ያስፈልጋል::

በመከላከያና በውጭ ጉዳይ፣ በፊናንስና በመገናኛዎች በኩል፣ ሕገ መንግሥቱ ለንጉሠ ነገሥቱ የሰጠው ሥልጣን ብጣም ሰፊ ስለሆነ፣ ተፈሪ መኰንን ምንም የጐደለባቸው ነገር አልነበረም:: በዚያን ዘመን በኤርትራ ውስጥ እንዲፈጸም ጃንሆይ ፈልገው፣ በሥልጣን እጥረት ምክንያት ማድረግ ያልቻሉት ዐቢይ ጉዳይ ምን ነበር ? ተብሎ ቢመረመር፣ ምንም ዓይነት አጥጋቢ መልስ አይገኝም:: እርግጥ በተድላ ባይሩ ጊዜ፣ ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የተለየ የኤርትራ ባንዲራ በመውለብለቡ፣ የአስተዳደሩም መጠሪያ « መንግሥቲ ኤርትራ » እየተባለ ነጋሪት በመጐሰሙ፣ ንጉሠ ነገሥቱን ቅር እንዳላቸው ያልተረዳ የለም:: ሆኖም እነዚህን ሁለት ጉዳዮች ፓርላማው እንዲሰርዛቸው ጃንሆይ አለመጠየቃቸውን፣ አስፍሐ ወልደሚካኤል የኤርትራ አስተዳዳሪ ደጋግመው አረጋግጠዋል:: እንደዚሁም ሌላ ምርጫ በማጣት ሳይወዱ በግድ ተቀብለው በንጉሣዊ ፊርማቸው ያጸደቁትን የኤርትራን ፌዴሬሽን አፍርሱልኝ ብለው፣ መሪዎቹን ተድላን ሆነ አስፍሐን፣ በጽሑፍ ሆነ በቃል፣ በቀጥታ መጠየቃቸውን የሚያመለክት አንዳችም ማስረጃ እስካሁን አልተገኘም:: እንደ እውነቱም ከሆነ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የኤርትራ አስተዳዳሪዎችና የፓርላማ አባሎች ፌዴሬሽኑን እንዲያፈርሱ ለማዘዝ የሚያስችል ቀጥታ ሥልጣን አልነበራቸውም:: በዚህ ጉዳይ ለተደረገው ውሳኔ <u>የመጀመሪያዎቹ ኃላፊዎች የኤርትራ ሕዝብ እንደራሴዎችና የአስተዳደሩ ባለሥልጣኖች መሆናቸው ግልጽ ነው::</u> የፓርላማውን አባሎች፣ ሕዝቡ እንደራሴዎቹ አድርጐ የመረጣቸው ሕገ መንግሥቱን ተመርኩዘው መብቱንና ደህንነቱን እንዲያስከብሩለት፣ ቢያስፈልግም እንዲሰዉለት ስለሆነ፣ ኃላፊነታቸው በቀጥታ ለሕዝቡ እንጂ፣ የፌዴራሉ መንግሥት መሪ ለሆኑት ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አለመሆኑ ለማንም የተሰወረ አይደለም:: የፌዴሬሽኑ መፍረስ ለሕዝቡ ሠላምና ብልፅግና ይጠቅማል ብለው የወሰኑት እንደራሴዎች፣ ያለ አንዳች ግዴታ በፈቃዳቸውና በእምነታቸው ተመሥርተው መሆኑን የኤርትራ ሕዝብ በጥልቅ መረዳት አለበት:: ይሁን እንጂ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ አልፈለጉም ነበር ብሎ መናገር አይቻልም:: አፍራሾቹም ጥረት በሚያደርጉበት ጊዜ ከንጉሠ ነገሥቱ የሞራል ሆነ የማናቸውም እርዳታ አልተሰጣቸውም አይባልም:: ከሰልሣ ስምንቱ የምክር ቤት አባሎች ውስጥ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ ብዙ የለፉት የአንድነት ወገኖች ዕድሜያቸውን ሙሉ ባመኑበት በኢትዮጵያዊነት ጥልቅ መንፈስ መሆኑ ባያከራክርም፣ ቀድሞ ተቃዋሚዎች ከነበሩት ወገኖች መካከል በገንዘብም ሆነ በሹመት የተደለሉ አልነበሩም ብሎ መከራከር ያዳግታል:: ንጉሠ ነገሥቱም ተፈሪ በሆነው ግርማ ሞገሳቸው በማይመለከታቸው በኤርትራ የውስጥ ጉዳይ፣ አልፎ አልፎ እየገቡ አላሽቆጠቆጡም አላርበተበቱም አንልም:: ዞሮ ዞሮ ማየት የሚያስፈልገው ለኢትዮጵያ አንድነት ሲባል ሆነ ለግል ጥቅም፣ ፌዴሬሽኑ ፈርሶ የአስተዳደሩ ውህደት የተፈጸመው በኤርትራውያኖች ሥልጣን ስለሆነ የመጀመሪያዎቹ ኃላፊዎች እነሱ ራሳቸው መሆናቸውን ነው::

በሁለተኛ ደረጃ ኃላፊነቱ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ይመለከታቸዋል ቢባል፣ ንጉሠ ነገሥቱ ምን ማድረግ እንደነበረባቸው ማስረዳት ያስፈልጋል:: አንድነቶች ከቀድሞዎቹ ተቃዋሚዎቻቸው ጋር አንድ ድምፅ ሆነው ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ ጃንሆይ እንዲፈቅዱላቸው ሲያመለክቱ፣ «የተሰጣችሁን የመተዳደሪያ አቶኖሚ ማፍረስ አይገባችሁም» ብለው ሊያቆሟቸው ይገባ ነበር ለማለት ይቻላል:: ነገር ግን

ይህ ዓይነቱ አስተያየት ከንጉሡ በላይ ንጉሥ ሆኖ እንደመቆም የሚቆጠር ስለሆነ፣ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሚጠበቅ አይደለም። ..... አቶኖሚዬን ይዤ በራሴ ከምተዳደር፤ በጌታዬ ሥልጣን ሥር መሆንን እመርጣለሁ ብሎ የሚቀርበውን ሕዝብ፤ « የለም የተሰጠህን መብት መጠበቅ አለብህ » ብሎ የሚያግድ « አቶክራሲ » በዚህ ዓለም ታይቶ ስለማይታወቅ፣ በእኔ በዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ አስተያየት በኤርትራ ፌዴሬሽን መፍረስ ጉዳይ፣ ተፈሪ መኰንን እንግዳ ናቸው ባይባልም የመጀመሪያው ተወቃሽ ሊሆኑ አይገባቸውም።

ታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት አምስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትቀላቀል የወሰነውን፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በሙሉ ደስታ አለመቀበላቸውን ለማንም አልሸሸጉም። ቀጥሎም በተድላ ባይሩ ዘመነ መንግሥት ፌዴሬሽኑን ወደ ማፍረስ የሚያዘነብል አንድ ምልክት ሲያዩ፣ በንቃት እንደሚመለከቱ እና ለማበረታታትም እንደሚጥሩ፤ ለማንም የተደበቀ አልነበረም። በመጨረሻም የተድላ ባይሩ መንግሥት ወድቆ የአስፍሐ ሲተካ፤ የታመኑት አገልጋያቸው ቀስ በቀስ የልባቸውን እንደሚያደርሱላቸው ተስፋ ማድረጋቸው ምሥጢር አልነበረም። ነገር ግን፤ ፌዴሬሽኑ የፈረሰው፣ ፓርላማው በጦር ኃይሎች ታንክ ተከቦ፣ መማክርቶቹ ማስፈራሪያ ተደርጐባቸው የተፈጸመ ነው እያሉ፣ ሕዝቡን ለማሳሳት በአንዳንድ ኤርትራውያኖች የተጻፉትን ተመልክተን ታዝበናል። በዚህ ጉዳይ እውነተኛው ታሪክ እየተሸሸገ፣ የፈጠራው ታሪክ እንዳይቀጥል፣ ዛሬ ከኛ ተለይተው ነፃ የሆኑት ኤርትራውያን ወንድሞቻችን ምርቱን ከግርዱ ለይቶ ማወቅ ይገባቸዋል።

..... ኅዳር 15 ቀን 1962 ዓ.ም ፌዴሬሽኑ በፈረሰበት ዕለት ያ ሁሉ በዓል በፓርላማውና በቤተመንግሥቱ ሲከናወን፣ እንኳንስ በታንኮች ላይ መድፍ የጠመዱ የጦር ኃይሎች ይቅሩና፣ ሽጉጥ የታጠቁ የጸጥታ ፖሊሶች እንኳን በብዛት አልነበሩም። ..... በሕዝብ የተመረጡት የኤርትራ ፓርላማ አባሎችና አስተዳዳሪዎች ፌዴሬሽኑን ያፈረሱት፣ የታሪክ ከላሾች እንደሚሉት በቀዳማዊ ኃይለሥላሴና በመንግሥታቸው ተገድደው ሳይሆን፣ በራሳቸው ሙሉ ፈቃድና ኃላፊነት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

እርግጥ፤ የኤርትራ ጉዳይ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ላይ ችግር የፈጠረውና በፕሮፓጋንዳ ረገድ ትልቅ ዝና ያገኘው ከፌዴሬሽኑ መፍረስ በኋላ ነው። ከዚያ በፊት በተለያየ አስተዳደር ከምንኖር፣ አንድ ላይ ብንጠቃለል ይሻላል ሲሉ የነበሩት ብዙዎቹ ኤርትራውያኖች፣ ፌዴሬሽኑ ከፈረሰ በኋላ የኃይለሥላሴ መንግሥት መብታችንን ገፈፈው ለሚለው ጩኸት አዳማቂዎች ሆነዋል። በተለይ በኤርትራ ውስጥ ታክስና ግብር ከፋይ የሆነው ሕዝብ፤ ለሁለት መንግሥት (ለኤርትራና ለኢትዮጵያ) ከምንገብር፣ አስተዳደሩ አንድ እንዲሆን እንመርጣለን እያሉ ለጥቅማቸው የሚነጫነጩት ጥቂቶች አልነበሩም። ኋላ ግን የሚፈልጉት ሲሆንላቸው፣ ፌዴሬሽኑ በመፍረሱ የሕዝቡ መብት ተነክቷል በማለት፤ ተቆርቋሪዎች ሆነው ብቅ አሉ። ሌሎች ደግሞ በኢትዮጵያ መንግሥትና ኤርትራን ነፃ ለማውጣት በተቋቋመው የፖለቲካ ድርጅት መካከል፤ ወዲያና ወዲህ እያማቱ ለሁለቱም ወገኖች ታማኝ በመምሰል በሁለት ቢላ ለመብላት የተሯሯጡ ነበሩ። በዚህ ዓይነቱ ጥቅም ላይ የተሰማሩት ሰዎች፣ የኢትዮጵያ መንግሥት በጥሩ መረጃ የሽፍቶቹን ፈለግ አግኝቶ እንዲያጠፋቸው፤ ሽፍቶቹም ጠንክረው የኢትዮጵያን መንግሥት በማዳከም ወደ ግባቸው እንዲጠጉ ፍላጐት አልነበራቸውም። ለእነሱ

ጥቅም የሚመቸው ከዚህም ከዚያም አብረን ነን እያሉ፣ ፕሮብሌሙ መፍትሔ ሳያገኝ ዳመናውን እንዳዘለ ሲቆይላቸው ነበር።

የነፃ አውጭ ድርጅቱም ከልዩ ልዩ አገሮች ገንዘብ ለመሰብሰብ እንዲመቸው፣ ኤርትራን በልዩ ልዩ የታሪክ ቀለም እየቀባ ነገደባት።

-- በነዳጅ ዘይት ሀብት በከበሩትና በጠገቡት አገሮች ዘንድ፣ የኤርትራ ሕዝብ ስማኒያ በመቶው (80%) ዘሩ ዓረብ፣ ቋንቋው ዓረብኛ ሀይማኖቱ እስላም ነው ተብሎ ታመነበት።

-- በእስላም አገሮች ዘንድ፣ የኢትዮጵያ የክረስቲያኑ ሕዝብ መሪ የሆኑት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ የአፄ ዮሐንስን ፈለግ በመከተል፣ እስላም የሆነውን የኤርትራን ሕዝብ በመጨፍጨፍ ላይ ናቸው ተባለ።

-- ፕሮግሬሲስቶች በሚባሉት ዓረቦች ዘንድ (ኢራቅ፣ ሶሪያ ወ.ዘ.ተ .....) ዓረብነቷና እስላምነቷ የተረጋገጠላት ኤርትራ፣ ከኃይለሥላሴ መንግሥት ነፃ ወጥታ፣ ፓን አራቢዝምን እንድትከተል የነፃ አውጭው ድርጅት ብዙ እርዳታ ጉረፈለት።

-- ለሕዝብ እኩልነት የቆሙ ናቸው በሚባሉት በመስኮቦችና በቻይናዎች ዘንድ፣ የኤርትራ ሕዝብ የነፃነት ንቅናቄ ድርጅት፤ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ነው ተብሎ፣ ለመሣሪያዎችና ለደፈጣ ውጊያ የሚያገለግሉ የቴክኒክ እርዳታዎች ቀረቡለት።

-- ሊበራል በሆኑት በምዕራባውያን አገሮች ዘንድ ደግሞ፣ በተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ ለኤርትራ የተሰጣት የአቶኖሚ መብት፣ ያለ አግባብ ፈርሶ የአዲስ አበባ ፊውዳል አስተዳደር ወድቆባት በመስቃየት ላይ ነች ተብሎ፣ የሞራልና የፐብሊሲቲ እርዳታ አገኘበት።

በዚህ አኳኋን ለዚች ለፈረደባት ኤርትራ፤ ነፃ መንግሥት እንድትሆን የተነሳላት ድርጅት ሁሉ፤ አንድ ጊዜ በአባዲሶች ዘመን ኤርትራ የባግዳድ ካሊፋ ተገዥ የነበረች የዓረብ አገር ነች ብሎ ሲሰይማት፤ ሌላ ጊዜ የቱርኮች ቅኝና የግብፅ አካል የነበረች የእስላም አገር አድርጐ ሲያቀርባት፤ ከኢትዮጵያም ጋር የዘር ሆነ የባሕል፤ የታሪክ ሆነ አብሮ የመኖር ግንኙነት ያልነበራት ነች ሲላት፤ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ይህን ሁሉ ውሸትና የፈጠራ ታሪክ ችላ በማለት ለዓለም ባለማስረዳቱ፤ የኋላ ኋላ ብዙ ችግር ወደቀበት። ፕሮፓጋንዳ አንድ ጊዜ ደህና ሜዳ አግኝቶ ካጠቃ በኋላ፣ ዘግይቶ የሚሠራጨው ማስተባበያ ተደማጭነት ስለማይኖረው፣ የነ ኢድሪስ አዱምና የነ ሣልህ ሳቤህ ፕሮፓጋንዳ በኤርትራ እየነገደ፣ እውነተኛውን ታሪኳን በፈጠራ ታሪክ ሸፍኖ ለመኖር ጣረ።

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴም መንግሥት፣ በኤርትራ ውስጥ ብዙ የሥራ መስክ በመፍጠርና ሥራ ፈቱን በመቀነስ፣ በአስተዳደር ረገድም ለኤርትራውያኖቹ የተለየ አስተያየት በማድረግ የሚወስዳቸው እርምጃዎች፣ የነፃ አውጭ ድርጅቱን የሚያዳክምለትና የሚያጠፋለት መስሎ ታየው። በዚህ አስተሳሰብ በአስተዳደሩ ላይ አንድ የኤርትራ ተወላጅ በሥራ ቢያጠፋ ወይም ቢሰንፍ፣ እንዳልታየ ታይቶ

ይታለፋል እንጂ እርምጃ አይወስድበትም:: ወደ ታላላቆቹማ ሠፈር ጨርሶ የሚነካ አልነበረም። አለአግባብ የሆነ ውሳኔ ለማድረግ፣ አስፈላጊም ከሆነ ከፍተኛ ስሁተት ለመፈጸም ኤርትራዊ በመሆኑ ይፈቀድለት ነበር:: እዚህ ላይ በሐማሴን አውራጃ የአንድነት ማህበር የመማክርት ጉባኤ አባል የነበሩት ቄስ ሀብተሥላሴ ጉልበት፣ በዚያ በትግሉ ዘመን ለአዲስ አበባ ሕዝብ ባደረጉት ንግግር ውስጥ የጠቀሱትን ማስታወስ ይጠቅማል::

« ..... ለእናንተ ለኢትዮጵያውያን ወንድሞቼና እህቶቼ የማሳስባችሁ፣ ኤርትራውያን ወንድሞቻችሁና እህቶቻችሁ ኢትዮጵያዊነት የሚሰማቸው፣ እንደራሳችሁ አድርጋችሁ ስትይዟቸው ብቻ ነው:: ..... ተለያይቶ የኖረው የአንድ አገር ሕዝብ፣ እንደገና አንድነቱ እንዲመለስ በሚደከምበት በአሁኑ ሰዓት፣ ለሌላው ኢትዮጵያዊ የማይደረገውን፣ ለኤርትራውያኖቹ የተለየ መንከባከብና አስተያየት ብታደርጉላቸው፣ ባዕድነት እንጂ ኢትዮጵያዊነት የበለጠ ይሰማቸዋል ብላችሁ አታስቡ:: ...... የኤርትራ ሕዝብ ለኢትዮጵያዊነቱ የሚሞተውና የሚታገለው፣ በማያጠራጥረው የአንድነት ታሪኩና ባሕሉ ተመሥርቶ መሆኑን አስቡበት:: ..... »

በኤርትራ፣ የታወቁት የከንቲባ ጉልበት ልጅ፣ ቄስ ሀብተሥላሴ ጉልበት፣ ይህን ንግግር ያደረጉት በ1948 ዓ.ም አዲስ አበባ መጥተው በኤርትራና በኢትዮጵያ አንድነት ማህበር አዘጋጅነት፣ በሲኒማ እድዋ አዳራሽ በተደረገው የሕዝብ ስብሰባ ላይ ነው:: እኝህ ሀይማኖተኛና ጨዋ የነበሩት የአንድነት ታጋይ፣ ከልባቸው የሚያምኑበትን የኢትዮጵያንና የኤርትራን መቀላቀል ሳያዩ፣ በሕመም ምክንያት በመጋቢት 1949 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ናቸው::

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከ1962 ዓ.ም ጀምሮ፣ ኤርትራ መሠረተ ታሪኳ እንደ ሸሚዝ እየተለዋወጠ፣ በያለበት ሲነገድባት ከቆየች በኋላ፣ በ1993 ዓ.ም ነፃ መንግሥት ስትሆን « የዓረብ አገር » አልተባለችም:: ወይም «የእስላም ሬፑብሊክ» አልሆነችም:: ከዓረብ አገሮች እነ ኢራቅና እነ ሶሪያ፣ ከእስላም ሬፑብሊኮች እነ ፓኪስታን፣ ኤርትራን በየበኩላቸው ለመያዝ ያን ሁሉ ጥረት ሲያደርጉ ከኖሩ በኋላ፣ ዛሬ በሚያዩት ሁሉ ምን ተሰምቷቸው ይሆን ?

ለብዙ ዓመታት ምርምር በማድረግ የደከምኩበትን የዚህን መጽሐፍ የመጨረሻ ምዕራፍ ስደመድም፣ ሀሳቤን የማጠቃልለው በሚከተሉት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ነው::

1. ነፃነታችን ከፋሽስት ከተላቀቀበት ከ1941 ዓ.ም ጀምሮ፣ የተባበሩት መንግሥታት ፍርዱን እስከሰጠበት እስከ 1950 ዓ.ም ድረስ፣ ኤርትራውያን ወንድሞቻችን ወደ እናት አገራቸው ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ያደረጉት ትግልና የተቀበሉት ስቃይ ራሱን የቻለ አንድ የታሪክ መጽሐፍ የሚዘጋጅለት ነው:: ኢትዮጵያም ያለማቋረጥ ለብዙ ዓመታት ለልጆቿ ጠንክራ ባትሟገት ኖሮ፣ ለኤርትራውያን ወንድሞቻችን በዚያን ጊዜ የሚጠብቃቸው ዕድል፣ እንደ ሞቃዲሾ ሱማሌ፣ በኮሎኒያሊስት ጣልያን ሞግዚትነት ከመገዛት በስተቀር ሌላ መንገድ አልነበራቸውም::

2. በ1950 ዓ.ም የመንግሥታቱ ድርጅት የፍርድ ሸንጐ፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትቀላቀል የወሰነው፣ አንዳንድ



ለአንዲት ኢትዮጵያ በፅኑ ታጋይ
የጃንሆይ ታማኝ አገልጋይ

*« ... የሰው ትላቅነቱ ሳይወላውል ባመነበት ጸንቶ መገኘቱ ነው። አስፍሐ ወ/ሚካኤል ይህን ጠባይ አይተንበታል ... »*

(ቀ.ኃ.ሥ ሰኔ 1962 ዓ.ም)

*« ... እኔ የምሞተው በኢትዮጵያ መሬት ነው። ሥጋዬም የሚፈርሰው በምወዳት ኢትዮጵያ አፈር ነው ... »*

(አ.ወ.ሚ ነሐሴ 1993 ዓ.ም)

*« .. የሚያምኑበትን በትክክል ፈጽመው ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ታላቅ ኢትዮጵያዊ በመሆናቸው፣ ታሪክ ምንጊዜም የተከበረ ቦታቸውን ይጠብቅላቸዋል.. »*

(ከደራሲው)

ኤርትራውያኖች እንደሚሉት ታላላቅ መንግሥታቶች የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መንግሥት ለመርዳት ባደረጉት ጥረት አለመሆኑን እውነተኛው ታሪክ ቁልጭ ብሎ ያሳየናል።

ሀ/ ሁለት ጊዜ በተደረገ ጥናትና ምርመራ አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ኢትዮጵያዊነትን በመጠየቁ፣

ለ/ በኤኮኖሚ ረገድ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ካልተቀላቀለች በስተቀር፣ ራሷን ችላ ለመኖር የማትችል መሆኗ በዓለም ድርጅት ተጠንቶ በመረጋገጡ ነው።

3. እኛ ሳንጠይቅ፣ በውጭ ተንኮለኞች ተዘጋጅቶ የተጫነብን የፌዴሬሽን አስተዳደር፣ በኢትዮጵያዊነታችን ላይ « መለዮ » ስለፈጠረብኝ ይህንን አፍርሰን ከእናታችን ጋር መዋሀድ አለብን ብለው፣ በኅዳር 15 ቀን 1962 ዓ.ም የወሰኑት ኤርትራውያኖች ራሳቸው ስለሆኑ፣ <u>የዛሬዎቹ ታሪክ አቅራቢዎች፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ብቻ ለማውገዝ በመረባረብ ፋንታ፣ በታሪኩ ሂደት ላይ ጥልቅ ምርምር ቢያደርጉ ትክክለኛውን ሁኔታ ሊረዱ ይችላሉ።</u>

4. ኢትዮጵያ፣ እናቴ ነሽ ብለው የተጠጋትን ኤርትራውያኖች፣ ከሌሎቹ ልጆቿ አስበልጣ በትምህርት እንዲታነጹና የተሻለ ሕይወት እንዲያገኙ ያደረገችው ሰፊ ድካም፣ ምን ያህል እንደሆነ በማስረጃ ስለሚረጋገጥ፣ የዛሬዎቹ ኤርትራውያኖች ውለታዋን መዘንጋት የለባቸውም።

5. በ1993 ዓ.ም ነፃነታቸውን ያወጁት ኤርትራውያኖች ከግባቸው ለመድረስ የቻሉት፣ ለብዙ ዓመታት ታግለውና ተዋግተው መሆኑን የሚክድ የለም። የእነዚህም የነፃነት ታጋዮች አባቶቻቸውና አያቶቻቸው ኢትዮያዊነትን ለማግኘት ያደረጉትን ከፍተኛ ተጋድሎ እነሱም መካድ የለባቸውም። ያ ! ያለፈ ትውልድ ኢትዮጵያዊነቱን ከልቡ አምኖበት፣ ብዙ መስዋዕት ተቀብሎ ኢትዮጵያዊ ሆኗል። ከዚያ የቀጠለው ትውልድ ደግሞ፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ለብቻዋ እንድትቆም ለብዙ ዓመታት ተዋግቶ ነፃነቱን አግኝቷል።

እንግዲህ፣ ከአርባ ዓመታት በፊት ታሪካችንና ክብራችን ነው ብለው፣ ከኢትዮጵያ ጋር አንድ መሆንን የወሰኑትና፣ ከአርባ ዓመታት በኋላ ደግሞ ከኢትዮጵያ መለየትን የመረጡት ራሳቸው ኤርትራውያኖች ስለሆኑ፣ እነሱም በምርጫቸው፣ እኛም ኢትዮጵያውያኖች በመሠረታዊው አቋማችን ጸንተን መቀጠል አለብን። ታሪክ፣ የሰዎች የሥራ ውጤት ነው። የዛሬዎቹ ሰዎች ዛሬ የሚሠሩትን ለሚቀጥለው ታሪክ ያስመዘግባሉ እንጂ፣ ያለፈውን መሠረታዊውን ታሪክ እነሱ እንደፈለጉ፣ ምንጊዜም መደምሰስ አይችሉም።

# ምስጋና

1. የዚህን መጽሐፍ ዝግጅት ለማጠናቀቅና ለእትም ለማቅረብ አዲስ አበባ በቆየሁባቸው በሰባት ወራቶች ውስጥ፣ የተመቸ ማረፊያና የተለየ ጽሕፈት ቤት አዘጋጅቶ በመስጠት፣ በመጽሐፉ ዝግጅት ላይ ጽሑፎቼ የሚያርፉባቸውን ገጾች በቴክኒክ አቀማመጣቸውን በማስተካከልና ጠቃሚ የሆኑ ሀሳቦችን በመለገሥ፣ በጠቅላላው ሥራው እንዲቃናልኝ አስፈላጊ የሆኑትን ጉዳዮች ሁሉ በማሟላት፣ ወዳጄ ወንድሜ አቶ በትሩ አድማሴ የሰጠኝን ድጋፍና ያደረገልኝን እርዳታ ለማመስገን የምገልጽበት ቃላቶች ያጥሩኛል።

2. የመጽሐፉ ፕላን ከተነደፈበት ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያስፈልጉትን ምርምሮች በማከናወን፣ ሥነ ጽሑፎቼን በየታሪካቸው አካሄድ እያሰባሰበ ቁም ነገር ያላቸው አስተያየቶች በመስጠትና በጠቅላላውም እርማቶቼን በማስተካከል፣ ወንድሜ አቶ ደሀኔ ረታ ያደረገልኝን እርዳታ ምንጊዜም አልዘነጋውም።

3. የታሪክ ምርምርና ጥናት ለማድረግ በልዩ ልዩ አገሮች በተንዝኩባቸው በነዚህ ባለፉት ሰባት ዓመታት ውስጥ፣ የሕይወት ጓደኛዬ ወይዘሮ ገሊላ ተፈራ፣ ፋታ ከማይሰጠው ሥራዋ ጋር ብቻዋን በትዕግሥትና በብርታት ያሳለፈችውን አስቸጋሪ ጊዜ ከልብ በመነጨ ጥልቅ ስሜት አስታውሳለሁ።

4. በኒውዮርክ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለሪሰርች በቆየሁባቸው ስድስት ወራቶች፣ የተሟላ ማረፊያ በማዘጋጀትና አስፈላጊ የሆኑትንም ሰነዶች በማሰባሰብ ከፍ ያለ እርዳታ ያደረገችልኝን እህቴን ወይዘሮ ኸኑት መክብብን ከልብ አሰባታለሁ።

5. ወዳጄ ወንድሜ ፕሮፌሰር መርዕድ ወልደአረጋይ ገና ከመነሻው ጀምሮ እስከ መጽሐፉ እትመት መጨረሻ ድረስ፣ ጠቃሚ ዶክመንቶችን ከመጠቆም በላይ፣ የታሰበው ከፍሬ እንዲደርስ የሰጠኝን የማበረታቻ ምክር እያስታወስኩ ከልቤ አመሰግነዋለሁ።

ከ1992 ዓ.ም እስከ 1998 ዓ.ም ድረስ በልዩ ልዩ አገሮች እየተዘዋወርኩ የታሪክ ምርምርና ጥናት በማከናውንበት ጊዜ በማናቸውም መልክ ከፍተኛ እርዳታ ያደረጉልኝን ወዳጆቼን ጥልቅ ከሆነ ምሥጋናዬ ጋር ላስታውሳቸው እወዳለሁ።

-- አቶ ስብሐት ሐብለሥላሴ
-- ፕሮፌሰር ምናሴ ኃይሌ
-- ዶክተር ብሥራት አክሊሉ
-- አቶ ወንዶሰን መንገሻ
-- ዶክተር ሙሉጌታ ወዳጆ
-- አቶ ጴጥሮስ አክሊሉ
-- አቶ ተካልኝ ገዳሙ
-- ዶክተር መክብብ ገበየሁ
-- አቶ አስፋ መንገሻ
-- አቶ ኃይሉ ወልደሥላሴ
-- ልጅ ዮሐንስ መንገሻ ሥዩም
-- አቶ ሞሐመድ ኢብራሂም

I. ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት፣ በልዩ ልዩ አገሮች ለመጓጓዝ እንድችል በአየር ትራንስፖርት ከፍተኛ ዕርዳታ ላደረገልኝ

**የኢትዮጵያ አየር መንገድ**
**ETHIOPIAN AIR LINES**

ባለውለተኛነቴን እገልጻለሁ።

II. መጽሐፉን ለማስተዋወቅ የተሰናዳውን ፕሮግራም በተሟላ ዝግጅት ላስፈጸመልኝና ላበረታታኝ

**አቢሲኒያ ባንክ**
**ABYSSINIA BANK**

ጥልቅ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።

## መረጃዎች

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የተፈጸመውን የኤርትራን ታሪክ ጽፌ ለማቅረብ ያስቻለኝ፣ በየአገሩ እየተዘዋወርኩ ለሰባት ዓመታት ያደረግኳቸው ምርምሮችና ጥናቶች ብቻ አይደሉም። በመቅድሙም ላይ እንደጠቀስኩት፤

1ኛ/ ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ የንጉሡ ነገሥቱን አደራ ተቀብለው፤ ከ1945 እስከ 1952 ዓ.ም ድረስ፤ በዓለም መንግሥታት ሸንጎ ላይ ለሰባት ዓመታት ፋታ ያልሰጠ ትግል ያደረጉት ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ፤

2ኛ/ ኤርትራን ከፌዴሬሽን አስተዳደር ወደ ፍጹም አንድነት ለማሸጋገር ለአሥር ዓመታት ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት፣ ቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል፤

ባላቸው ማስታወሻዎችና ሰነዶች እንድጠቀም ስለፈቀዱልኝ፤ ይህን መጽሐፍ በብዙ ረገድ የተሟላ አቀራረብ እንዲኖረው ለማድረግ በጣም ረድቶኛል።

በተወለዱ በሰልሣ አንድ ዓመታቸው ደርግ በግፍ የገደላቸው ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ፤ ፍርድ አግኝተው በሕይወት ቆይተው ቢሆን ኖሮ፤ ከጣልያን ቅኝ አስተዳደር በኋላ የኤርትራን የወደፊት ዕድል ለመወሰን፣ በአራቱ የዓለም ኃያላን አገሮችና፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የተደረገውን የረዥም ጊዜ ውዝግብና፣ በመጨረሻም የተገኘውን ውጤት፣ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለዓለምም ሕዝብ እውነተኛውን ታሪክ በሰፊው ያቀርቡለት ነበር።

ከጦርነት እሳት ወጥቶ ከሥቃዩ ላልተላቀቀው ለመከረኛው የዓለም ሕዝብ፤ መብቱን ለመስጠትና ሠላሙን ለመመሥረት፤ የነ ሞሎቶቭ ሆነ የነ ኧርነስት ቤቨን፣ የነ ዲን አቸስን ሆነ የነ ዣርዥ ቢዶ የፍርድና የዲሞክራሲ አሠራር፤ መልኩ እንዴት እንደነበረ አክሊሉ ሀብተወልድ የታሪኩ ምስክር ነበሩ።

ቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል፤ በደርግ ዘመን ምንም እንኳ ከሞት ተርፈው ብዙ ነገሮች ያሳለፉ ቢሆኑም፤ አስተማማኝና ሠላም በሌለው ሕይወት አእምሮአቸው እየተሰቃየ፤ ጤናቸውም ስለአስቸገራቸው፣ በዚያ በሚያምር ብዕራቸው ለብዙ ዓመታት በአእምሮአቸው ያከማቿቸውን ማስታወሻዎች በጽሑፍ ሳያጠናቅቁ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ በሕይወት በነበሩበት ዘመን፣ ሁኔታው ሲፈቅድልህና ጊዜው ሲያመችህ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የመንግሥት ታሪክ የመጻፍ ዕድል ስለሚኖርህ፤ ከአሁኑ አሰብበት እያሉ ያተጉኝ ነበር። በተለይ የኤርትራን ጉዳይ ከመነሻው እስከ መጨረሻው የነበረውን የታሪክ ሂደት፣ ጥቂት ዕረፍት ባገኙ ቁጥር ያስጠኑኝ ስለነበረ፤ በዚያን ጊዜ የያዝኳቸው ማስታወሻዎች፣ በየአገሩ ላደረግኳቸው ምርምሮችና ዝርዝር ጥናቶች ትልቅ መሠረት ሆነውኛል። አክሊሉ ሀብተወልድ በዚያ በኤርትራ ሙግት ዘመን፤ በተለይ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እና ከጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ ጋር የነበራቸውን ኮሬስፖንዳንሶች፤ ከዚህም በላይ

ከንጉሠ ነገሥቱ በቀጥታ በኮድ ቴሌግራምና በጽሑፍ የሚደርሷቸውን መምሪያዎች እንዳውቃቸውና ስነዶቹንም እንድጠቀምባቸው ለግሠውኛል::

ቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ ከ1987 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ፣ በተለያዩ ጊዜያቶች በሮምና በአዲስ አበባ እያገኘኋቸው፤ ኤርትራን ከፌዴሬሽን ወደ ኢትዮጵያ አስተዳደር ለማዋሀድ ስለተደረገው ጥረት፤ በዝርዝር የሰጡኝን ጥናቶች መዝገቢያቸዋለሁ:: በ1995 ዓ.ም ጤናቸው እያስቸገራቸውና አቅምም እያነሳቸው ሲሄድ፤ « ...... *ይህን የኤርትራን ታሪክ በሚገባ ለመጻፍ ትችላለህ ብዬ ስለማምን፣ የማውቀውን ሁሉ እንድነግርህ ወሰኛለሁ* ...... » ብለው ወደ ሰባ (70) ገጽ የሚጠጉ በብዕራቸው የተጻፉ ማስታወሻዎች ሰጥተውኛል::

ከእነዚህ ከሁለቱ ታላላቅ ሰዎች (ከአክሊሉና ከአስፍሐ) በስተቀር፣ በጠቅላላው በኤርትራ ጉዳይ በቅርብም ሆነ በሩቅ ተካፋይነት የነበራቸውን ሰዎች እየቀረብኩ በማነጋገሬ የተቻላቸውን ሁሉ ረድተውኛል:: ከእነዚህም መካከል፤

1. በኤርትራ ሙግት ዘመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር፤ ቀጥሎም ምክትል ሚኒስትር የነበሩት ቢትወደድ ዘውዴ ገብረሕይወት፤

2. የኤርትራ ጉዳይ ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ የአቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ልዩ ጽሕፈት ቤት ሹም የነበሩትና፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች አባል በመሆን በየጉባኤው የተካፈሉት ልጅ አምሩ ዘለቀ፤

3. ለአራት ዓመታት (1946 - 1950) በአሥመራ የንጉሠ ነገሥቱ ላይዘን ኦፊሰር የነበሩት፤ ሌፍትናንት ጄኔራል ነጋ ኃይለሥላሴ፤

4. ያገር ፍቅር አንድነት ትጉህ አባል የነበሩት የራስ ኃይሌ ተሰፋማርያም ልጅ፤ ፊታውራሪ ኪዳነማርያም ኃይሌ፤

5. "የፍቅሪ ሀገር የሴቶች" ፕሬዚዳንት ሆነው ከፍተኛ ሞያ የፈጸሙት የታወቁት የወይዘሮ አስካለማርያም የማነ ልጅ፣ ብሪጋዲየር ጄኔራል አበበ ተፈሪ፤ ይገኙበታል::

ከዚህም በቀር፤ ቀደም ብዬ በመቅድሙ ላይ እንደጠቀስኩት በጋዜጠኝነት ሞያ የተሰማራሁት የአሥራ ስምንት ዓመት በነበረኝ ጊዜ ስለሆነ፤ በማስታወቂያና በጋዜጣ መሥሪያ ቤት (ኋላ የማስታወቂያ ሚኒስቴር) በአገለገልኩበት በአሥራ ስምንት ዓመታት ውስጥ፤ በኤርትራ ጉዳይ ያየሁትና በጽሑፍ የመዘገብኩት ሁሉ፤ ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት የተለየ ድጋፍ ሆኖኛል::

ከ1992 እስከ 1999 ዓ.ም ድረስ ለሰባት ዓመታት በልዩ ልዩ አገሮች እየተዘዋወርኩ ባደረግኳቸው ጥናቶች የመረመርኳቸው ሰነዶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

# Bibliography


UNITED - NATIONS (New York)

*The Ethiopian Claims and Position in Regard to the Former Italian Colonies. Documentation Presented by the Ethiopian Delegation*, A/C 1/W.8, 20 October 1948, Restricted.

General Assembly Official Records:

Third Session, Part I, Plenary Meetings, *Summary Records of Meetings 21 September - 12 December 1948, Paris*, Palai de Chaillot, 1949;

Third Session, Part I, General Committee;

Third Session, Part II, Plenary Meetings, *Summary Records of Meetings 5 April - 18 May 1949*, Lake Success (New York), 1949;

Third Session, Part II, First Committee, *Summary Records of Meetings 5 April - 13 May 1949 (id. 1949);*

Fourth Session, Plenary Meetings, *Summary Records of Meetings 20 September - 10 December 1949* (id. 1950);

Fourth Session, Plenary Meetings, *Annex* (id. 1950);

Fourth Session, First Committee: Political and Security Question, *Summary Records of Meetings 20 September 6 December 1949 (id. 1950);*

Fourth Session, First Committee, *Annex* (id. 1950);

United Nations, 1950, *Report of the United Nations Commission for Eritrea.* General Assembly official Records supplement no. 8(A/1285). Lake Success, New York;

United Nations, 1952, *Final Report of the United Nations Commissioner in Eritrea.* General Assembly Official Records supplement no. 15 (A/2188). New York;

**United Nations, 1952, *Year Book of the United Nations. New York.***

<u>UNITED STATES</u> (Washington D.C.)

National Archives And Congress Library

*United States and Italy 1936-1946. Documentary Records,* Department of State Publication 2669, Washington, United States Government Printing Office, 1949.

*Paris Peace Conference 1946: Selected Documents, Washington,* United States Government Printing Office, 1947.

Foreign Relations of the United States. Diplomatic Papers (FRUS):

*1942, vol. III: Europe* (Washington, United States Government Printing Office 1961);

*1943, vol. III: Europe* (id. 1963);

*1943, vol. IV: The Near East and Africa* (id. 1964);

*1943, The Conferences at Washington and Quebec 1943* id. 1970);

*1945, The Conferences at Malta and Yalta 1945* (id. 1955);

*1945, The Conference of Berlin (Postdam),* voll. I e II (id. 1960);

*1945, vol. II: General: Political and Economic Matters* (id. 1967);
*1945, vol. IV: Europe* (id. 1968);
*1946, vol. VII: The Near East and Africa* (id. 1969);
*1946, vol. II: Council of Foreign Ministers* (id. 1970);
*1946, vol. III: Paris Peace Conference: Proceedings* (id. 1970);
*1947, vol. IV: Paris Peace Conference: Documents* (id. 1970);
*1947, vol. III: The British Commonwealth: Europe* (id. 1972);
*1947, vol. V: The Near East and Africa* (id. 1971);
*1948, vol. I: General; The United Nations, part 2* (id. 1976);
*1948, vol. III: Western Europe* (id. 1974);
*1948, vol. V: The Near East, South Asia and Africa, part 2* (id. 1976)
*1949, vol. IV: Western Europe* (id. 1975);
*1949, vol. VI: The Near East, South Asia, and Africa* (id. 1977).

UNITED KINGDOM

Public Records Office

Entrean Affairs 1945 - 1950

FO - 371: File No. 73873, 74, 75, 76, 77, 78, 79, 80.73899, 73900, 69349, 113520, 146570, 108196, 108191, 96723, 96722, 108201, 113519, 73877, 63198, 69350, 69360, 69366,69300.

FRANCE

**Ministère des Affaires étrangères**

**Quai D'Orsay Paris**

**1. Relation avec l'Italie - question des anciennes colonies italiennes, conceme principalement les revendications éthiopiennes sur l'Eritrée.**

**2. La Commission d'enquête sur les anciennes colonies italiennes et, à un degré moindre, la question de la reprise des relations diplomatiques entre l'Ethiopie et l'Italie. (Octobre 1944 - décembre 1948).**

A) Doc. K9
B) Doc. K. Afrique Levant Vol. 54)
3. C) Conference de la paix (1946)
Document de la Conférence de Paris 4 Voll, Paris imprimerie nationale 1947.

ARCHIVIO STORICO DEL MINISTERO DEGLI AFFARI ESTERI

Affari Politici, 1946 - 1956,Roma

Fondo ministero dell Africa Italiana
Fondo Presidenza del Consiglio dei Ministri
Verbali delle sedute del Consiglio dei Ministri
Carte Sforza
Serie Affari Politici
Fondo Ambasciata Parigi

Fondo Ambasciata Londra
- Memorandum on the Italian Colonies
Presented by the italian Government 1945

SFORZA CARLO,
L'italia El Problemi Della Pace Europea, Milano-Roma Edizioni Viola, 1944.

BRUSASCA GIUSEPE,
Il Ministero Degli Affari Esteri. Governo E Diplomazia Al Servizio De Popola (1948).

## SELECT BIBLIOGRAPHY

Zewde Gebre-Sellassie (Doctor Dejasmatche)
Eritrea, Ethiopia in the context of the Red Sea and Africa (1976).

Pankhurst, Sylvia,
Ethiopia And Eritrea, 1941 - 1952 -Woodford Green, England: Lalibela House. 1953

Spencer, John, H.,
*Ethiopia at Bay: A Personal Account of the Haile Sellassie Years,* Michigan: Reference Publications Inc. ,1983

Sforza, Carlo,
Cinque anni a palazzo Chighi. La politica estera italiana da 1947 al 1951. Roma: Atlante, 1952.

Trevaskis, G.K.N.,
Eritrea: *A Colony in Transition, 1941 - 1952.* Oxford University Press, 1960,

Rossi Gianluigi,
L'africa Italiana Verso L'indipendenza (1984).